# የገቢና የወጪ ንግዱ የሚዛን ጉድለት አሁንም ትኩረትን ይሻል



የወጭ ንግድ (ኤክስፖርት) አፈጻጸም ባለፉት ዓመታት ቅናሽ ሲያሳይ በአንጻሩ የገቢ ንግዱ እያሻቀበ፣ ልዩነቱም እየሰፋ መምጣቱን የተለያዩ መረጃዎች እየጠቆሙ ነው። በማምረቻ ኢንዱስትሪ ዘርፍ (ማኒፋክቸሪንግ) የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ያለፉት አራት ዓመታት በተከታታይ ዕድገቱ እየጨመረ የመጣና በአማካይ በ36 በመቶ ዕድገት ቢመዘገብም ይህ እድገት ከዕቅዱ ጋር ሲነጻጸር ከ36 በመቶ መብለጥ አልቻለም።

ክቡር ጠ/ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ባለፈው ሳምንት ባቀረቡት የመንግሥት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በ2007 በጀት ዓመት ስድስት ወራት የወጪ ንግድ አፈጻጸም ደካማ መሆኑን አምነዋል። በአንጻሩ የገቢ ንግዱ በየዓመቱ እያደገ መሄዱ የወጪ ንግዱ ግን ቅናሽ ማሳየቱ ለኢኮኖሚውም ቢሆን ፈታኝ መሆኑን አቶ ኃ/ማርያም ተናግረዋል።

የሀገሪቱ ኤክስፖርት ገቢ ከ85 በመቶ በላይ በግብርና ምርቶች ላይ ጥገኛ መሆኑ፣ ከግብርና ምርቶችም መካከል ሰፊውን የገበያ ድርሻ የሚወስደው የቡና ምርት መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን በዓለም ገበያ የቡና ዋጋ ሲያሽቆለቁል ገቢውም አብሮ የሚያሽቆለቁልበት ሁኔታ መኖሩ ትልቅ ችግር ሆኗል። የቡና ምርትን በብዛትና በጥራት በማሳደግ ዋጋ ቢወርድም አቅርቦትን በማሻሻል ጥሩ ገቢ ማግኘት እንዲቻል ታስቦ በመንግስት በኩል እየተከናወኑ ያሉ ስራዎች መኖራቸው ባይካድም አጥጋቢ ባለመሆናቸው ውጤቱ ደካማ ሆኖ እንዲታይ አንድ ምክንያት መሆኑ አልቀረም።

በኢንዱስትሪው ዘርፍ የመሰረተ ልማት አቅርቦት ችግር፣ የመስሪያ ቦታ፣ የፋይናንስ አቅርቦት፣ የግብዓት ችግሮች በሰፊው የሚታይ ሰሆን እነዚህን ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት መንግስት እያደረገ ያለውን ጥረት አቀናጅቶ ሊቀጥልና የገቢና ወጪውን የንግድ ሚዛን ጉድለት ቢያንስ እንዲቀራረብ ተግቶ ሊሰራ ይገባል።

በተጨማሪም የማምረቻ ዘርፉ ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲቀጥል የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ መሆን ያለበት ሲሆን የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ኢንዱስትሪዎች በገቡት ውለታ መሠረት ምርቶቻቸውን ለደንበኞቻቸው እንዳያቀርቡ እንቅፋት እየሆነ መጥቷል። መንግስት የኃይል ችግር የለብኝም ከሚለው ተደጋጋሚ መግለጫው ባሻገር የኃይል መቆራረጥ ችግርን በመለየት የማያዳግም መፍትሔ መስጠት እስካልቻለ ድረስ ችግሩ እየተንከባለለ መቀጠሉ የማይቀር ይሆናል።

በአጠቃላይ የኤክስፖርት ዘርፉ ተወዳዳሪና ጠንካራ እንዲሆን መንግስት እስካሁን ያደረገው ጥረት በቀላሉ የሚታይ ባይሆንም የዘርፉን ችግሮች ለመፍታት አሁንም የዘርፉ ተዋንያን ጋር በቅርበት መስራትና የሚያደርገውንም እገዛ በጥናት ላይ ተመስርቶ ሊያጠናክር ይገባል።■

## ቁጥሮች

የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር

በ2006 ዓ.ም
87.9 ሚሊዮን

በ2007 ዓ.ም
90 ሚሊዮን

በ2029 ዓ.ም
136 ሚሊዮን

ምንጭ:-
ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ

## መልዕክቶች

### የትራፊክ አደጋው አሳስቦናል

በአዲስ አበባ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የውስጥ ለውስጥ መንገዶችን ጨምሮ በርካታ መንገዶች እየተሰሩ ይገኛሉ። ከእነዚህ መንገዶች መበራከት እና መስፋፋት ጋር ተያይዞ ታዲያ በየዕለቱ በርካቶች በትራፊክ አደጋ ምክንያት ህይወታቸውን እየተነጠቁ ናቸው። እኛም በየዕለቱ በትራፊክ አደጋ ምክንያት ይሄን ያህል ሰዎች ህይወታቸውን አጡ የሚለውን ዜና እየለመድነው መጥተናል። በዚህ ትራፊክ ምክንያት ደግሞ ጉዳቱ የደረሰበት ሰው ብቻ ሳይሆን ሌሎች በዙሪያው ያሉትም ተጎጂዎች ናቸው። አንድ መኪና አንድ ሰው ገጭቶ ሲገድል የተገጨው ሰው ይሞታል፤ የገጨው ማረሚያ ቤት ይገባል። በእነዚህ ሁለት ሰዎች ዙሪያ ያሉት ሰዎች ደግሞ የህይወታቸው መስመር ይለወጣል። በዚህ አደጋ በአሁኑ ጊዜ ህይወታቸው እየተቀጠፈ ያለው ደግሞ ሰርተው እራሳቸውን እና ቤተሰባቸውን አልፎ ተርፎም ሀገሪቱን ይጠቅማሉ የሚባሉ አምራች ዜጎች ናቸው። በዚህ ሳቢያ የስንቱ ቤት ፈርሶ የስንቱ ቤተሰብ እንደተበተነ መገመት ቀላል ነው።

ለዚህ በየዕለቱ ለሚስተዋል አሰቃቂ የትራፊክ አደጋ ተጠያቂው ማንም ይሁን ማንም ችግሩ ግን ጊዜ የሚሰጥ አይደለም። አሽከርካሪዎች ከሚሰጣቸው የመንጃ ፈቃድ በተጨማሪ ያላቸው ስነ-ምግባርም ከግምት ውስጥ መግባት ያለበት ይመስለኛል። በመጠጥ እና ጫት ራሳቸውን ከሳቱ አሽከርካሪዎች ከዚህ የተለየ ተግባር መጠበቅ ከእባብ የእርግብ እንቁላል እንደመጠበቅ ነው። ይሄን እና የመሳሰሉትን የትራፊክ አደጋ መንስኤዎች የሚመለከተው አካል አጣርቶ እርምጃ የማይወስድ ከሆነ ማንም ሰው በሰላም ወጥቶ በሰላም ስለመመለሱ እርግጠኛ አይደለም። አስፈላጊ ከሆነ እግረኛውም ስርዓቱን ጠብቆ የሚጓዝበት እና ከአደጋው ራሱን ሊጠብቅ የሚችልበት ትምህርት በተከታታይ እና በቁርጠኝነት ሊሰጠው ይገባል። በማነህ ማነህ የዜጎች ህይወት እየተቀጠፈ ነውና አፋጣኝ መፍትሄ መፈለግ አለበት።

በስልክ የተሰጠ አስተያየት

### የማጥፋት ሩጫ

በተለያዩ የአዲስ አበባ ቦታዎች ላይ ለመልሶ ማልማት ታስበው በርካታ ግንባታዎች እየፈረሱ ነው። ነገር ግን እነዚህ ግንባታዎች በውስጣቸው ያሉትን ሰዎች ለማስለቀቅ ብቻ የተቸኮለ ይመስል በመፍረስ ጅምር ላይ ቀርተው ይታያሉ። እነዚህ ግንባታዎች የሚፈርስባቸው አካባቢዎች የመልሶ ማልማት ስራው በሚጀመርበት ወቅት ቢፈርሱ እና በአፋጣኝ ወደ ስራ ቢገባ መልካም ነበር። አሁን እየታየ ያለው ግን አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩትን ግንባታዎች በተወሰነ ደረጃ እያፈረሱ በውስጡ የነበሩትን ማፈናቀል እና በጅምር መተው ነው። እነዚህ ግንባታዎች በአንድ እና በሁለት ወራት ውስጥ ስራ ቢሰራባቸው ለባለቤቱም ሆነ ለሀገር ከፍተኛ ጥቅም ሊያስገኙ የሚችሉ ይሆናሉ። እኔ በበኩሌ መልሶ ማልማቱን ባልቃወምም መኖሪያ እና ንግድ ቤቶችን ለማፍረስ ከመሯሯጥ በፊት በቦታዎቹ ላይ ግንባታ ለመጀመር የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማሟላቱ ለሁሉም ወገን ጠቃሚ እንደሆነ መጠቆም እፈልጋለሁ።

አቶ ታደሰ - ከቂራ


"ሰንደቅ" ጋዜጣ በሰንደቅ የሕትመትና የማስታወቂያ አገልግሎት ኃ/የተ/የግ/ማኅበር በንግድ ሚኒስቴር በንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር 14/673/7498/2004፣
በብሮድካስት ባለሥልጣን የምዝገባ ቁጥር 38/2001 የተመዘገበ ሳምንታዊ ጋዜጣ ነው

ዋና አዘጋጅ
ፍሬው አበበ
ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር 12/201
0911 61 79 35
abebeferew@gmail.com

ም/ዋና አዘጋጅ
ፋኑኤል ክንፉ
0911 865119
Kinfu2006@yahoo.com

አዘጋጅ
ፀጋው መላኩ

ከፍተኛ ሪፖርተሮች
አሸናፊ ደምሴ
መስከረም አያሌው

ግራፊክ ኤዲተር
ነብዩ መሥፍን
0911 18 09 33
nebiyou1st@yahoo.com

ኮምፒዩተር ጽሁፍ
አለምነሽ ታከለ
ሰብለወንጌል ንጉሴ
ምናለሽዋ ተ/አረጋይ

ህትመት ክትትልና ስርጭት
በዛብህ ተክሉ
0911 41 68 00

ማስታወቂያ ሽያጭ
ባይለየኝ ወርቁ
bayleyworku@gmail.com
0921 56 95 03
0912 95 67 95


አታሚ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት
አድራሻ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 07 የቤት ቁጥር 984

የአሳታሚው አድራሻ:- ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 05/03 የቤት ቁጥር 027 ከአትላስ ሆቴል በስተጀርባ 011-6-62 81 90/ 011-6-18 40 34/ 0911 95 58 16 ፖ.ሣ.ቁ. 80964
www.sendeknewspaper.com

# የፖለቲካ ፓርቲዎች ዕጩዎች ምዝገባ ዛሬ ይጠናቀቃል

## - ከኢህአዴግ ቀጥሎ ሰማያዊ፣ መድረክ እና ኢዴፓ በርካታ ዕጩዎችን አስመዝግበዋል


ጠ/ሚ ሃ/ማሪያም ደሳለኝ


ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ


ወ/ሮ አስቴር ማሞ


ኢ/ር ይልቃል ጌትነት


ዶ/ር መረራ ጉዲና

በጋዜጣው ሪፖርተር

በመጪው ግንቦት ወር 2007 ዓ.ም ለሚካሄደው አምስተኛ ዙር ሀገር አቀፍ ምርጫ የዕጩዎች ምዝገባ ዛሬ የካቲት 4 ቀን 2007 ዓ.ም የሚጠናቀቅ ሲሆን ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በተገኘው መረጃ መሠረት እስከየካቲት 2 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ 38 ያህል ፓርቲዎች 1ሺ306 ዕጩዎች ማቅረባቸውን ታውቋል:: በተጨማሪም 10 ያህል ዕጩዎች በግል የቀረቡ ሲሆን ከነዚህ መካከል አንድ ሴት ይገኙበታል::

የቦርዱ የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ደምሰው በንቲ ለሰንደቅ ጋዜጣ እንደገለጹት እስከየካቲት 2 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ ብቻ ኢህአዴግ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት 457፣ ለክልል ም/ቤቶች 1ሺ 222 ያህል ዕጩዎችን አቅርቧል:: መድረክ ለተወካዮች 214፣ ለክልል 488 ሲያቀርብ ኢዴፓ ለተወካዮች 127፣ ለክልል 136 ያህል አቅርቧል:: ሰማያዊ ፓርቲ በበኩሉ ለተወካዮች 83፣ ለክልል 82 ማቅረቡ ታውቋል:: ይህ አሃዝ እስከምዝገባው ማጠቃለያ የካቲት 4 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ ሊለወጥ እንደሚችል አቶ ደምሰው ጠቁመዋል::

ከኢህአዴግ በተገኘ መረጃ መሠረት ኢህአዴግ ለመጪው ምርጫ ዕጩዎቹ ማስመዝገቡን ማጠናቀቁን ይጠቅሳል:: በዚሁ መሠረት ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት 501፣ ለክልል ም/ቤቶች 1ሺ 322 ያህል ዕጩዎችን ማስመዝገቡን ይፋ አድርጓል:: ለፌዴራል ፓርላማ ከቀረቡት ዕጩዎቹ መካከል 300 ያህሉ ከፍተኛ የግንባሩ አመራሮች ሲሆኑ 290 ያህሉ ደግሞ መካከለኛ አመራሮች መሆናቸው ታውቋል:: ግንባሩ ለፓርላማ ካቀረባቸው ዕጩዎች መካከል 38 በመቶ ያህሉ ሴቶች ናቸው::

ከሰማያዊ ፓርቲ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶዮናታን ተስፋዬ ለሰንደቅ ጋዜጣ እንደተናገሩት ፓርቲው እስከ የካቲት 3 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ ባሉት ጊዜያት ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት 345፣ ለክልል ም/ቤት 597 ዕጩዎችን ማስመዝገባቸውን አረጋግጠዋል:: የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት በአዲስ አበባ ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ፣ ምክትል ፕሬዚደንት አቶ ስለሺ ፈይሳ በአዲስ አበባ ሽሮ ሜዳ አካባቢ፣ በምርጫ ቦርድ ዕውቅና ከተነፈገው የቀድሞ አንድነት ፓርቲ አባላት የሆኑና ሰማያዊን ከተቀላቀሉት መካከል አቶ አበበ አካሉ በለገዳዲ አካባቢ፣ አቶ አማኑኤል አዱኛ በአዲስ አበባ ልደታ አካባቢ፣ አቶ ነገሰ ተፈራ በአዲስ አበባ በቦሌ አካባቢ፣ አቶ ስንታየሁ ቸኮል በአማራ ክልል እንደሚወዳደሩ አቶ ዮናታን ጨምረው ገልፀዋል::

በምርጫ ቦርድ ባይረጋገጥም ምንጮቻችን እንደጠቆሙት ጠ/ሚኒስትር ኃ/ማርያም ደሳለኝ በወላይታ አካባቢ፣ በምክትል ጠ/ሚኒስትር ማዕረግ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትር ወ/ሮ አስቴር ማሞ በአዲስአበባ ምርጫ ክልል 19 ንፋስ ስልክ አካባቢ፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታደሰ ኃይሌ በአዲስ አበባ ምርጫ ክልል 20 ቄራ አካባቢ፣ የአዲስአበባ መገናኛ ብዙሃን ኃላፊ ወ/ሮ ፍሬህይወት አያሌው አዲስአበባ ምርጫ ክልል 7 አዲስከተማ አካባቢ፣ በሚኒስትር ዴኤታ ማእረግ የጠ/ሚኒስትሩ አማካሪ አቶ ሰለሞን ተስፋዬ በአዲስአበባ ቂርቆስ አካባቢ ኢህአዴግን ወክለው ከሚወዳደሩት መካከል ይጠቀሳሉ::

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) ከፍተኛ አመራሮች መካከል ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ በሐዲያ አካባቢ፣ ዶ/ር መረራ ጉዲና በአምቦ አካባቢ፣ አቶ ጥላሁን እንደሻው በደቡብ ቡርጂ ወረዳ አካባቢ እንደሚወዳደሩ ታውቋል::

የመድረክ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ጥላሁን እንደሻው ለሰንደቅ ጋዜጣ እንደተናገሩት የአረና ከፍተኛ አመራሮች በትግራይ የሚወዳደሩ መሆናቸውን በኦሮሚያ፣ በትግራይ እና በደቡብ ክልሎች በርካታ ዕጩዎችን ማቅረባቸውን እንዲሁም በአማራ በተወሰኑ አካባቢዎች ዕጩዎች ማቅረባቸውን ተናግረዋል::

የምርጫ ቦርድ ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የዕጩዎች ምዝገባ መጠናቀቂያ ጊዜ ጥር 27 ቀን 2007 ዓ.ም የነበረ ሲሆን የፖለቲካ ፓርቲዎች ጊዜው እንዲራዘምላቸው ለቦርዱ ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ምዝገባው እስከየካቲት 4 ቀን 2007 ዓ.ም እንዲራዘም መወሰኑ የሚታወስ ነው::■

# የቀብር ማስፈፀሚያ ኢንሹራንስ ሊጀመር ነው

በፀጋው መላኩ

በኢትዮጵያ እስካሁን ተግባራዊ ያልሆነው የቀብር ማስፈፀሚያ ኢንሹራንስ በቅርቡ ተግባራዊ ሊሆን ነው:: ኢንሹራንሱ ተግባራዊ የሚሆነው በኢትዮጵያ መድን ድርጅት ሲሆን ይህም በመጪው ሀሙስ ይፋ ይደረጋል ተብሎ ይጠበቃል:: ኢንሹራንሱ በበርካታ ሀገራት ተግባራዊ ሆኖ እየተሰራበት ይገኛል::

በሌሎች ሀገራት በስፋት የሚሰራበት ይህ የኢንሹራንስ አይነት፤ ኢንሹራንሱን የገዙ ሰዎች ዘመድ አዝማዶቻቸው በሞት ሲለዩአቸው የቀብር ስነስርአቱን ወጪ የሚሸፍን ነው:: ይህም የሟች ቤተሰቦች ለቀብር ስነስርአት በድንገት ከሚያወጧቸው ከፍተኛ ወጪዎች የሚታደግ ሲሆን በሌሎች ሀገራት ያለው አሰራር በአንድ አካባቢ የቀብር ማስፈፀሚያ ኢንሹራንስ የገዛ ሰው አካባቢውን ቢቀይርም ኢንሹራንስ ሽፋኑ ባለበት ቦታ ተከትሎት የሚሄድ መሆኑ ነው::

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የቀብር ማስፈፀሚያ ኢንሹራንስ ሐሙስ እለት የፋይናስ ድርጅቶች አጀንሲ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎችና ሌሎች የመንግስት ባለስልጣናት በተገኙበት ይፋ ይሆናል ተብሎ የሚጠበቅ መሆኑን ያገኘነው መረጃ ያመለክታል::■

# ለሦስተኛ ወገን የሚተላለፉ የአድባራት የንግድ ማዕከላት ኪራይ አሳሳቢ ኾኗል

- በቤተ ክርስቲያን በር ሳይ የተከራየው የቢራ ማከፋፈያና የውበት ሳሎን ምእመናንን አስቆጥቷል፤ ውሉ ተቋርጦ ስፍራው ነጻ እንዲደረግ መመሪያ ተሰጥቷል
- የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት አስተዳደር የአድባራት መሬትና የንግድ ተቋማት ኪራይን በተመለከተ ለሚካሔደው ጥናት ዕንቅፋት መፍጠሩ ተጠቁሟል

በጋዜጣው ሪፖርተር

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት አብያተ ክርስቲያናት ለግለሰቦች የሚያከራዩዋቸው በርካታ የንግድ ማዕከላት/ሱቆች/ ቤተ ክርስቲያኒቱን በማይጠቅምና በሚያስተች አኳኋን ለሦስተኛ ወገን በከፍተኛ ጥቅም እየተላለፉ (ቁልፋቸው እየተሸጠ) እንደሚገኝ ተገለጸ።

በሀገረ ስብከቱ ገዳማትና አድባራት ይዞታ ውስጥ የሚገኙ መሬቶችንና ሕንፃዎችን ኪራይና አጠቃቀም በመፈተሽ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ዘላቂ ጥቅም የሚሰጡባቸውን መንገዶች የሚያመቻች ጥናት ለማቅረብ የተቋቋመው ኮሚቴ እያካሔደ ባለው የማጣራት ሥራ፣ ግለሰቦች ከአድባራቱ የሚከራዩዋቸው አብዛኞቹ የንግድ ማእከላት /ሱቆች/ ‹‹እጅግ በጣም አሳዛኝ በኾነ መንገድ የተከራዩና ለሦስተኛ ወገን የተሸጡ›› ሲኾን የመካነ መቃብር ይዞታም እየተቆረሰ ከዓላማው ውጭ መዋሉ እንደተረጋገጠ ተመልክቷል።

በተመረጡ 69 አድባራትና ገዳማት ላይ የጀመረውን ጥናት በድርጊት መርሐ ግብሩ መሠረት እያከናወነና ግብዐት ሊኾኑ የሚችሉ መረጃዎችንም እያሰባሰበና እያደራጀ እንደሚገኝ የገለጸው ኮሚቴው፣ ጥር 26 ቀን 2007 ዓ.ም. ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ባቀረበው ጽሑፍ÷ አፋጣኝ ምላሽ ያስፈልጋቸዋል ያላቸው አሳሳቢ ችግሮች መመሪያና ማስተካከያ እንዲሰጥባቸው ጠይቋል።

በገፅ 7 ዞሯል

# ዳሸን ባንክ፡ የላቀ አፈፃፀም ያሳዩ ደንበኞቹን ሸለመ

በፀጋው መሳኩ

ዳሸን ባንክ በኤክስፖርት ዘርፍ የላቀ አፈፃፀም ያሳዩ ደንበኞቹን የካቲት 3 ቀን 2007 ዓ.ም በሸራተን አዲስ ሆቴል ባካሄደው ሥነ-ሥርዓት የዕውቅና ሽልማት ሰጠ።

ባንኩ በኤክስፖርት ዘርፍ የላቀ አፈፃፀም ላሳዩ ደንበኞቹ የዕውቅና ሽልማት በሰጠበት በዚሁ ፕሮግራም ላይ ሽልማቱን በአራት ዘርፍ በመክፈል ማለትም በፕላቲኒየም፣ በጎልድ፣ በሲልቨር፣ በብሮንዝ ደረጃ ሰጥቷል።

ትናንት ምሽት ለሕትመት እስከገባንበት ሰዓት ድረስ በፕላቲንየም ደረጃ ባንኩ ዕውቅና ከሰጣቸው ላኪዎች መካከል ሆራይዘን ኢንቨስትመንት

*ዳሸን ባንክ በየዓመቱ የደንበኞች ቀን ሲያከብር የቆየ ሲሆን፤ በኤክስፖርት ዘርፍ የተሻለ የውጭ ምንዛሪ ያስገኙ ደንበኞቹን ሲሸልም ይህ የመጀመሪያው ነው*

ግሩፕ፣ በእህልና ጥራጥሬ ኤክስፖርት አቶ አብርሃም አበበ- ከአዳማ፣ ሞጆ ሞደርን ኤክስፖርት አባቲየር የተባሉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ተሸልመዋል።

ዳሸን ባንክ በየዓመቱ የደንበኞች ቀን ሲያከብር የቆየ ሲሆን፤ በኤክስፖርት ዘርፍ የተሻለ የውጭ ምንዛሪ ያስገኙ ደንበኞቹን ሲሸልም ይህ የመጀመሪያው ነው።

በሥነ-ሥርዓቱ ላይ ዶ/ር ያዕቆብ ያላ የንግድ ሚኒስትር ዴኤታ በክብር እንግድነት የተገኙ ሲሆን፤ በተጨማሪም የባንኩ የቦርድ ሊቀመንበር አቶ ተካ አስፋውን ጨምሮ የባንኩ ፕሬዚደንት አቶ ብርሃኑ ወ/ስላሴና ሌሎች የባንኩ ሥራ መሪዎችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።■

# ትውልደ ኢትዮጵያውያን አይሁዶች ዛሬም ጠባሳቸው አልሻረም ተባለ

በመስከረም አያሌው

በእየሩሳሌም ያሉ ኢትዮጵያውያን በተረጋጋ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ኑሯቸውን እየመሩ እንዳልሆነ ተገለፀ።

እየሩሳሌም ፖስት በጉዳዩ ላይ ጥናት ያደረጉ ባለሞያዎችን ጠቅሶ እንደዘገበው፤ ዘመቻ ሙሴን ጨምሮ በተለያዩ ጊዜያት ወደ እየሩሳሌም የገቡ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ስደቱ ጥሎባቸው ያለፈው ጠባሳ ዛሬም ድረስ ህይወታቸውን በጭንቀት እንዲመሩ አድርጓቸዋል። ትውልደ ኢትዮጵያውያኑ በሱዳን በኩል ተሻግረው ወደ እየሩሳሌም ለመግባት በተጓዙት ጉዞ ወቅት የደረሰባቸውን ተገዶ መደፈር፣ ዝርፊያ፣ ግድያ፣ ህመም እና ረሀብ እያሰቡ በከፍተኛ የስነ-ልቦና ችግር ውስጥ ናቸው።

ትውልደ ኢትዮጵያውያኑ በተፈጠረባቸው የስነ-ልቦና ቀውስ ምክንያት ከአይሁዳውያን ባህል እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ጋር ለመጣጣም እየተቸገሩ ናቸው። በምናባቸው ስለዋት የነበረችውን እየሩሳሌም ከማግኘት ይልቅ ወደ ሀገሪቱ እንደገቡ የጠበቃቸው ድህነት፣ መገለል፣ ከኢትዮጵያ ለየት ያሉ ሕጎች፣ እንዲሁም አይሁዳዊነታቸውን የመጠርጠር ችግሮች ለዚህ የስነ-ልቦና ቀውስ እንደዳረጓቸው ተገልጿል። ድህነትን ለማምለጥ ሴቶቹ በተለያዩ ሙያ በማይጠይቁ ስራዎች ላይ የሚሳተፉ ሲሆን ወንዶቹ ግን የሚሰሩትን ነገር በማጣት ይሰቃያሉ። ወንዶች በኢትዮጵያ የነበራቸውን ክብር ማግኘት ባለመቻላቸው በሚፈጠርባቸው የስነ-ልቦና ቀውስ በመነሳሳትም በአይሁዳውያን ዘንድ ነውር የሆኑ እንደ ሚስቶቻቸውን መደብደብ፣ መግደል፣ ግፋም ሲል እራሳቸውን ማጥፋት የመሳሰሉ ሕገወጥ ተግባራትን እንደሚፈፅሙ ዜናው አስነብቧል።

በአሁኑ ወቅት አንድ መቶ ሰላሳ አምስት ሺህ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና እዚያው የተወለዱ አይሁዳውያን መሰረታቸውን በሀገሪቱ እንደጣሉ የገለፀው ዘገባው፤ እየሩሳሌም ከገቡት ትውልደ ኢትዮጵያውያን መካከል 28 በመቶዎቹ ወደእየሩሳሌም በመግባታቸው የገጠማቸው ችግር ጠባሳ ተጠቂዎች እንደሆኑ አብራርቷል። ወደእስራኤል ከገቡት ትውልደ ኢትዮጵያውያን መካከል 80 በመቶዎቹ በጉዞ ወቅት ዘመዶቻቸውን ያጡ ናቸውም ተብሏል። ብዙዎቹ ወላጆች ሚስጢራቸውን ለህክምና ባለሙያዎች እንኳን ለመናገር ካለመፈለጋቸው የተነሳ ግራ ተጋብተው እንደሚኖሩ እንዲሁም የህክምና ባለሙያዎችም ችግራቸውን ሊረዱላቸው እንዳልቻሉ ተገልጿል።

የሀገሪቱ ጤና ሚኒስቴር በእነዚህ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ላይ ያለውን የስነ-ልቦና ውጥረት በመገንዘብ በቅርቡ የተወሰኑ ትውልደ ኢትዮጵያውያን አይሁዶችን በማሰልጠን በዚህ ውጥረት ውስጥ ባሉ ማህበረሰብ ላይ እንዲሰሩ እንደሚያደርግ ገልጿል። እነዚህ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚሰለጥኑ ትውልደ ኢትዮጵያውያን አይሁዶች ማህበረሰቡን የመቀየር ሥራ ይሰራሉ ተብሎ ታስቧል። በዘመቻ ሙሴ ወቅት በሱዳን አድርገው ወደእየሩሳሌም ከገቡ ኢትዮጵያዊያን አይሁዶች መካከል አራት ሺ ያህሉቹም መሞታቸውንም ዘገባው አስታውሷል።

# ከአዲስ አበባ ህገወጥ የጎዳና ንግድ በስተጀርባ ግለሰቦች ተሳታፊ መሆናቸው ተገለፀ

*• ሕጋዊ ነጋዴዎች ከጨዋታ ውጭ እየሆኑ ነው*



በፀጋው መሳኩ

ከተወሰኑ ጊዜያት ወዲህ አዲስ አበባ በከፍተኛ ህገወጥ የጎዳና ላይ ንግድ የተጥለቀለቀች ሲሆን ከዚህ ንግድ ጀርባ ጠንካራ የገንዘብ አቅም ያላቸው ግለሰቦች መኖራቸውን መረጃዎች እያመለከቱ ነው:: በመዲናዋ ዋና ዋና መንገዶች በተለይም በሜክሲኮ፣ በቄራ፣ በመገናኛ፣ በፒያሳ፣ በአራት ኪሎ፣ በሳሪስና በመሳሰሉት አካባቢዎች በከፍተኛ ደረጃ የጎዳና ላይ ንግድ እየተባባሰ ሄዷል::

በዚህ ንግድ ልባሽና አዳዲስ አልባሳት፣ ሻንጣዎች፣ የሴት ቦርሳዎች፣መጫሚያዎች፣ የቤት እቃዋዎች የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችና ሌሎችም በርካታ እቃዎች ይሸጣሉ:: ቀደም ባሉት ጊዜያት በከተማዋ አስተዳደር በኩል አልፎ አልፎም ቢሆን ጥብቅ ቁጥጥሮች ይደረጉ የነበረ ሲሆን ከተወሰኑ ጊዜያት ወዲህ ግን ቁጥጥሩም ላልቷል፤ የጎዳና ላይ ንግዱም ከምንጊዜውም በላይ በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል:: የመንገድ ላይ ንግዱ በዚህ ደረጃ እንዲስፋፋ የንግድ እቃዎቹን በማቅረቡ ረገድ አሰራሩ ምን እንደሚመስል ለማጣራት ባደረግነው ሙከራ ከዚህ ጀርባ ጠንካራ የገንዘብ አቅም ያላቸው አካላት የሚሳተፉ መሆኑን በጎዳና ላይ ንግዱ ከሚሳተፉ ግለሰቦች ገለፃ መረዳት ችለናል:: በዚሁ ሥራ ውስጥ ካሉት ሰዎች ገለፃ መረዳት እንደቻልነው ልብሶቹም ሆነ ሌሎቹ ቁሳቁሶች ወደ ከተማው የሚሰራጩት በከተማዋ በተለያዩ ቦታዎች ከሚገኙ ትልልቅ መጋዘኖች ነው:: እነዚህ መጋዘኖች መርካቶ፣ መሳለሚያ፣ ኮልፌና ቄራ አካባቢ እንደሚገኙ የጠየቅናቸው የጎዳና ላይ ነጋዴዎች ገልፀውልናል:: በዚሁ ንግድ ሥራ የተሰማሩት የጎዳና ላይ ነጋዴዎች በአከፋፋዮቹ በኩል በቂ እምነት እስኪጣልባቸው ድረስ የንግድ እቃዎቹን በቀጥታ ከማግኘት ይልቅ በሌሎች ግለሰቦች በኩል በተዋረድ እንዲያገኙ የሚደረግ ሲሆን ነጋዴዎቹ በሂደት አቅማቸው እየተጠናከረና መተማመኑም እያደገ ሲሄድ ግን በቀጥታ ምርቶቹን ከመጋዘን ለመውሰድ እድሉ እንደሚመቻችላቸው በዚሁ ሥራ ከተሰማሩት ግለሰቦች ገለፃ መረዳት ችለናል:: ከመጋዘኖቹ እቃ አውጥቶ ለነጋዴዎቹ የማከፋፈሉ ሥራ ከጠዋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ጀምሮ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ብቻ የሚከናወን ሲሆን፤ የጎዳና ላይ ነጋዴዎቹ ደግሞ የሽያጭ ሥራቸውን የሚያከናውኑት የአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት የደንብ ማስከበር ሰራተኞች ስራቸውን ካጠናቀቁበት ሰዓት በኋላ ነው::

ህገወጥ ንግዱን በተመለከተ በህጋዊ መንገድ የሚሰሩ የአልባሳት ነጋዴዎች ንግዱ በሥራቸው ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖን እያሳደረ መሆኑን ነው የገለፁልን:: በሜክሲኮ ቡናና ሻይ ፊት ለፊት በሚገኝ አንድ ቡቲክ በስራ ላይ ያገኘነው ወጣት አብዱልለጢፍ ኡመር የጎዳና ላይ ነጋዴዎቹ በሳልቫጅ ስም ይነግዱ እንጂ የሚይዟቸው አልባሳትና መጫሚያዎች እነሱ በህጋዊ መንገድ ከገዟቸው ቁሶች ጋር አንድ አይነት መሆናቸውን ነው የገለፀልን:: ሆኖም እነሱ የቤት ኪራይ እንደዚሁም የመንግስት ግብር እየከፈሉ ማትረፍ ስላለባቸው ከወጪ ቀሪ አስልተው የመሸጪያ ዋጋን ቢተምኑም ከዚያው ከሱቃቸው ፊት ለፊት ጎዳና ላይ ተመሳሳይ እቃ በመቶና በመቶ ሀምሳ ብር ልዩነት የሚሸጥ መሆኑን ነው የገለፀልን:: በዚሁ ዙሪያ ያነጋገርናቸው ሌሎች የቡቲክ ቤት ነጋዴዎችም መንግስት ህጋዊ ከለላ እንዲያደርግላቸው ነው የጠየቁት::


በዚሁ ዙሪያ ማብራሪያ የሰጡን በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የትምህርትና ኮሙኑኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ኤፍሬም መኮንን ህገወጥ አልባሳትን በተመለከተ በሁለት አይነት መልኩ ሀገር ውስጥ የሚገቡ መሆኑን ገልፀውልናል:: በአንድ መልኩ ልባሽ ጨርቆች ሲሆኑ በህጋዊ መልኩ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ስለማይፈቀድ አንዳንድ ውጪ ቆይተው ሀገር ውስጥ የሚገቡ ግለሰቦች የእለት መጠቀሚያቸው እንደሆነ በመግለፅ አልባሳትን በማስገባት ወደገበያ የሚያወጡ እንዳሉ ገልፀውልናል:: ለችግሩ መፍትሄ ለመስጠት ከውጪ ልባሽ ጨርቅ እንዳይላክ ሰርኩላር ተበትኖ ወደተግባር የተገባበት ሁኔታ መኖሩም አቶ ኤፍሬም ጨምረው ገልፀውልናል:: ከዚህ ውጪ ኮንትሮባንድ ልባሽ ጨርቆች ሲያዙ ህብረተሰቡ ውስጥ እንዲሰራጩ የሚደረግ ሳይሆን ተቃጥለው እንደሚወገዱ ነው፤ ኃላፊው የገለፁት:: በሌላ መልኩ አዳዲስ አልባሳት በኮንትሮባንድ መልኩ ሀገር ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ መኖሩን የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተሩ ገልፀው፤ እነዚህ አልባሳት በሚያዙበት ወቅት ተወርሰው ለጂንአድ እንደዚሁም አዲስ ፋና ለሚባል የንግድ ድርጅት የሚተላለፉ መሆኑን ገልፀውልናል::

> ***በተጠቀሱት ወራት ግምታቸው 197 ነጥብ 16 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ የተለያዩ እቃዎች ሀገር ውስጥ ሲገቡ ሲሉ ተይዘዋል***

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሁለት ሺ ሰባት የስድስት ወራት አፈፃፀም እንደሚያሳየው ከሆነ፤ በተጠቀሱት ወራት ግምታቸው 197 ነጥብ 16 ሚሊዮን ብር የሚያወጡ የተለያዩ እቃዎች ሀገር ውስጥ ሊገቡ ሲሉ ተይዘዋል:: በዚሁ ግማሽ በጀት ዓመት የተያዘው የእቃ መጠን ካለፈው ተመሳሳይ ወቅት አንፃር ሲታዩ በብር 4 ነጥብ 22 ሚሊዮን ያነሰ መሆኑን የባለስልጣን መስሪያቤቱ የግማሽ አመት ሪፖርት ያመለክታል:: በዚሁ አመት አጋማሽ ድረስ የተያዙት ንብረቶች በአይነት ሲታዩ አዳዲስና አሮጌ አልባሳት እንደዚሁም የኤሌክትሮኒክስ ምርቶች ሰፊውን ድርሻ እንደሚይዙ ሪፖርቱ ያመለክታል::

በዚህ ዙሪያ ያነጋገርናቸው በአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር አገልግሎት ፅህፈት ቤት ምክትል ስራ አስኪያጅ ኮማንደር ተሰማ ነጋሽ ፅህፈት ቤታቸው በደንብ ቁጥር 14/ 2005 በተሰጠው ስልጣንና ሀላፊነት መሰረት እየሰራ መሆኑን ገልፀውልናል:: ደንቡ ህገወጥ የጎዳና ላይ ንግድን ይከላከላል ተብሎ የወጣ መሆኑን የገለፁት ኃላፊው፤ አልባሰትን በተመለከተ ልባሽ ጨርቆች ይባሉ እንጂ ህጋዊ ንግድ ፈቃድ ያላቸው ነጋዴዎች የሚይዩዟቸው እቃዎች ሳይቀሩ በጎዳና ላይ ህገ ወጥ ነጋዴዎች እጅ ተይዘው የሚታዩ መሆኑን ጨምረው ገልፀውልናል:: ደንቡ የወጣው ለህጋዊ ነጋዴዎችም ጭምር ከለላ ለማድረግ መሆኑን የገለፁት ኃላፊው፤ ህገወጥ የጎዳና ላይ ንግዱ በተለይ ከባቡሩ ሥራ መጀመር ጋር በተያያዘ ከፍተኛ እክልን ስለሚፈጥር ከወዲሁ መልክ ለማስያዝ እንቅስቃሴዎች እየተጀመሩ መሆኑን አመልክተዋል:: አሁን በከተማዋ ካለው ህገወጥ የጎዳና ላይ ንግድ አኳያ በጎዳና ላይ የሚሸጡት እቃዎች ሲታዩ ከዚህ ጀርባ ጠንካራ የገንዘብ አቅም አላቸው የሚባሉ ህገወጥ ግለሰቦች ይኖራሉ ተብሎ የሚያስጠረጥር መሆኑንም ኮማንደር ተሰማ ገልፀውልናል::■

# የተቀናቃኝ ፓርቲዎች ጠንካራ ፉክክር፤ ለገዢ ፓርቲ ህልውና ያላቸው ፋይዳ



በሳምሶን ደሳለኝ

አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በምርጫ 2007 ዓ.ም በሚደረገው ሀገራዊ ምርጫ ከፍተኛ ፉክክር ይዳረጋል ብሎ ለመገመት አስቸገሪ ሁኔታዎች ናቸው ያሉት። በተለይ በተፎካካሪ ፓርቲዎች በኩል ያለው ዝግጅት በጠንካራ መሰረት ላይ የቆመ አድርጎ ለመቀበል አደጋች ነው። ይህም ሲባል ተፎካካሪ ፓርቲዎች በመደበኛ ስራነት ፖለቲካን እየሰሩ ባለመሆናቸው እና ትንሽም ብትሆን የደከሙብትን የፖለቲካ ስራዎች በፖለቲካ ሴራ እያጠፉት፣ ሃይላቸውን እየቀነሱ፣ እየደከሙና የኃይል መሰረታቸው የሆነው ህዝባቸው ተስፋ እየቆረጠባቸው ያለበት የፖለቲካ ሂደት ይስተዋላል።

በተፎካካሪ ፓርቲዎች ውስጥ ለሚፈጠሩ የፖለቲካ ሴራዎች ብዙ ምክንያቶች ሲቀርቡ ይሰማል። ከሚጠቀሱት መካካል፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው ያለው የፖለቲካ ባሕል፣ የገገዡው ፓርቲ ተፅዕኖ፣ በፓርቲያቸው ውስጥ በግልና በቡድን የፖለቲካ ስልጣን የመያዝ ራሮት፣ የዲያስፖራው ቅጥ ያጣ የአዛዥነት ሚና፣ ግልፅ የመደብ ውክልና አለመያዝ፣ መዋቅራዊ አደረጃጀቶችን አለመፍጠር፣ ገዢውን ፓርቲ ባለው የፖለቲካ ቁመና አለመተንተን እንዲሁም የገዢውን ፓርቲ አቅም ዕውቅና በመስጠት ተመጣጣኝ የሃይል አሰላለፍ ከመዘርጋት ይልቅ አቅሙን መካድ፣ ለሚከሰቱባቸው አስተዳደራዊና ሕጋዊ ውሳኔዎች ፈጣን እና ተገቢ ምላሽ አለመስጠት እና ሌሎች ምክንያቶችንም መጥቀስ ይቻላል።

የሆኖ ሆኖ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ከሀገራዊ ምርጫ ተወዳዳሪነት ተገቢውን ተሳትፎ ባይኖራቸው ወይም ሙሉ ለሙሉ እየከሰሙ ከምርጫ ውድድሮች ቢወጡ፣ ገገዡው ፓርቲ የሚያጣው ነገር ምን ይሆን? ወይንስ ገገዡው ፓርቲ ከልካይ የሌለው የፖለቲካ ግልቢያ የሚያደርግበት ሜዳ ያገኝ ይሆን? ወይንስ ተፎካካሪ ፓርቲዎች በሌሉበት ገገዡው ፓርቲ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችልበት የራሱ የፓርቲው ትንታኔ ይኖረው ይሆን? በሚሉ መልክ ብዙ መጠይቆች በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ሊሰጡ የሚችሉ ትንታኔዎች ቢቀርቡም ተፎካካሪ ፓርቲዎች መኖራቸው ለገዢው ፓርቲ በሶስተኛ ወገን የአምክኒዮ ከሚያስገኝለት የቅቡልና ጥያቄ በዘለለ ለህልውና ቀጣይነት ያላቸው ሚና እና ፋይዳ ቀላል የሚባል አይደለም።

ምንአልባት በተፎካካሪ ፓርቲዎች መኖር አለመኖር የገገዡው ፓርቲ ህልውና እንዴት ይለካል የሚል መከራከሪያ የሚያነሱ ባለድርሻ አካለት ይኖራሉ። መኖራቸውም የሚጠበቅ ነው። ዋናው አስታራቂ ግን የሚነሱት መከራከሪያ ነጥቦች ናቸው። ስለዚህም ተፎካካሪ ፓርቲዎች እንዴት ለገገዡው ፓርቲ የህልውና መሰረቶች ሊሆኑ ይችላሉ?

አንዱን የመከራከሪያ ነጥብ ከምሳሌ ጋር አያይዘን እናንሳው። ይሄውም እ.ኤ.አ. 1978 በቻይና ታይናሚን አደባባይ በቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ በግፍ የረገፉ ወጣቶችን ታሪክ መለስ ብለን እንመልከተው። በወቅቱ እነዚያ በግፍ የረገፉት የቻይና ወጣቶች "የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ ግልፅነት የሌለው አሰራር በመከተሉ በሙስና በስብሷል። ስራአጥነት ንሯል፣ ለውጥ እንሻለን፣ ዴሞክራሲ እንሻለን" የሚል ግልፅ መፈክር አንግበው ነበር፤ በታይናሚን አደባባይ የተሰለፉት። እነዚያ ወጣቶች በግፍ በቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ በአደባባይ ላይ ቢረግፉም፣ ያነሷቸው ጥያቄዎች ግን ምላሽ የሚሹ ከዚህም በላይ የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ ህልውና የሚቀጥለው የወጣቶቹን ጥያቄ የራሱ አድርጎ መታጠቅ ሲችል ብቻ መሆኑን አንቅተውታል።

የእነዚያ የቻይና ወጣቶች ጥያቄን የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ የራሱ አድርጎ ለመታጠቅ ያባከናቸው ጊዜያት አልነበሩም። ወጣቶችን በሃይል ኮሚኒስት ፓርቲው ቢያንበረክካቸውም፣ ጥያቄያቸው ግን የፓርቲውን ህልውና የታደጉ ስለመሆናቸው የዛሬዋ ቻይና ምስክር ነች። ኮሚኒስት ፓርቲው በ1978 በቻይና ታይናሚን ስኩዌር ወጣቶቹን በግፍ አርግፎ ወደሌላ የፀረ-ሙስና ትግል ዘመቻ ውስጥ ነበር የገባው። ምህረት አልባው የፀረ-ሙስናው ትግል እገሌን ከእገሌ ሳይመርጥ ከከፍተኛ አመራሮች ጀምሮ እስከ በታች ሹማምንቶች ድረስ በሞትና በእስር የቀጣቸው የኮሚኒስት ፓርቲ አባላት ቁጥር የትየሌሌ ነው።

በአሁን ሰዓትም ኮሚኒስት ፓርቲው በአዲስ መልክ የፀረ ሙስና ትግሉን እያፋፋመ ከዚህም በላይ እርቆ በመሄድ ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶችና ተቋማት እንዲሁም መንግስታት አብረውት እንዲሰለፉ በይፋ ጥሪ አቅርቧል። ወደ ውጭ ሀገራት የኮበለሉ ሙሰኞችንም የማሳደድ ዘመቻውን አጠንክሮ ኮሚኒስት ፓርቲው ቀጥሏል። በዚህ ሁሉ እልህ አስጨራሽ የፀረ-ሙስና ትግል ውስጥ፣ አሁንም ሙስና የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲና የቻይና መንግስት መገለጫዎች ናቸው። ይሄውም ሆነ እድሜ ለፈጣን የቻይና ኢኮኖሚ እድገት ምስጋና ይግባውና ሙሰኞቹ ኮሚኒስት ፓርቲውን እስካሁን ጠልፈው ሊጥሉት አልቻሉም። የደቀኑት አደጋዎች ግን ቀላል የሚባሉ አይደለም። የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ ባስመዘገበው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ያገኘውን ቅቡልነት (performance legitimacy) ወደ ቁልቁል እየወረወሩት ይገኛሉ።

ከዚህ አንፃር የመጀመሪያ የመከራከሪያው ነጥብ ተፎካካሪ ፓርቲዎች በአንድ ሀገር ውስጥ መኖራቸው፣ አንድን ገገዡ ፓርቲ በሙስና ከመበስበስ አደጋ ይታደጉታል። ይህም ሲባል፣ ፓርቲው በሙስና አደጋ በስብሶና ተጠልፎ የፖለቲካ ስልጣኑን ከማጣቱ በፊት በፓርቲው ውስጥ ያሉ ጓዶች ውስጣዊ የፀረ-ሙስና ትግል በማፋፋም ሙሰኞችን የመልቀም ከፍተኛ ስራዎች ይሰራሉ። ሙሰኞችን ከመልቀም ጎን ለጎን፣ በኪራይ ሰብሳቢ ፖለቲካ ኢኮኖሚ የሚገኝን ንዋይን የሚጸየፉ አዳዲስ አመራሮችን የመተካት ስራዎችንም ያከናውናሉ። ይህ የሚሆነው ግን ፓርቲው በሙስና በመበስበሱ የፖለቲካ ስልጣን እንደሚያጣ ግልፅና ቅርብ አደጋ መኖሩ ሲረጋገጥ ብቻ ናቸው።

እነዚህ ሁኔታዎች እስካልተሟሉ ድረስ፣ እውነተኛ የፀረ-ሙስና ትግል በአንድ ገገዡ ፓርቲ ውስጥ አይካሄድም። በህዝቦች የምጣኔና የማህበራዊ ፍትህ በማጣት ዋጋ፣ የሚታገሳቸው ወይም በማስተማሪያነት ብቻ የሚመርጣቸውን ሙሰኞችን ለፍርድ የማቅረብ ስራዎች ላይ ማተኮርን ይመርጣል። ይህ ማለት ገገዡ ፓርቲ ሙስናን መደራደር ይጀምራል። ሆኖም በፓርቲው ውስጥ የመበስበስ አደጋዎች እየጨመሩ ሲሄዱ፣ ብስባሹም በተራዘመ ቁጥር የገገዡው ፓርቲ ህልውና ተፎካካሪ ፓርቲዎች አደጋ ባይሆኑ እንኳን በማሕበራዊ አብዮት መቀጠፉ፣ መበላቱ አይቀሬ ነው።

ሌላው የተፎካካሪ ፓርቲዎች አለመኖር በገገዡው ፓርቲ ውስጥ ንዑስ ከበርቴዎች በቀላሉ ቢሮክራሲውን የመቆጣጠር እና የኔትዎርክ መንግስት የመመስረት እድላቸው ሰፊ ነው። የኔትዎርክ መንግስት ሲባል፣ አሳታፊ ቢሮክራሲዎችንና የሕዝብን የመወሰን መሰረቶችን እየናደ፣ የአሰራር ቢሮክራሲውን በሚደግፉ አካላቶች ቢሮክራሲውን እያዋቀረ፣ እየሰየመ፣ የመወሰኛ መዋቅሮችንና ፈጻሚዎችን በቁጥጥሩ ስር በማዋል የሚፈጠር የመንግስት ባህሪ ነው። ማንኛውንም አይነት የውሳኔ ሃሳብና አፈፃፀም ከአሳታፊ ቢሮክራሲ ወይም ሕዝባዊ መሰረት ካለው የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት የሚነሳ ሳይሆን፣ ▶

በተዘረጋው የኔትዎርክ መስመር (የቢሮክራሲ መረብ) የሚቀርብና የሚፈጸም ብቻ ነው:: ይህም በመሆኑ፣ በገዢው ፓርቲ ውስጥ ሕዝባዊ መሰረት ያላቸው ጥያቄዎች ሆኑ አሰራሮች የማይስተናገዱበትና ስርነቀል የለውጥ ጥያቄዎችም ቦታ የማይኖራቸው አሰራር መፈጠሩ አይቀሬ ነው:: ይህን ከላይ ወደታች የሚዘረጋ የቢሮክራሲ መረብ አደጋ ከመሆኑ በፊት መከላከል የሚቻልበት ብቸኛ አማራጭ፣ ገዢው ፓርቲ አሳታፊ ቢሮክራሲዎችንና የሕዝብን የመወሰን መሰረቶችን እየናደ መቀጠል እንደማይችል የፖለቲካ ስልጣኑንም በተፎካካሪ ፓርቲዎች ሊያጣ እንደሚችል ግልፅና ቅርብ አደጋ መደቀኑን የሚያሳይ ማሕበራዊ መሰረት መኖሩን ሲያውቅ ብቻ ነው:: ከዚህ ውጪ የሚዘረጋው የቢሮክራሲው መረብ ሕዝባዊ መሰረቱን እያሳጣው ተፎካካሪ ፓርቲዎች ግልፅና ቅርብ አደጋ ባይሆኑበት እንኳን በማሕበራዊ አብዮት መቀጠፉ፣ መበላቱ አይቀሬ ነው:: ፈረንጆቹም እንደሚሉት፣ "ቆብ የሌለው ምስማር ወደ ጠረጴዛ ውስጥ መተህ ብታስገባው መልሰህ አታወጣውም::"

ሌላው አንድ ገዢ ፓርቲ ሙሉ ለሙሉ የመንግስት ስልጣንን ሲቆጣጠር የህዝብ እና የፓርቲ ጥቅም መስመሩን የመሳት አደጋዎች ያጋጥሙታል:: ዋነኛው አደጋ አንድ ገዢ ፓርቲ ራሱን ብቸኛ የፖለቲካ አካል አድርጎ መመልከት ሲጀምር፣ የህዝብና የፓርቲ ጥቅምን የመለየት ወይም የመደባለቅ ወይም ለፓርቲው ጥቅም ቅድሚያ የመስጠት ሁኔታዎች ያጋጥሙታል:: ይህ ማለት ለፓርቲው፣ ለፓርቲ ድርጅቶች፣ ለፓርቲ አባሎች፣ እንዲሁም ከፓርቲው ጋር ተያያዥ ለሆኑ አካሎች ቅድሚያ የሚሰጡ አሰራሮችን መዘርጋት ያካትታል:: ይህን መሰል አሰራር በባህሪው ከፓርቲ ውጪ ያሉ የህዝብ ቅሬታዎችን ያስነሳል:: ለዚህ አይነት የህዝብ ቅሬታዎች የሚሰጡት ምላሾች በአብዛኛዎቹ፣ ለገዢው ፓርቲ ስራዎች ቅድሚያ መስጠት፤ ለሕዝብ ጥቅም ቅድሚያ መስጠት መሆኑን አድርገው የሚገነዘቡ አመራሮች መከማቸት ነው:: በአንዳንድ የገዢው ፓርቲ አባላት ይህን አይነት ምላሽ ሲቀርቡ ከቀና ልቦና የሚመነጩ ቢመስሉም፣ አስተሳሰቡ ግን መሰረታዊ የመደብ ውክልና "በእኔ እጅ" ነው ከማለት የሚመነጭ በሂደት መወገድ ያለበት ነቀርሳ ነው:: በየትኛውም ሀገር የሚገኝ ገዢ ፓርቲ የማይክደው ጥሬ ሃቅ ቢኖር፣ የሕዝቦችን ውክልና ሙሉ ለሙሉ ማግኘት አለመቻሉን ነው:: ማግኘት የሚቻለው ውክልና የአብዛኛውን ሕዝብ ውክልናን ብቻ ነው::

ለምሳሌ አንድ ገዢ ፓርቲ አብላጫ የህዝብ ድምጽ አግኝቶ ስርዓተ መንግስት ሲመሰርት የሚያስተዳድራቸው ሕዝቦች የመረጡትና ያልመረጡትን በጋራ መሆኑ ይታወቃል:: ይህ ማለት ስርዓተ መንግስት የሚመሰርተው ፓርቲ ሁሉንም መደቦች በእኩል የማስተዳደር ሕገመንግስታዊ ግዴታ አለበት:: ይህ አይነት አስተዳደራዊ ስርዓት የህዝብ እና የፓርቲ ጥቅም በመደባለቅ ከሚከሰቱ አደጋዎች ለመከላከል ያስችላል:: ከዚህ አግባብ ውጪ አስተዳደሩን የሚዘረጋ ስርዓተ መንግስት፣ ጠያቂ ሊኖረው ይገባል:: መጠይቆቹም ስርዓት ባለው መንገድ እንዲቀርቡና ምላሽ እንዲሰጣቸው ከተፈለገ፣ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ለማይሰጥ ስርዓተ መንግስት ሊከፍል የሚችለው ግልፅና ቅርብ ፖለቲካዊ ዋጋ መኖሩን እንዲገነዘብ ማድረግ ምትክ አልባ እርምጃ ነው:: እስካሁን ያለው ተሞክሮ የሚያሳየው ጠንካራ መሰረት ያላቸው ተፎካካሪ ፓርቲዎችን ሲበዙ ነው:: ከዚህ ውጪ ዜጎች በአንድ ፓርቲ ውስጥ መሰለፍ አለመሰለፍ በራሱ የምጣኔ ሃብት ወይም የማሕበራዊ ፍትህ ከማግኘት እና ከማጣት ጋር አስተሳስረው መመልከት ከጀመሩ ስርዓተ መንግስት የዘረጋው ፓርቲ በማሕበራዊ አብዮት መቀጠፉ፣ መበላቱ አይቀሬ ነው::■

# ለሦስተኛ ወገን የሚተላለፉ...



የጥናቱን ውጤት ተከትሎ የሚመጣውን የአሠራር ለውጥና ማስተካከያ ሳይጠብቁ በሀገረ ስብከቱ አስተዳደር አፋጣኝ መመሪያ ሊሰጣቸው ይገባል ከተባሉት አድባራት መካከል የቦሌ ቡልቡላ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አንዱ ነው:: ሕዝበ ክርስቲያኑ በሚሳለምበት የደብሩ ዋና መግቢያ በር ግራና ቀኝ፣ የቢራ ማከፋፈያና የሴቶች የውበት ሳሎን ተከፍተው የተከራዩ ሲኾኑ ተከራዩ ደግሞ ለሦስተኛ ወገን በከፍተኛ ጥቅም አከራይቷቸዋል:: ይህም ከቤተ ክርስቲያኒቱ አስተምህሮና ቀኖና አንጻር የማይደገፍና እምነቱን የሚያስተች ከመኾኑም በላይ ምእመናኑን ለቁጣ እንዳነሣሣው ተገልጧል::

የሱቆቹ ውሎች ተቋርጦ ቦታው ነጻ ይደረግ ዘንድ መመሪያ እንዲሰጥ የጠየቀው ኮሚቴው፣ የደብሩ ባዶ ቦታዎችም ሕጋዊ ባልኾነ አግባብ ሊከራዩ የሚችልበት ዕድል እንደሚኖር በማሳሰብ ጥናቱ እስኪጠናቀቅና ተለዋጭ መመሪያ እስከሚሰጥ ድረስ ደብሩ በይዞታው ውስጥ የሚገኙ የንግድ ቦታዎችንና ሱቆችን እንዳያከራይ ጥብቅ መመሪያ እንዲተላለፍለት አመልክቷል::

ደብሩ ለመካነ መቃብር አገልግሎት የተሰጠው ቦታ ተቆራርሶ ለሌሎች አገልግሎቶች የተከራየ ሲኾን ይህም ‹‹ያለጨረታ፣ በጣም አሳዛኝ በኾነ ዋጋ›› መፈጸሙን ኮሚቴው በጥናቱ አጣርቷል:: ቦታው ከአገልግሎቱ ውጭ ለሌላ ዓላማ መዋሉ ይዞታውን እንደሚያጣብበና በመንግሥት ሊያስነጥቅ እንደሚችል የጠቆመው ኮሚቴው፣ ተከራዮች እንዲለቁና ቦታው በተገቢ መንገድ ጥቅም ላይ ይውል ዘንድ ጥብቅ መመሪያ እንዲተላለፍ አሳስቧል::

በቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን 17 ሱቆች በብር 1500 ለአንዲት ግለሰብ የተከራየ ሲኾን ግለሰቧም ለሌሎች በማከራየት በወር ከብር 30,000 በላይ በማግኘት እንደሚጠቀሙ ተገልጧል:: የደብሩ አስተዳደር ኹኔታውን በመቃወም ውላቸው እንዲቋረጥ ለማድረግ በክሥ ላይ የሚገኝ ቢኾንም ሀገረ ስብከቱ ውሉ እንዲታደስ የሚያስገድድ ደብዳቤ ለደብሩ በመጻፉ ለውዝግብ መንሥኤ መኾኑ የኮሚቴው ጽሑፍ ያስረዳል:: በመካኒሳ ደብረ ገነት ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል ለኪራይ ከዋሉት 55 ሱቆች ውስጥ 50ዎቹ ለሦስተኛ ወገን የተከራዩ(ቁልፋቸው የተሸጡ) መኾኑን የደብሩ የአስተዳደር ሓላፊዎችና የሰበካ ጉባኤ አባላት ባሉበት መረጋገጡ ታውቋል::

በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የፓትርያርኩ ረዳት ሊቀ ጳጳስ ለጥናቱ የሚያደርጉት ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚደነቅና የሚመሰገን ነው ብሏል - ኮሚቴው:: ይኹንና የሀገረ ስብከቱ አስተዳደር በመሬትና በንግድ ተቋማት ዙሪያ ለአድባራቱ የተላለፈውን መመሪያ የሚጥሱ ደብዳቤዎች በመጻፍ ተግዳሮት እየፈጠረ እንዳለ አስታውቋል:: በመኾኑም አስተዳደሩ ዕንቅፋትና ውዝግብ ከሚፈጥሩ መሰል ተግባራቱ እንዲታቀብና ጥናቱን ከመደገፍና ከማስተባበር አኳያ ተገቢውን ትእዛዝ ለአድባራቱ እንዲያስተላልፍ በጠቅላይ ጽ/ቤቱ በኩል ጥብቅ መመሪያ እንዲሰጠው ኮሚቴው በአጽንዖት ጠይቋል::■



www.sendeknewspaper.com




# አድማሱን እያሰፋ ያለው የከተማ ማደስ

## ■ቂርቆስ ክፍለ ከተማ እንደማሳያ

በፀጋው መላኩ

በአዲስ አበባ ከተማ የመልሶ ማልማት ሥራ ከተጀመረ ረዘም ያሉ ዓመታት ተቆጥረዋል፡ በመልሶ ማልማቱ ሥራ በርካታ የቆዩና ያረጁ የከተማዋ አካባቢዎች እየተነሱ የመልሶ ልማት ሥራ እየተከናወነባቸው ይገኛል። በዚህ ረገድ ቀደም ሲል በሰንጋተራና ልደታ ፍርድ ቤት አካባቢዎች በ26 ሄክታር መሬት ላይ የመልሶ ማልማት ሥራ ሲከናወን ቆይቷል። በሸራተን አዲስ ማስፋፊያ 42 ሄክታር፣ በመስቀል አደባባይ በኢሲኤ ጀርባ 3 ነጥብ 6 ሄክታር፣ በአራዳ ክፍለ ከተማ ባሻ ወልዴ ችሎት አካባቢ 25 ሄክታር ስፋት ያላቸው ያረጁ ሰፈሮችን የማንሳቱ ሥራ በስፋት ሲከናወን ቆይቷል። በርካቶቹ አካባቢዎች በመልሶ ማልማቱ ሥራ እንዲነሱ የተደረገ ሲሆን በእቅድ ተይዘው ወደ አፈፃፀም ያልተገባባቸውም አካባቢዎች ቀላል አይደሉም።

በዚህ ዙሪያ ሰፊ የመልሶ ማልማት ሥራዎች ከሚከናወንባቸው የከተማዋ ክፍለ ከተሞች መካከል አንዱ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ነው። ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ከአጠቃላይ የከተማዋ ቆዳ ስፋት 14 ነጥብ 62 ስፋትን ኪሎ ሜትር ካሬ ይዟል። ክፍለ ከተማው ከ235ሺ በላይ ነዋሪዎችንም በውስጡ አቅፎ ይዟል። ከቆዳ ስፋት አንፃር ሲታይ አነስተኛ ይሁን እንጂ በስሩ በርካታ የንግድ ተቋማት፣ አለም አቀፍ መስሪያቤቶች፣ ኢምባሲዎችና ከፍተኛ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ያካተተ የከተማዋ ክፍል ነው። እንደማሳያ ኢ.ሲ.ኤ እና የአፍሪካ ህብረት ጽህፈት ቤትን የመሰሉ ታላላቅ ክፍለ ከተሞች የሚገኙት በዚሁ ክፍለ ከተማ ነው።

ክፍለ ከተማው ከዚህ ቀደም የአፍሪካ ህብረት የተገነባበትን አካባቢ በማፅዳት የህብረቱ ጽህፈት ቤት ግንባታ እንዲካሄድ ያደረገ ሲሆን አሁንም አካባቢውን የተሻለ ገፅታ ለማላበስ ለተጨማሪ መልሶ ማልማት የልማት ተነሺዎችን በማስነሳት ላይ ይገኛል።

ከዚህም በተጨማሪ ከዚህ ቀደም ሲል በካዛንቺስ አካባቢ ያረጁ ቤቶች በመልሶ ማልማት አካባቢው እንዲፀዱ ከተደረገ በኋላ በአካባቢው በርካታ የልማት ሥስራዎች እንዲከናወኑ ሁኔታዎችን ተመቻችተው የመልሶ ማልማት ሥራው ተካሂዷል። ክፍለ ከተማው በአሁኑ ሰአትም የአካባቢውን ገፅታ በከተማዋ ማስተር ፕላን መሰረት ለመለወጥ ነዋሪዎቹን አወያይቶ ለተነሺዎች ካሳ፣ ኮንደሚኒየም ቤቶችንና የቀበሌ ቤቶችን በመስጠት አካባቢውን በማፅዳት ላይ ይገኛል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በክፍለ ከተማው



ቀደም ሲል በመልሶ ማልማቱ ስራ ፀድቶ ግንባታ የተከናወነበት ካዛንቺስ ቁጥር አንድ አካባቢ በወቅቱ በነበረው ማስተር ፕላንና ሀገሪቱ በነበረችበት የኢኮኖሚ ደረጃ መሰረት የተከናወነ ሲሆን በአሁኑ ሰአት ሀገሪቱ ባለችበት የተሻለ የኢኮኖሚ አቅምና የከተማዋ ማስተር ፕላን መሰረት ደግሞ በካዛንቺስ ቁጥር ሁለት የመልሶ ማልማት ሥራ፤ በቀጣይ የተሻሉ ሥራዎች የሚጠበቁ መሆኑን ኃላፊዋ ጨምረው አመልክተዋል።

የመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ፅህፈት ቤት ኃላፊ የሆኑትን ወይዘሮ ወይንሸት ዘሪሁንን አነጋግረናል።

ወይዘሮ ወይንሸት በልማቱ ተነሺ የሆነውን የህብረተሰብ ክፍል ከዚሁ ልማት ተጠቃሚ ለማድረግ ቅድሚያ ተሰጥቶ እየተሰራበት መሆኑን ነግረውናል። እንደ ኃላፊዋ ገለፃ፤ ነዋሪዎቹን በመልሶ ማልማቱ ሂደት ከነበሩበት ቀዬ ሲነሱ እንደየሁኔታው ነዋሪዎችን መልሶ መኖሪያ እንዲያገኙ የሚያደርግ የተጠናከረ አሰራር አለ። የልማት ተነሺዎቹ የካሳ ክፍያ፣ የማህበራዊ ቀውስ ክፍያ፣ የትራንስፖርት መጓጓዣ የሚሰጣቸው ሲሆን የግል ቤት ተነሺዎች የዓመት የቤት ኪራይም የሚታሰብላቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ምትክ ቦታም የሚሰጣቸው መሆኑም ታውቋል። የካሳ ክፍያን በተመለከተ የግንባታ ግብዓቶች የዋጋ ሁኔታ በየጊዜው እየጨመረ ስለሚሄድ ጭማሪውን ታሳቢ ባደረገ መልኩም በየአመቱ የካሳ ክፍያ ተመን ማስተካከያው የሚወጣ መሆኑን ወይዘሮ ወይንሸት ገልፀውልናል።

በንግድ ስራ የሚተዳደሩ ነጋዴዎች ከአካባቢያቸው ሲነሱ አቅሙ ካላቸው ተደራጅተው ደረጃቸውን የጠበቁ የንግድ ሱቆችን በመገንባት የሱቅ ባለቤት የሚሆኑበት እድል ያላቸው መሆኑም ተመልክቷል። ነጋዴዎቹ ፍላጎታቸው በነባር ይዞታዎች አካባቢ በሚካሄደው የመልሶ ማልማት ሥራ መሳተፍ ከሆነ የከተማውን ማስተር ፕላን ታሳቢ ባደረገ መልኩ አካባቢውን መልሰው እንዲያለሙ ይደረጋል። ሆኖም እነዚህ ነጋዴዎች መሬቱ ተሸንሽኖ ለመልሶ ግንባታ ዝግጁ እስኪሆን ድረስ የተወሰነ ጊዜ መጠበቅ የሚገባቸው መሆኑን ሃላፊዋ ገልፀውልናል።

የካሳያ ክፍያ የግምት ተመንን በተመለከተ መንግስት ያወጣው ታሪፍ ያለ ሲሆን ዋጋውን ማንም ሰው እንደፈለገ መጨመርም ሆነ መቀነስ በማይቻልበት መልኩ የተሰበሰቡት ግብዓቶች ወደ ኮምፒዩተር ገብተው ሂሳቡ ለዚሁ ስራ በተዘጋጀ ሶፍትዌር የሚሰራ መሆኑን ኃላፊዋ ጨምረው አመልክተዋል። አንድ መሀንዲስ ቤቱ ያለበት ቦታ በመገኘት በአይኑ ያየውን የቤቱን የግንባታ ግብዓትና ይዞታ (Building Material) በሚገባ ከመዘገበ በኋላ በኮምፒተር ዳታ ውስጥ ገብቶ የግምት ተመኑ እንዲወጣ የሚደረግ ይሆናል።

ከዛንቺስ ቁጥር አንድ አካባቢው በመልሶ ማልማት እንዲፀዳ ከተደረገ በኋላ ኢንተርኮንቲኔንታልን፣ ኢሊሌን፣ ራዲሰን ብሉን የመሳሰሉ ሆቴሎችና የተለያዩ ኮምፕሌክስ ህንፃ ግንባታዎች ተከናውኖበታል። ቀደም ሲል በመልሶ ማልማቱ ስራ ፀድቶ ግንባታ የተከናወነበት ካዛንቺስ ቁጥር አንድ አካባቢ በወቅቱ በነበረው ማስተር ፕላንና ሀገሪቱ በነበረችበት የኢኮኖሚ ደረጃ መሰረት የተከናወነ ሲሆን በአሁኑ ሰአት ሀገሪቱ ባለችበት የተሻለ የኢኮኖሚ አቅምና የከተማዋ ማስተር ፕላን መሰረት ደግሞ በካዛንቺስ ቁጥር ሁለት የመልሶ ማልማት ሥራ፤ በቀጣይ የተሻሉ ሥራዎች የሚጠበቁ መሆኑን ኃላፊዋ ጨምረው አመልክተዋል።

በመልሶ ማልማቱ ሂደት የመጀመሪያው ሥራ ነዋሪዎች በተገቢው መንገድ ከአካባበዊው እንዲነሱ ማድረግ ሲሆን ከዚያም ቦታውን በማፅዳት ማስተር ፕላኑ ባስቀመጠው መሰረት የመሬት ሽንሻኖው እንዲካሄድ ተደርጎ የልማቱ ሥራ የሚካሄድ መሆኑን ከሃላፊዋ ገለፃ መረዳት ችለናል። በመልሶ ማልማቱ የመሬት ሽንሻኖ ተካተው እንዲከናወኑ ከሚደረጉት ሥራዎች መካከል፤ በመሐል ከተማ መስፈር ለሚፈልጉ ተነሺዎች ቦታን መለየት፣ እንደ ገበያ ማዕከላት ሆስፒታልና ትምህርትቤት ያሉና የተለያየ ማህበራዊ አግለግሎቶችን የሚሰጡ ተቋማት ግንባታቸው የሚከናወኑባቸው ቦታዎችን መለየት ሲሆን ይህም በማስተር ፕላኑ መሰረት ወደ መሬት የሚወርድ መሆኑን ወይዘሮ ወይንሸት ጨምረው ገልፀውልናል።

ነዋሪዎችን በማንሳቱ ሂደት ቅሬታዎች ከተነሱ የሚስተናገዱበት አግባቦች የተዘጋጁ መሆኑን የገለፁልን ሃላፊዋ፤ "ቅሬታ አለኝ" የሚል ነዋሪ ቅሬታውን በፅሁፍ ማቅረብ የሚጠበቅበት ሲሆን ጉዳዩ ከተመረመረ በኋላ የሚሰጠው ምላሽም በፅሁፍ መሆኑ ታውቋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ነባር ባለይዞታ ነዋሪዎች የቦታና የቤት ባለቤት የሆኑባቸው በርካታ መንገዶች። ከእነዚህም ውስጥ ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው ነዋሪዎች

በገፅ 15




# በአነስተኛና ጥቃቅን የተጣለው መሠረት የእምቧይ ካብ እንዳይሆን . . .

- ትኩረት ለሙያ ስልጠናና ድጋፍ ማዕከላት፣
- ከስኬት ጎን ችግሮች ያልተለዩት የአነስተኛና ጥቃቅን ዘርፍ በኢትዮጵያ፣
- አነስተኛና ጥቃቅን እንዴት ተመራጭ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ይሆናል?

በበሳይ ከአዳማ

በተባበሩት መንግስታት ድህነትን በተመለከተ ባለሙያው ባለሙያ የሆነው ጆናታን ሞርዱች በማይክሮ ፋይናንስ የሚደገፈው የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ በዓለም ላይ ተመራጭና ውጤታማ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂነው ይላል። ጆናታን ለአባባሉ ማረጋገጫዎች ሲያክል፣ ዘርፉ በተወሰነ ካፒታል ለብዙ ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር ማስቻሉ፣ ለመካከለኛና ታላላቅ ኢንዱስትሪዎች ሽግግር ዋነኛ ድልድይ መሆኑ፣ እንዲሁም የሰው ሀብትን በአግባቡ ለማልማት እና ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሐገር ውስጥ በማምረት የውጭ ምንዛሪ ወጪን ማስቀሩት ተጠቃሾች ናቸው።

በተለይ በድሃ ሀገራት በመሰብሰብ ችግሮች እግር ተወርች ተጠፍንገው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ነፃነታቸውን ለማረጋገጥ ብርቅ ለሆነባቸው ሴቶች የላቀ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ውጤታማ እንደሚያደርግ በተግባር የተፈተሸ ሀቅ ነው። የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎችም ያረጋገጡት ይህንኑ እውነት ሲሆን፤ በተለያዩ ጊዜያት ባደረጉት የዳሰሰና ጥልቅ ጥናት በተመሳሳይ መጠንና አይነት ወደሥራ ከሚሰማሩ ሴቶችና ወንዶች በሴቶች ረገድ የተሻለ ውጤት ስለመገኘቱ አረጋግጠዋል። ቤተሰብን በመምራት ረገድም የሴቶቹ ድርሻ / Women head family/ ከወንድ የቤተሰብ ኃላፊ /Men head family/ ብልጫ ያለው ውጤት ተገኝቶበታል ባይ ናቸው። በመሆኑም በአነሰተኛና ጥቃቅን የኢንዱስትሪ ልማት ረገድ በዋናነት ሴቶችን ተጠቃሚ ያደረጉ ሥራዎች መተግበር ድህነትን ለመቀነስ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ቀላል አይደለም። ከዚህ በተጨማሪም ታዋቂ ሰዎች ባነሳነው ጉዳይ ዙሪያ ምስክርነታቸውን አክለዋል። ታዋቂው አቀንቃኝ ሶኒ ቦኖ እንደሚለው፤ ለወንድ ልጅ አሳ ብተሰጠው ይመገበዋል። ለሴት ልጅ ግን የአሳውን ግምት መጠነኛ ገንዘብ ብትሰጣት ራሷን ጨምሮ ባለቤቷን ልጆቿንና ዘመድ አዝማዶቿን በህይወታቸው እስካሉ ጊዜያት ድረስ ታኖራቸዋለች በሚል ሴቶች በመጠነኛ ገንዘብ ብዙ ሥራ መስራት እንደሚችሉ ይመሰክራል። የቀድሞ የእንግሊዟ ጠቅላይ ሚኒስተር ማርጋርት ታቸርም ሴቶች የተግባር ሰው ሰልመሆኗቸው በሚከተለው መልኩ ገልፃቸዋለች "ስለ አንድ የተነገረ ጉዳይ ለማወቅ ሳይሆን ስለአንድ የተከናወነ ወይም ስለተሠራ ጉዳይ ለማወቅ ሴቶችን ጠይቅ" በመሆኑም በአነስተኛና ጥቃቅን የኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ውስጥ በሚደረግ ጥረት ለሴቶች ቅድሚያና ትኩረት ሰጥቶ መሥራት የታቀደውን ግብና ዓላማ ለማሳካት ያስችላል የሚለው ደግሞ የብዙ ባለሙያዎች አስተያየት ነው።

- ከስኬት ጎን ችግሮች ያልተለዩት የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪ ዘርፍ በኢትዮጵያ፣

ሀገራችን ኢትዮጵያ የህዝቧ ቁጥር 90 ሚሊዮን መድረሱን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህ ቁጥር ውስጥ ደግሞ ከግማሽ በላይ የሚሆነው እድሜው ከ25 ዓመት በታች የሆነው ነው። ይህም ከ45 ሚሊዮን በላይ የሆነ አፍላ ጉልበት ያለው የልማት የዕድገት ሞተር የሆነ ሠራተኛ የሰው ኃይል እንዳላት ያረጋግጣል። በተለይ በእንደዚህ የእድሜ ክልል ውስጥ ያለ ህዝብ በአግባቡ የሚለማ ከሆነ የሀገሪቱ የእድገትና ብሎም የጥንካሬ ምንጭ ይሆናል። በተቃራኒው ግን ችላ የሚባል ከሆነ የማህበራዊ ቀውስ መነሻ መሆኑ አይቀርም። በእርግጥ እንደ ኢትዮጵያ ባሉት ሀገራት ውስጥ ዋነኛው የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ የሥራ ፈጠራ መሆኑ አጠያያቂ አይሆንም። ምክንያቱም ቁጥሩ ቀላል የማይባል በቀላሉ ሰልጥኖ መልማት የሚችል ርካሽ የሰው ጉልበት አለና። እናም ዋነኛው የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ በመጠነኛ ካፒታል /With limited capital/ ሰፋ ያለ የሰው ጉልበት አስተባብሮ በመጠቀም የታሰበውን ዓላማ ማሳካት ነው፡ ከዚህ አንፃር የአነስተኛና ጥቃቅን ዘርፍ ግንባር ቀደም ድርሻ የሚመጣ ተቋም ነው። በነገራችን ላይ ከሰሞኑ በሀገራችን በዚሁ ዘርፍ ሥር ተደራጅተው ውጤታማ ለሆኑ 241 ያህል አንቀሳቃሾች በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ በጠቅላይ ሚኒስተር ኃይለማርያም ደሳለኝ የማበረታቻ ሽልማት መስጠቱን ተከታትለናል። ሽልማቱን የሰጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ፤ "ዘርፉ ሀገሪቱ ወደ ኢንዱስትሪ የምታደርገውን ሽግግግር ለማፋጠን የድርሻውን እየተወጣ ነው። የዘርፉ ስኬታማነትም ከእያንዳንዱ ዜጋ ህይወት ጋር የተቆራኘ በመሆኑ የመንግሥት ድጋፍ ይቀጥላል" ብለዋል። ወደቀደመው ሃሳባችን ስንመለስ በሀገራችን የአነስተኛና ጥቃቅን ልማት ከአንድ አስርት ዓመታት የዘለለ እድሜ የለውም።

> በተባበሩት መንግሥታት እና በኢትዮጵያ መንግስት ትብብር በአዲስ አበባ ተቋቁሞ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው የሥራ ፈጣሪዎች ስልጠናና የድጋፍ ማዕከል በሌሎም እንደ ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ትግራይና ደቡብ ክልሎችም በብዛት ሲቋቋሙ እንደሚገባ ሙያዊ ምክራቸውን ይለግሳሉ

ያም ሆኖ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በከተማና በገጠር የሚገኙ ሥራ አጥ እና ሥራ ፈጣሪ ወጣቶችን በማህበር በማደራጀት ወደሥራ እንዲገቡ ተደርጓል። በዚህም በሚሊየን ለሚቆጠሩ በማህበር ለተደራጁ ወጣቶች በቢሊዮኖች የሚቆጠር ብድርና በቢሊዮኖች የሚቆጠር የገበያ ትስስር ተፈጥሯል። ጅምር ጥረቶቹ ቀላል የማይባሉ የግለሰቦችንና ቤተሰቦችን ህይወት ከመለወጥ አልፎ በሀገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ እያበረከተ የሚገኘውን አስተዋጽኦ ቀላል ባለመሆኑ ሊበረታታ የሚገባው ነው። ግና ዘርፉ ከስኬት ጎን ለጎን ችግሮች ያልተለዩት መሆኑን ደግሞ ማንሳትና የመፍትሄ ሃሳብ መጠቆም ሥራውን የተሟላ በማድረግ በሚደረገው ጥረት ውስጠት የበኩሉን ድርሻ ያበረክታል የሚል ዕምነት አለኝ። ሙሉ ብርሃኑ በሐረማያ ዩኒቨርስቲ የማህበራዊ ሳይንስና የሰብዓዊ መብት ትምህርት ክፍል እጩ ተመራቂ ናት። ለምርቃቷ ማሟያም ሴቶች በሥራ ፈጠራ ለመሰማራት መሰናክል የሚሆኑባቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው የሚለውን ርዕስ መርጣለች። የጥናት ጊዜዋ እ.ኤ.አ ከ2013 መጋቢት 2014 ባሉት ሲሆን ማዕከል ያደረጋቸው ሶስት ከተሞች ናቸው። ሐረር፣ ጅጅጋና ድሬዳዋ። በሶስቱም ከተሞች በአነስተኛና ጥቃቅን የሥራ ዘርፎች የተሰማሩ 204 ሴቶችን መርጣ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ምላሻቸውን መሠረት ያደረገ መደምደሚያ አቅርባለች። በተለይ ከ20 ሴት ሥራ ፈጣሪዎች ጋር ሰፋ ያለ ቃለምልልስ ማድረጓን በጥናት ወረቀቷ ያካተተችው። እናም በመደምደሚያዋ በዘርፉ ተሰማርተው ያሉትም ሆነ ሥራ ለመጀመር ያልቻሉት አሁንም የገበያ ትስስር በቂ አለመሆን፣ የሙያ ስልጠና እጥረት፣ የቴክኒክ ድጋፍ አናሳ መሆን ከዋና ዋናዎቹ ችግራቸው ተጠቃሾች ናቸው ብላለች።

በተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም የኢትዮጵያ ተወካይ ኢዩጂን ኦውሱ በበኩላቸው ሐገራቱ ባለ ሁለት አሀዝ ፈጣንና ተከታታይነት ያለው እድገት ማስመዝገቧን መስክረው እድገቱን ቀጣይ ለማድረግ ግን በአነስተኛና ጥቃቅን ዘርፍም ሆነ በሌሎች ሴክተሮች ለሰው ሀብት ልማት የተሰጠው ትኩረት በቂ አይደለም ይላሉ። ሀገሪቱ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በሰው ሀብት ልማት ረገድ በሰራቸው ሥራ በጥቅል ሲታይ የ32 በመቶ መሻሻል ብታሳይም አሁንም ግን ብዙ ይጠበቅበታል ብለዋል። በተለይ በአነስተኛና ጥቃቅን የስራ ዘርፍ ለሚሰማሩት ሥራ ፈጣሪዎች የስልጠናና ድጋፍ ማዕከል በብዛትና በጥራት ሊኖር ይገባል ይላሉ ሚ/ር ኢዩጂኒ። በተባበሩት መንግሥታት እና በኢትዮጵያ መንግስት ትብብር በአዲስ አበባ ተቋቁሞ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው የሥራ ፈጣሪዎች ስልጠናና የድጋፍ ማዕከል በሌሎም እንደ ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ትግራይና ደቡብ ክልሎችም በብዛት ሊቋቋሙ እንደሚገባ ሙያዊ ምክራቸውን ይለግሳሉ። በዘርፉ ሽግግር ሂደት የሰለጠነ፣ በቴክኒክና ሙያዊ ብቁ የሆነ የሰው ሃይልም አስፈላጊነቱ ግድና ግድ በመሆኑ አዜብ አሰፋ ከአዲስ አበባ የሥራ ፈጣሪዎች ማዕከል ስልጠናና ድጋፍ ያገኘች የገበያ ፈጠራ ባለቤትነት ወደሰልጠነው ማዕከል ከመግባቷ በፊት የነበሩባት የግንኙነት፣ የቴክኒካል እውቀትና ከህሎት ችግር እንደተቀረፈለት ትናገራለች። እናም እንደ እነ አዜብ አሰፋን የመሳሰሉ የፈጠራ ሰዎችን በብዛት ማፍራት የሚያስችል የሙያ ስልጠናና ድጋፍ ማዕከል ያስፈልጋል። የሙያ ስልጠናና የቴክኒክ ድጋፍ የተሻለ ትምህርት እና ልምድ በማስገኘት ሥራ ፈጣሪዎችንም ሆነ የቢዝነስ ሰዎችን ውጤታማ ውሳኔ እንዲወሰኑ ያስችላቸዋልና። ይህ ሲሆን ብቻ ነው በአነስተኛና ጥቃቅን ዘርፍ የተጣለው መስረት የእምቧይ ካብ ከመሆን የሚድነው፤ ይህ ሲሆን ብቻ ነው። ተፈጥሮአዊ ሂደቱን ጠብቆ ዘርፉ በለውጥ ጎዳና በመጓዝ የሀገሪቱንም የኢንዱስትሪ ሽግግር ለማሳለጥ የሚያስችል ነው የሚል እምነት አለኝ።

## ኪነ-ጥበብ እና ባህል



በኒውዮርክ ከተማ ነዋሪ የሆነችው ጁሊ ምሕረቱ በሥዕል ችሎታዋ አያሌ የአሜሪካንን ሽልማት ያገኘች ስትሆን ስራዎቿም በልዩ ልዩ የአሜሪካን ታላላቅ ጋላሪዎችና ሙዚየሞች ውስጥ የተቀመጡላት ናት።

# ትውልደ ኢትዮጵያዊቷ ሰዓሊት የ2015 የአሜሪካ መንግሥት ተሸላሚ ሆነች

በጥበቡ በለጠ

የአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት በዘንድሮው የ2015 ዓ.ም ከሸለማቸው ምርጥ ሰዓሊያን መካከል ትውልደ ኢትዮጵያዊቷ ሰአሊት ጁሊ ምሕረቱ አንዷ በመሆን ተሸላሚ ሆናለች።

ጁሊ ምሕረቱ ለሽልማት ያበቃት በአለማችን ውስጥ ያሉ ህዝቦችን፣ ሐገራትን በስዕል ጥበቧ ባህላቸውን እና ታሪካቸውን እያቀለመች የማቀራረብና የመግለፅ ችሎታዋ ከእለት ወደ ዕለት አስደማሚ እየሆነ በመምጣቱ እንደሆነም ተገልጿል።


ጁሊ ምህረቱ እ.ኤ.አ. በ1970 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የተወለደች ሲሆን እ.ኤ.አ. በ1977 ዓ.ም ደግሞ ወደ አሜሪካ በመጓዝ ትምህርቷም ሆነ ሥራዋ በዚህችው አሜሪካ ውስጥ ሆኗል። በግማሽ ጎኗ ከኢትዮጵያዊ ቤተሰብ የተወለደችው ይህች ሰዓሊት በአሁኑ ወቅት በአሜሪካ ውስጥ ካሉት ዘመናዊ ሰዓሊያን ተርታ ስሟ ከፍ ብሎ የሚጠራ ነው።


በኒውዮርክ ከተማ ነዋሪ የሆነችው ጁሊ ምሕረቱ በሥዕል ችሎታዋ አያሌ የአሜሪካንን ሽልማት ያገኘች ስትሆን ስራዎቿም በልዩ ልዩ የአሜሪካን ታላላቅ ጋላሪዎችና ሙዚየሞች ውስጥ የተቀመጡላት ናት።

በአሜሪካ መንግሥት ስቴት ዲፓርትመንት አማካይነት የባሕል ዲፕሎማሲን በማስፋፋት ረገድ ተጠቃሽ መሆኗ የተነገረላት ጁሊ ምህረቱ፤ በእንግሊዝና በአሜሪካ፣ በኢትዮጵያ እና በአሜሪካ ብሎም በሌሎችም ሀገራት ውስጥ ያሉ የባህል ትስስሮችን አጉልታ በማሳየት ስሟ ከፍ ብሎ ይጠራል።


የ2015 ዓ.ም የስቴት ዲፓርትመንት ተሸላሚ መሆኗም በዓለም አቀፉ ደረጃ በእጅጉ ከሚከበሩ ሰዓሊያን ተርታ የሚያስገባት መሆኑም ተነግሮላታል።

ጁሊ ምህረቱ፤ በተለያዩ ታላላቅ መድረኮች ላይ ተሸላሚ እንደሆነ የሚነገርለትን እና በዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ የአያሌ ጭቅጭቆች፣ ክሶች እና ውዝግቦች ማዕከል የሆነውን "ድፍረት" የተሰኘውን ፊልም ኤግዘኪዩቲቭ ፕሮዲዩሰር እንደሆነችም ይታወቃል።





# የኢትዮጵያ በቱሪስቶች ምርጫ ከምርጥ 10 የዓለማችን ሀገራት አንዷ ሆነች



በዓለም አቀፉ ደረጃ በአያሌ ቱሪስቶች የሚነበበው `Rough Guides` በመባል የሚታወቀው የህትመት ውጤት በቅርቡ ለአንባቢዎቹ አንድ ጥያቄ አቅርቦ ነበር:: ይህም ጥያቄ እ.ኤ.አ. በ2015 ዓ.ም ማየት የምትፈልጓቸውን አስር የዓለማችን ሀገራትን ጥቀሱ የሚል ነበር:: በዚሁ እጅግ ተነባቢ በሆነው የቱሪስቶች ጋይድ መፅሐፍ ውስጥ በተሰጠው ምላሽ ኢትዮጵያ ከተመረጡት አስር ሀገራት መካከል የሰባተኛ ደረጃን ማግኘቷን ድርጅቱ በድረ-ገፁ ባሰራጨው ዜና ይፋ አድርጓል::

ኢትዮጵያ በምርጫው ውስጥ መካተቷ እና የዚህ ሁሉ ቱሪስት የፍላጎት አቅጣጫ መሆኗ ወደፊት ሀገሪቱ ከዚሁ ዘርፍ ልትጠቀምበት የምትችልበት እድል በእጅጉ ፈክቶ እያንፀባረቀ መሆኑን አስተያየት ሰጪዎች ገልጸዋል::

በዚሁ `Rough Guides` በተሰኘው የቱሪስቶች መፅሀፍ ውስጥ አስር ምርጥ የቱሪስቶች ምርጫ የሆኑት የ2015 ዓ.ም ሀገራት ይፋ ሆነዋል:: እነዚህም የሚከተሉት ናቸው:-

1. ዩናይትድ ኪንግደም (UK)
2. ግሪክ
3. አይስ ላንድ
4. ኢንዶኔዥያ
5. ጃፓን
6. ቺሊ
7. ኢትዮጵያ
8. ቱርክ
9. ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ (USA)
10. አየርላንድ

ሆነው በቱሪስቶች ተመርጠዋል::

ኢትዮጵያ ከነዚህ አስር ሀገራት ውስጥ በቱሪስቶች ምርጫ ውስጥ መካተቷን በተመለከተም የመፅሐፉ ድረ-ገፅ ማብራሪያ ሰጥቶበታል:: እንደ ድረ-ገፁ ገለፃ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ አያሌ የቱሪዝም መስዕብ ያላት ሀገር መሆኗ ተዘግቧል:: በተለይ ደግሞ በተፈጥሮ መስዕብም ቢሆን ከታላቁ የኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ጀምሮ ልዩ ልዩ ግዙፍ ተራሮች ያሏት ሀገር በመሆኗ መልክአ ምድሯም እንድትመረጥ አስተዋፅኦ እንዳደረገ ዜናው በሚከተለው መልኩ ገልጾታል:-

From the dramatic Great Rift Valley to the lush highlands, the diversity of Ethiopia's landscapes might surprise you.

በማለት ገልጿል::

ይህን የ2015 ዓ.ም ምርጥ አስር የዓለማችን የቱሪስቶች ምርጫን ይፋ ያደረገው ድረ-ገፅ roughguides.com/best-places/2015/peoples- choice/ የሚሰኝ ሲሆን፤ ኢትዮጵያንም በተመለከተ አዲስ መፅሐፍ በቅርቡ አሳትሞ ይፋ እንደሚያደርግ ገልጿል::

# ጥበበኞቹና በጎ ተግባራቸው

የኪነ-ጥበብ ሰዎች በሕዝብ ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነትና ፍቅር መሠረት በማድረግ ለበጎ ተግባር ራሳቸውን ማሰለፍ ባደጉት ሀገራት በአብዛኛው የተለመደ ነው:: የኪነ-ጥበብ ሰዎች ለበጎ አድራጎት ተግባር አድናቂዎቻቸውን ሲጋብዙ እና የተለያዩ ጥበባዊ ሥራዎችን ሲያከናውኑ ከፍተኛ ገቢ ማሰባሰብ እና ያንን ገቢ ደግሞ ለምግባረ ሰናይ አገልግሎት ሲያውሉ ሕዝባዊና ማህበራዊ ጥሪያቸውን ኃላፊነታቸውን ተወጡ ተብሎም ይነገራል::

ማህበራዊ ኃላፊነት /Social Responsibility/ በኪነ-ጥበብ ውስጥ ጉልህ ስፍራ የሚሰጠው ነው:: ጥበበኞች ለሕዝባቸው፣ ለወገናቸው፣ ለሐገራቸው ልማት ብልፅግና እንዲሁም ርዕይ ከሁሉም ቀድመው ከፊ መሰለፍ እንደሚገባቸው ብዙዎች ያምናሉ::

በቀደመው ዘመን ኢትዮጵያ በረሀብ ስትመታ እነ ማይክል ጃክሰን፣ ቦብ ጊልዶፍና፣ እነ ሄሪ ቤላሮንቴን የመሳሰሉ ታላላቅ ጥበበኞች የጥበብ ተሰጦኦዋቸውን ሰንቀው ለሀገራችን ችግር ቀድመው የደረሱልን ነበሩ:: በዝግጅቶቻቸውም ትልቅ ገቢ አሰባስበዋል::

በሀገራችንም ቢሆን ጥበበኞች ብዙም ሳይሆን አልፎ አልፎ ሙያቸውን ለበጎ ተግባራት ሲያውሉ ይታያሉ::

ከሰሞኑ ደግሞ ኒውዮርክ ውስጥ ያሉ ወጣት ሰዓሊያን ከተለያዩ ዓለማት ተሰባስበው የተሠጣቸውን የጥበብ ፀጋ ለበጎ ተግባር አውለውታል:: እነዚህ የጥበብ ባለሙያዎች በዕድሜያቸው በጣም ወጣቶች ናቸው:: የተሰበሰቡትም ከኢትዮጵያ፣ ከካናዳ ከአሜሪካ እና ከልዩ ልዩ የአውሮፓ ከተሞች ነው::

ለዚህ ለበጎ ተግባራቸውም የሰጡት መጠሪያ Artists for Charity (AFC) ወይም ወደ አማርኛ ስንመልሰው አርቲስቶች በግብረ ሰናይ ዓላማ እንደ ማለት ነው:: በማናታን ኒውዮርክ የተሰባሰቡት እነዚህ ጥበበኞች ልዩ ልዩ ሥራዎቻቸውን በጨረታ በመሸጥ ፣ ታዳሚዎቻቸውን ደግሞ የሚግቢያ ዋጋ በማስከፈል ለበጎ ተግባር የሚል ገንዘብ አሰባስበዋል:: ገንዘቡ በHIV ኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ህፃናት እንዲሁም ደግሞ ከዚሁ ባይረስ ጋር አብረው የተወለዱ ልጆችን መደጎሚያ ብሎም ደግሞ ልጆቹ ወደፊት ለመሆን የሚፈልጉትን ነገር ህልማቸውን ማሳኪያ ይሆን ዘንድ የተቻላቸውን አድርገዋል::

እነዚሁ ወጣት የስዕል ባለሙያዎች በዩናይትድ ስቴትስ ርዕሰ ከተማ በዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ ይህን ጥበብን ለበጎ ተግባር የማዋል መርሃ ግብራቸውን ከሰሞኑ ያካሂዳሉ:: ወጣቶቹ ሰዓሊያን የሚባሰቡበት ለ8ኛ ጊዜ በሚካሔደው የጥበበኞች የበጎ ሥራ ቀን ላይ ተሳትፈው በብዙ ችግሮች ውስጥ ላሉ ህፃናት መደጎሚያ የሚሆን ገቢ ለማሰባሰብ ነው::

ከአዘጋጆቹ መካከል የሆነው ኢትዮጵያዊው ወጣት አርቲስት እንደሚናገረው ከሆነ ይህ መርሃ ግብር የሚካሔደው በጎ ፈቃደኛ በሆኑ የጥበብ ሰዎች አማካይነት ነው:: እነዚህ ሰዎች ጊዜያቸውን እና ሙያቸውን ብሎም ገንዘባቸውን ለዚህ ለተቀደሰ ዓላማ የሚያውሉ መሆናቸውን ተናግሯል::

እነዚህ በጎ ፈቃደኛ ሰዎች ከተለያዩ የጥበብ መስኮች ውስጥ የተውጣጡ ብሎም ደግሞ ከአሜሪካ፣ ከካናዳ እንዲሁም ከአውሮፓና ከአፍሪካ መምጣታቸውንም ተናግሯል::

ከበጎ ፈቃደኞቹ መካከል አንዷ የሆነችው አሜሪካዊቷ ሀና ስትናገር ልጆች ህልም አላቸው፣ አንደ ለመሆን የሚያልሙት ነገር አለ:: ውስጣቸው የሚነግራቸው ነገር አለ:: እዚያ ነገር ላይ ለመድረስ ደግሞ አጋዥ ይፈልጋሉ:: ምክንያቱም አቅም የላቸውማ:: ስለዚህ እኛ ደጅን ልንሆናቸው ይገባል የሚል ሀሳብ ሰንዝራለች::

በተለይ ከዚሁ ከHIV ቫይረስ ጋር የሚኖሩት ህፃናትም የወደፊት ህልማቸውን ሲናገሩም ተደምጠዋል::

- ሳድግ አርቲስትነት መሆን ነው የምፈልገው፣
- ሳድግ ፓይለት ነው መሆን የምፈልገው፣
- ሳድግ ደራሲ ነው መሆን የምፈልገው፣
- ዳንሰኛ ነው መሆን የምፈልገው፣
- ኢንጂነር /መሀንዲስ/ ነው መሆን የምፈልገው፣

እነዚህ ከHIV ቫይረስ ጋር የሚኖሩትን ህጻናት ጥበበኞች የትም ቦታ ቢኖሩ መረዳት እንደሚገባቸው አዘጋጆቹ ይናገራሉ:: ህፃናቱ በHIV ወላጆቻቸውን ያጡ በመሆናቸውና ከቫይረሱ ጋርም ስለሚኖሩ ክብካቤ እንደሚያስፈልጋቸው አዘጋጆቹ ወጣት አርቲስቶች ይናገራሉ::


በዚሁ በአርቲስቶች ድጋፍ ተጠቃሚ የሆኑ ታዳጊ ህፃናትም ስለ HIV ኤድስ ቫይረስም ማብራሪያ ሰጥተዋል:: እነዚህኑ ልጆች መሠረት አድርጎ በተሰራው ዶክመንተሪ ፊልም ወስጥ የሚከተለውን ብለዋል:: "ነገን ለማየት ህልም አለን:: ያንን ህልማችንን ደግሞ እውን የምናደርገው እኛም ጠንክረን እናንተም ስትወዱን ስታቀርቡን ነው" ሲሉ ተናግረዋል::

በነዚህ ወጣት አርቲስቶች የሚደገፉት ህፃናት ኑሯቸው ከቀን ወደ ቀንም እየተሻሻለ መምጣቱን ይናገራሉ::

ከአሜሪካ ሆነው ኢትዮጵያዊያን ህጻናት የሚረዱትን ወጣቶች በማስተባበር እየሰራች ያለችውና በሃያዎቹ የእድሜ አጋማሽ ላይ የምትገኘው ታታሪዋ ወጣት አበዛሽ ታምራት ነች:: በእርሷ አማካይነት የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች ከተለያዩ አለማት እየተሰባሰቡ ሙያቸውን ለበጎ ዓላማ እያዋሉት ይገኛሉ::

እንደ አበዛሽ አባባል፣ አሁን ከተለያዩ የዓለማችን ሀገራት የተውጣቱ በጎ ፈቃደኛ ሰዎች ለውጥ ማምጣት ችለዋል:: ለእነዚህ ህጻናት አጋርነታቸውን ገልጸዋል:: ወደፊትም በሌሎች ሀገራት ያሉና የእኛን ድጋፍ ለሚሹ ህፃናት በሙሉ ከጎናቸው መቆም አለብን ብላለች::

በአጠቃላይ ሲታይ፣ እነዚህ ወጣት የኢትዮጵያ አርቲስቶች ጥበብን ለበጎ ተግባር ማከናወኛ አድርገው ብዙ እየተጓዙ ነው:: ሌሎችም የእነርሱን አርአያነት ከተከተሉ ጥበብ ማህበራዊ አገልግሎቷ ሰፊ ይሆናል ተብሏል::




# አዶት ሲኒማ እና ቴአትር የጥበባት - እናት



በአሸናፊ ደምሴ

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ካሉ በጣት የሚቆጠሩ የሲኒማ አዳራሾች በይዘቱም ሆነ በዓይነቱ አንድ እርምጃ ቀደም ያለ ነው ተብሎለታል፡፡ ባሳለፍነው ቅዳሜ ጥር 30 ቀን 2007 ዓ.ም ተመርቆ አገልግሎት መስጠት የጀመረው - አዶት ሲኒማና ቴአትር፡፡ አዶትን ለየት ከሚያደርጉት የአዳራሽ ስፋቱ፣ ምቹ መቀመጫዎቹና ከዙሪያ ገብ የድምፅና የምስል ቴክኖሎጂዎቹ በተጨማሪ አዳራሹ ለፊልም ብቻ ሳይሆን ለቴአትር፣ ለስታንድአፕ ኮሜዲዎች፣ ለግጥም ምሽቶችና ለሌሎችም የኪነ-ጥበብ ሥራዎች ምቹ ሆኖ መገንባቱ ነው፡፡

አዶት ሲኒማና ቴአትር 420 መደበኛ እና 180 የልዩ ማዕረግ (VIP) በድምሩ 600 የሚደርሱ ተመልካቾችን በአንድ ጊዜ ማስተናገድ የሚችል ሲሆን፤ ከዚህም መካከል ለአካል ጉዳተኞች አመቺ የሆነ መቀመጫ ተዘጋጅቷል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በአዶት ኢንተርናሽናል ትሬዲንግና በአናቤ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ውስጥ ከ180 በላይ ለሚደርሱ ሰዎችም ቋሚ የሥራ ዕድልን መፍጠር የቻለ የመዝናኛ ስፍራ ነው፡፡ ይህም ለበርካታ የከተማዋ የኪነ-ጥበብ አፍቃሪዎች እንደ አማራጭ ሆኖ ከመቅረቡም በተጨማሪ ለኪነ-ጥበብ ባለሙያዎችም የማሳያ ስፍራን በተመለከተ ለሚገጥሟቸው ፈተናዎች እንደመደላድል ሆኖ በምርጥነቱ የሚመረጥ ያደርገዋል፡፡

አዶት ማለት በጉራግኛ ቋንቋ "እናት" ማለት ሲሆን፤ በሲኒማና ቴአትር አዳራሽም ከፊልም፣ ከቴአትር፣ ከስታንዳፕ ኮሜዲ፤ ከሙዚቃና ከግጥም ምሽቶች በተጨማሪ ልዩ ልዩ የመዝናኛ ፕሮግራሞችን ማስተናገድ መቻሉ አዶትን የኪነ-ጥበብ እናት እና መዳረሻ ያሰኘዋል፡፡ የግንባታ ሂደቱን በተመለከተ በአዳራሹ ለታደሙት እንግዶች ንግግር ያደረጉት የአዶት ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበርና የአልፈሪድና ቤተሰቡ (አናቤ) ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ባለቤትና ሥራ አስኪያጅ አቶ አልፈሪድ ከማል፤ "የንግድ ተቋማት ትርፍ ማግኘት ዋናው ዓላማቸው ቢሆንም፤ ይህን ውጤት በአጭር ጊዜ ለማሳካት ከሚያስችል መስክ በመውጣት ብዙም ባልተሰራበት ሲኒማና ቴአትር ቤት ኢንቨስትመንት ውስጥ እንድንሳተፍ ስንወስን የዛሬውን ሳይሆን የሩቁን አስበን ነው" ብለዋል፡፡ በዚህም የአዶት ሲኒማና ቴአትር መገንባት ከአማራጭ የመዝናኛ ማዕከልነቱ ባሻገር ባህልና ኪነ-ጥበብን በማስተዋወቅ እንዲሁም ለባለሙያዎች ስራዎቻቸውን የማሣያ ቦታ በመስጠት እንደ አንድ ማኅበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት መስራታቸውን አስረድተዋል፡፡

በአዶት ሲኒማና ቴአትር ደማቅ የምረቃ ፕሮግራም ላይ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሙሉጌታ ሰኢድን ጨምሮ በርካታ የመንግስት ባለስልጣናት፣ የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች፣ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶችና የመገናኛ ብዙሃን አባላት ተገኝተዋል፡፡

በ2 ሺህ 350 ካሬ ሜትር ላይ ህንፃውን የገነባው አዶት ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ፤ መሠረቱ አናቤ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ መሆኑ ሲታወስ በቤተሰቡ ጥረት እያደገና እየሰፋ የመጣ ተቋም ስለመሆኑም በምረቃ ፕሮግራሙ ወቅት ተነግሯል፡፡ አዶት ሲኒማና ቴአትር ሥራ መጀመሩ ለበርካታ ወጣቶች የመዝናኛና የባህል ማሳያ እንደሚሆን ተስፋቸውን የገለፁት የዕለቱ የክብር እንግዳ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታው አቶ ሙሉጌታ ሰኢድ፤ በትርኢት ማሣያ ስፍራዎች እጥረት ምክንያት የፈጠራ ባለሙያዎች ያላቸውን አቅም በሙሉ ተጠቅመው ጥበብን እንዳያበረክቱ የተጋረጠውን እንቅፋት (አዶትን) መሰል የመዝናኛ ስፍራዎች ሊፈቱት እንደሚችሉ ያላቸውንም ተስፋ ገልፀዋል፡፡



የአዶት ሲኒማና ቴአትር ባለቤትና ሥራ አስኪያጅ አቶ አልፈሪድ ከማል

በከተማችን ውስጥ ተገንብተው አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙት የሲኒማ አዳራሾች ቁጥር ጥቂት ነው ባይባልም አብዛኞቹ ተቋማት ግን የተለያዩ የኪነ-ጥበብ ትርኢቶችን ለማቅረብ በሚያስችል መልኩ ከመነሻው ታቅደው አለመሰራታቸው ወደአገልግሎት በሚገቡበት ወቅት የሚገጥማቸው የአቅም ውስንነት በግልፅ የሚታይ ነው የሚሉት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታው፤ "አዶት ሲኒማና ቴአትር ግን ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ታስቦበት የተሰራ በመሆኑ ለተመልካችና ለኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች የሚሰጠው እርካታ እንዳለ ሆኖ ኪነ-ጥበብንም አንድ እርከን ከፍ ያደርጋል" ብለዋል፡፡

የሲኒማና ቴአትር አዳራሽን በተሟላና ዘመናዊ መልኩ ገንብቶ ለማጠናቀቅ ከሦስት ዓመታት ያላነሰ ጊዜን እንደወሰደባቸው የተናገሩት ባለቤቱና ሥራ አስኪያጁ አቶ አልፈሪድ ከማል፤ በተለይም የህንፃ ግንባታ ቁሳቁሶች ዋጋ በየጊዜው ማሻቀብና ከውጪ ሀገር የገቡ ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች በርከት ያለ የውጪ ምንዛሬ መጠየቃቸው በቅድሚያ ተይዞ ከነበረው በጀት ከ60 በመቶ በላይ ስለማስጨመሩም አልሸሸጉም፡፡ በመሆኑም ይህን ታላላቅ የሥነ-ምህንድስና ባለሙያዎችና አማካሪ ተቋማት የተሳተፉበትን ዓይነ-ግቡ ሲኒማና ቴአትር ቤት ገንብቶ ለመጨረስ ከ180 ሚሊዮን ብር በላይ ፈሰስ መደረጉ ታውቋል፡፡ በመድረኩም ሥራው ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድጋፋቸውን ላልነፈጉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ የግል ተቋማትና ግለሰቦች የምስጋና ሽልማትና የምስክር ወረቀት ተበርክቶላቸዋል፡፡

የአዶት ሲኒማና ቴአትር አዳራሽ በተመረቀበት ዕለት የሲኒማውን የምስልና ድምፅ ደረጃ የሚያመላክት በ3ዲ መነጽር የታገዘ ፊልም ለታዳሚያኑ የቀረበ ሲሆን፤ በደራሲ ሉዋን.ጂ. ትራዴሎ የተፃፈውና በ1970ዎቹ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴአትር ጥበባት መምህራንና ተማሪዎች ተተርጉሞ በተስፋዬ ገ/ማርያም የተዘጋጀው "ሞርሳው" የተሰኘ አጭር ድራማም ለመድረክ በቅቷል፡፡ በትወናው አለማየሁ ታደሰ፣ ሽመልስ አበራ (ጆሮ)፣ መሠረት ህይወትና አዲስዘመን አደላ ናቸው፡፡ ከዚያም በመቀጠል የተመሰገን ልጆች በመባል የሚታወቁት የዳንስ ቡድን አባላት በባህላዊና ዘመናዊ ሙዚቃዎች የተቀናበሩ የውዝዋዜና የዳንስ ትርኢቶቻቸውን ለታዳሚው አቅርበው አድናቆትን አግኝተዋል፡፡

አዶት ሲኒማና ቴአትር ብስራተ ገብርኤል አካባቢ በሚገኘው አዶት መልቲፕሌክስ ህንፃ 4ኛ ፎቅ ላይ በይፋ ሥራውን የጀመረ ሲሆን፤ የከተማችን የመብራት መቆራረጥ የማያሰጋውና ለ24 ሰዓታት ያለምንም መቆራረጥ የኃይል አቅርቦት መስጠት የሚችል ዘመናዊ ጄኔሬተር ተተክሎለታል፡፡ አዶት ሲኒማና ቴአትር በተለያዩ የኪነ-ጥበብ ዘርፎች ውስጥ የሚገኙ ባለሙያዎች ጥራታቸውንና ደረጃቸውን የጠበቁ ሥራዎቻቸውን ይዘው በመምጣት ያለ አንዳች ደጅ መጥናት እና ክፍያ አንቱ በተሰኙ ባለሙያዎች አማካኝነት ሥራዎቻቸው ተገምግመው ለዕይታ መብቃት እንደሚችሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡




## አንዳንድ

በመስከረም አያሌው

# ጦርና ጎራዴን ወደ ማረሻ

ፕላውዲን የተባለው የእንግሊዝ መንግሰት ወኪል ስለአፄ ቴዎድሮስ ባሰፈረው ገለፃ፤ እንዲህ ብሏል። "ንጉስ ቴዎድሮስ በእድሜ ወጣት ናቸው። ትሁትና ደስተኛ ናቸው። የባሪያ ንግድን አጥብቀው የሚቃወሙ ናቸው። የተሸጡ ባሪያዎችን ሲያገኙ የተገዙበትን ዋጋ እየከፈሉ ባሪያዎቹን ነፃ ያወጧቸዋል። ወታደሩም በሚከፈለውና እየሰራ ከሚያገኘው ገቢ በስተቀር ከገበሬው ዘንድ እንዳይደርስ ጥብቅ ትዕዛዝ ሰጥተዋል። የአበሾችን አለባበስ እንኳ ለመለወጥ ጥረት ጀምረዋል። ግማሽ ሰውነትን ብቻ የሚሸፍነው አለባበስ ቀርቶ ሙሉ ሰውነት የሚሸፍን ልብስ እንዲለበስ አዘዋል።

በየአውራጃው ያለውን ወታደር ሁሉ በአንድ አዛዥ ስር እያደረጉ ለመፍረድና ለቅጣት ስልጣን በሌላቸው በታማኞቻቸው ስር እንዲታዘዝ አድርገዋል። ለወታደሩም ገንዘብ በመስጠት በደመወዝ እንዲተዳደር ወስነዋል። ለሹማምንትም እንደደረጃቸው ከመቶ ብር እስከ ሺህ ብር ቋሚ ክፍያ ወስነውላቸዋል። ወታደሩም ጠመንጃ እንጂ ጦርና ጐራዴ መታጠቅ እንዲያቆም ለማድረግ አስበዋል። ጦርና ጐራዴን ወደማረሻነት ለመለወጥ ይመኛሉ።

አፄ ቴዎድሮስ -የሺህ ዓመቱ
ጀግና በማርቆስ የሻነው

# ስጠቅሳባ እውቀት

አንድ ጐልማሳ ሰው በሰውነቱ ውስጥ ከሁለት እስከ ዘጠኝ ቶን ባክቴሪያ ይኖራሉ።

ከመሳሳም ይልቅ በመጨባበጥ ወቅት የሚተላለፉት ጀርሞች ቁጥር ይበልጣል።

ትንኝ 47 ያህል ጥርሶች አሏት።

በዓለማችን ላይ በመንትዮች መካከል የተመዘገበው ረጅሙ የጊዜ ልዩነት 87 ቀን ነው።

የዓለማችን እድሜ ጠገቡ ኮንደም እ.ኤ.አ በ1640ዎቹ የተሰራ ሲሆን፤ የተሰራውም ከእንስሳት እና ከዓሣ አንጀት ነበር።

እ.ኤ.አ በ2007 ኮሬይ ታይለር የተባለው አሜሪካዊ የቆጠረበትን የሞባይል ታሪፍ ላለመክፈል ብሎ እንደሞተ ቢያስነግርም እውነቱ ግን በኋላ ላይ ሊወጣ ችሏል።

ለአንድ ሰዓት ያህል የጆሮ ማዳመጫ ማድረግ በጆሮ ውስጥ ያሉትን ባክቴሪያዎች ቁጥር በ700 እጥፍ ይጨምረዋል።

ጐሪላዎች በቀን እስከ 14 ሰዓታት የሚደርሰውን በእንቅልፍ ያሳልፋሉ

የፈረስን ጾታ ጥርሱን በማየት ብቻ መለየት ይቻላል። አብዛኞቹ ወንድ ፈረሶች 40 ጥርሶች ያሏቸው ሲሆን፤ የሴቷ ደግሞ 36 ናቸው።

ሊኦናርዶ ዳቪንቺ በተመሳሳይ ወቅት በአንድ እጁ እየፃፈ በሌላው እጁ ስዕል መሳል ይችል ነበር።

የአንድ ሰው ልብ በቀን 100ሺህ ጊዜ ይመታል።

አዶልፍ ሒትለር አትክልት ተመጋቢ ነበር።

# ከኢንተርኔት ሱስ ለመላቀቅ ቻይናዊው ግራ እጁን ቆረጠ

በቻይና ናንተንግ ከተማ ጂያንግሱ ግዛት ነዋሪ የሆነው የ19 ዓመቱ ወጣት በኢንተርኔት ሱስ ከተጠመደ ሰነባብቷል። ነጋ ጠባ ማረፊያው ኢንተርኔት በመሆኑም ከዚህ ከተጠናወተው ሱስ ለመላቀቅ ዘላቂ መፍትሔ መውሰዱን ኦዲቲ ሴንትራል ሰሞኑን አስነብቧል። ይኸውም የግራ እጁን በቢላዋ መቁረጥ ነበር።

የወጣቱ እናት እንደገለፀችው ባለፈው ረቡዕ ወደ ልጇ መኝታ ቤት ስታመራ ልጇ መኝታ ቤቱ ውስጥ አለመኖሩን ነገር ግን በመኝታ ቤቱ ውስጥ ማስታወሻ ጥሎላት እንደሄደ ተናግራለች። እናቴ ለጊዜው ወደ ሆስፒታል ሄጃለሁ። አትጨነቂ ከሰዓት በኋላ ወደቤት እመለሳለሁ ብሎ መልዕክት እንዳስቀመጠላት ተናግራለች። ይሄንን ማስታወሻ ካስቀመጠ በኋላም ከማብሰያ ክፍል ቢለዋ በመውሰድ ግራ እጁ ክንዱ ላይ እንደቆረጠ ተገልጿል። እጁን ቆርጦ መሬት ላይ ከጣለ በኋላም ታክሲ ጠርቶ በአቅራቢያው ወዳለው ድንገተኛ የህክምና ቦታ ሄዷል።

ከቆይታ በኋላ ፖሊስ ወደ ስፍራው አምርቶ የተቆረጠውን የወጣቱን እጅ ወደ ሆስፒታል የወሰደው ሲሆን፤ የቀዶ ህክምና ባለሙያዎችም የወጣቱን እጅ መልሰው ለመግጠም ጥረት አድርገዋል። ነገር ግን እጁ ከተገጠመ በኋላ እንደበፊቱ ሙሉ እንቅስቃሴ ለማድረግ ይችላል የሚለውን በእርግጠኝነት መናገር እንደሚቸገሩ ባለሙያዎቹ ተናግረዋል።

የሀገሪቱ ኤክስፐርቶች እንደሚገልፁት በቻይና 649 ሚሊዮን የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ያሉ ሲሆን፤ 24 ሚሊዮን ወጣቶችም በኢንተርኔት ሱስ የተጠመዱ ናቸው። ይህ ማለት ደግሞ ከሀገሪቱ ወጣቶች መካከል 14 በመቶዎቹ የዚህ ሱስ ተጠቂዎች ናቸው። በዚህ ሱስ ምክንያት ግማሾቹ ከትምህርት ገበታቸው እንደሚርቁ፤ ቀሪዎቹም ወደመኝታቸው እንኳን መሄድን እንደማይመርጡ ተዘግቧል። ወደመኝታቸው የሚሄዱትም ቢሆኑ አልጋቸው ላይ ተጋድመው ኢንተርኔት መጠቀምን እንደሚመርጡም ዘገባው ጨምሮ አስነብቧል።

# ቅጣት በፀጉር ቁርጥ ላይ

ከወደ አትላንታ ሰሞኑን የስነ-ምግባር ችግር ያለባቸውን ህፃናት እና ታዳጊዎች ለመቅጣት ለየት ያለ እርምጃ እየተወሰደ ነው። ይኸውም የስነ-ምግባር ችግር ያለባቸው ህፃናት እና ታዳጊዎች ሽማግሌ የሚያስመስላቸውን እና ቤንጃሚን በተን የተባለውን የፀጉር ቁርጥ እንዲቆረጡ ማድረግ ነው። ይህን አይነቱ የፀጉር ቁርጥ የጭንቅላት መካከሉን በመላጨት ከበስተኋላ እና ከዳርና ዳር ፀጉር በማስቀረት ታዳጊው ሽማግሌ እንዲመስል ያደርገዋል ተብሏል።

የፀጉር ቤት ባለቤት የሆነው ፌሬድሪክ ራኬል ይህን ዓይነቱን የቅጣት ሙከራ የ12 ዓመት እድሜ ባለው የገዛ ልጁ ላይ እንደሞከረው ገልጿል። በዚህም ሳቢያ ከክፍል ወደ ክፍል መዛወር አቅቶት የነበረው ልጁ ለውጥ ማምጣቱን ገልጿል። ፍሬድሪክ ይህን የቅጣት የፀጉር ቅርፅ ያለመንም ክፍያ እየሰጠ መሆኑን የገለፀ ሲሆን፤ በዚህ ዓይነቱ መንገድ ልጇ እንዲቀጣ ያደረገችው አንዲት ሴትም ውጤታማ መሆኗን ተናግራለች። በትምህርት ቤት ውስጥ ያልተገባ ባህሪይ እያሳየ ያስቸግር የነበረው ልጇ ፀጉሩ በዚህ ቅርፅ በመቆረጡ ፀባዩን ማስተካከሉን እና ከአራት ቀናት በኋላም ፀባዩን በማስተካከሉ የፀጉር ቁርጡን ሊያስተካክል ወደ ፀጉር ቤቱ ማምራቱ ተገልጿል። አብዛኞቹ ልጆችም እንዲህ አይነቱ ቅጣት ለምን እንደተጣለባቸው ስለሚገባቸው ከስህተታቸው እየተማሩ ነው ተብሏል ሲል ያስነበበው ዋሺንግተን ፖስት ነው።

# ባላገር

የአንድ ሀገር ንጉሥ የሚያስተዳድራትን ሀገር ዙሪያ ገባዋን ለመጎብኘት አስቦ ሠራዊቱን ከአንድ ገላጣ ሜዳ ላይ ይተውና አልባሌ ልብስ ለብሶ እንደነገሩ በሆነች በቅሎ ይቀመጥና ወደ አንድ መንደር ይዘልቃል። ከመንደሯ መግቢያ ላይ አንድ ባላገር ከገበያ መልስ ጌሾውን ተሸክሞ ወደቀየው ሲያቀና ያገኘዋል። ንጉሡም "ባላገር ለሀገሩ እንግዳ ነኝ እባክህ ይህን አካባቢ በቅጡ እንዳውቀው ብትረዳኝ?" ብሎ ይጠይቀዋል። ባላገሩም "ጌታው እርስዎ እበቅሎ ላይ እኔ ደግሞ እንደሚያዩኝ በእግሬ እያዘገምኹ ነው እንዴት ይሆናል" አለ። ንጉሡም "ና ወደበቅሎዬ ውጣና ላፈናጥህ" አለው፤ ባላገሩመ "እንዴ ጌታው ጌሾዬንስ የት ላድርገው?" ብሎ ይጠይቃል። ንጉሡም "የጌሾህን ዋጋ ሁለት እጥፍ አድርጌ እሰጥሃለሁ ጣለው" ይለዋል ባላገሩ ጌሾውን ወዲያ ጥሎ ከንጉሡ በቅሎ ላይ ከኋላ ተፈናጠጠ። ባላገሩ ከንጉሥ ጋር መሆኑን በጭራሽ አላወቀም። የመንደሩን ውስጡንና ውጪውን እያዟዟረ በደንብ ካስጎበኘው በኋላ ሰራዊቱ ተሰብስቦ ደጅ ወደሚጠናበት /ወደሚጠብቅበት/ ገላጣ ሜዳ ያመራሉ። የሰራዊቱን በፈረስ ላይ ሆኖ መጠባበቅ ከርቀት ያየውና በንጉሡ በቅሎ ከኋላ የተፈናጠጠው ዕድለኛ ባላገር በነገሩ ግራ ይጋባና ይጠይቃል። "ጌታው እዚህ አካባቢ ንጉሥ አለ እንዴ?" ሲል ንጉሡም "እንዴት እንዲህ ልትል ቻልክ? ቢለው "ሰራዊቱን ባይ ጊዜ ነዋ! ጌታው" ብሎ ይመልሳል። ንጉሡም "አዎን እዚህ አካባቢ ንጉሥ አለ" ይለዋል "ታዲያ ንጉሡ ማነው ጌታው?" ብሎ ይጠይቃል የዋሁ ባላገር። ንጉሡም እራሱን ደብቆ "እኔም አላወኩትም ባላገር ዝም ብለን ወደ ሠራዊቱ እንጠጋና ሰራዊቱ ከየፈረሱ እየወረደ እጅ ሲነሳ አንድ በፈረስ ወይም በበቅሎ የተቀመጠ ሰው ብቻ ይቀራል። ያኔ እኛም ለዛ ሰው እጅ እንነሳለን፤ ያ ሰው ንጉሡ ነውና" ይለዋል። በዚህ ተስማምተው ሁለቱም ወደ ሠራዊቱ ያቀናሉ። ሠራዊቱ ሁሉ ከፈረሱ ይወርድና ለንጉሡ እጅ ይነሳል። ንጉሡ ባላገሩን ወርዶ እጅ ይነሳኛል ብሎ ቢጠብቀው ባላገር ሆዬ እንኳን ደንግጦ ሊወርድ ቀርቶ ምንም ስሜት አልታየበትም። በሁኔታው የተገረመው ንጉሡ ወዳፈናጠጠው ባላገር ዞር ብሎ "ባላገር ንጉሡ ማነው?" ሲለው ባላገሩ ቀልጠፍ ብሎ "አሃ! ጌታው እኔ ነኛ!" አለና አረፈው።

ምጥን ቅመም -
በዲ/ን ምትኩ አበራ

## ባለ ቀለም ህልሞች

ከጥንት እንቅልፋችን
ዛሬ ያልፋቅናቸው፣
ህልም አለን እያልን
ደብዝዘው የቀሩ
ቅርፅ ስዕላቸው፣
ነፍስን የማይዘሩ
ከደም የቀጠኑ
ቀለም አልባ ናቸው።
ፈዛዛው ቅርፅና
ጥበብ ፈለጋቸው
ደርሶ አይታወቅም፣
በውድቅት የሳሉት
ንጋትን ይሸሻል
ሰንብቶ አይዘልቅም።
ቀለምአማ ህልሞች
ላመታት ካለሙ፣
ፅልመትን ገላልጠው
ነፍስን እያከሙ፣
ከልብ እሽክርክሪት
ዘመናት አይሸርም
ህልምና ቀለሙ።
ዘመን ተሻጋሪ
ስሜትን ጠንስሰው፣
በምኞት ምዕራፍ
ህይወትን ሸብ አርገው፣
ያለምን ልቃቂት
የንባዎችን ጅረት
መድረሻ አበጅተው፣
መጪን በሚናፍቅ
ሂያጅን በሚያፀና
ጥበብ ይቦካሉ፣
በፀዳል ብርሃን
ትንሳኤና ፍቅርን
በአንድ ይሰብካሉ፣
አመታት ሲነጉዱ
ዘመን እያሰሉ
ልቦችን ወጥረው፣
የማይደበዝዙ
ባለቀለም ህልሞች
አይረሱ ምነው።
ቋጠሮ - በማህደር ሽፈራው

# ፎሮፎር የሚተላለፍ በሽታ አይደለም

**ዶክተር ድጋፌ ፀጋዬ የቆዳ እና የአባላዘር በሽታ ስፔሻሊስት ናቸው። ዶክተር ድጋፌ በዚህ ሙያ ለአስር ዓመታት ያገለገሉ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅትም በአለርት ሆስፒታል በማገልገል ላይ ይገኛሉ። ዶክተር ድጋፌን በፎረፎር በሽታ እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ አነጋግረን የሚከተለውን ጽሁፍ አቅርበናል።**

**በመስከረም አያሌው**



ዶ/ር ድጋፌ ፀጋዬ

ሰንደቅ፡- ፎሮፍር የሚባለው በሽታ ምንድን ነው?

ዶ/ር ድጋፌ፡- ፎሮፎር በህክምና አጠራር ሴቦሪክ ደርማታይተስ የሚባል በሽታ ውስጥ የሚመደብ ነው። ዋና ስሙም ደንድሮፍ ነው የሚባለው። ሴቦሪክ ደርማታይተስ የሚባለው የቆዳ መቆጣት ነው። የቆዳ መቆጣት የሚከሰትባቸው የሰውነት ቦታዎች አሉ። ይኸውም ፊት ላይ፣ ፀጉር ላይ፣ ደረት እና ጀርባ ላይ እንዲሁም ጆሮ ላይ ይከሰታል። እነዚህ ቦታዎች ቆዳ ወዛማ የሚሆንባቸው ቦታዎች ወይም ሴቦሪክ ኤሪያ የሚባሉት ናቸው። በእነዚህ ቦታዎች ላይ የቆዳ ቅባት የሚያመነጩ ዕጢዎች አሉ። እነዚህ ዕጢዎች ባሉበት ቅባታማ ቆዳ ላይ የሚከሰተው የቆዳ መቆጣት ይኖራል።

በጣም ቀላሉ እና የመጀመሪያው የቆዳ መቆጣት ፎሮፎር ወይም ዳንድሩፍ ይባላል። ይሄኛው ደረጃ በጣም አነስተኛው ደረጃ ነው። ይሄ ፎሮፎር የፀጉር ብቻ ችግር አይደለም። አልፎ አልፎ ደረት እና ጀርባ ላይ እንዲሁም ከጆሮ ፊት ለፊት እና በጆሮ ጀርባ ላይ ሊታይ ይችላል።

ፎሮፎር እና ቆረቆርን መለየት ያስፈልጋል። ፎሮፎር የአዋቂ በሽታ ነው። ህፃናት ላይ ከተከሰተ ከተወለዱ ከአንድ ዓመታቸው በፊት የሚከሰት ነው። በአብዛኛው ህክምናውም የሚቀባ ነው። ነገር ግን እድሜያቸው ከአንድ ዓመት እስከ 14 ዓመት በሆናቸው ልጆች ላይ የሚከሰተው ፎሮፎር የሚመስል ነገር ካለ ቆረቆር ነው። ይሄ ቆረቆር ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ የመተላለፍ ባህሪይ አለው። ካልታከመ ደግሞ መቆሳሰልን እና የፀጉር መመለጥን ያመጣል። ነገር ግን ታክሞ መዳን ይችላል።

ሰንደቅ፡- የፎሮፎር በሽታ መንስኤ ናቸው ተብለው የሚቀመጡት ምን ምን ናቸው?

**ፎሮፎር እና የቆዳ ድርቀትንም መለየት ተገቢ ነው። ሰዎች ፎሮፎር የቆዳ ድርቀት ይመስላቸዋል። ድርቀት ከሆነ ፀጉር ብቻ ሳይሆን ሌሎችም የሰውነት ክፍሎች የሚደርቁበት ሁኔታ አለ። በተፈጥሮ ደረቅ ቆዳ ያላቸው ሰዎች ፀጉራቸው ብቻ አይደለም የሚደርቀው። የቆዳ ድርቀት ሲኖር መታጠብን በመቀነስ እና ከታጠብን በኋላ ቅባቶችን ማዘውተር ያስፈልጋል።**

ዶ/ር ድጋፌ፡- የፎሮፎር መንስኤው ከሦስት ነገሮች ጋር ተያይዞ የሚጠቀስ ነው። አንደኛው ከሰውነት ቆዳ ቅባት መጨመር ጋር ይያያዛል። ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ፈንገስ ነው። ማልሴሲያ ፈርፈር የሚባል ፈንገስ አለ። ፎሮፎር የሚለው ስምም የመጣው በዚህ ነው። ይሄ ፈንገስ የማይተላለፍ እና አንድ ሰው በተወለደ በ48 ሰዓታት ውስጥ ቆዳ ላይ የሚያርፍ ፈንገስ ነው። ፈንገሱ ከእናት ወደ ልጅ የሚያልፍ ፈንገስ ሲሆን፤ ጉጂ ያልሆነ እና ሁልጊዜ ከቆዳችን ላይ የማይታጣ የፈንገስ አይነት ነው። የዚህ ፈንገስ ከመጠን በላይ መጨመርም የፎሮፎር መንስኤ እንደሆነ ይገለፃል። በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ የዚህ ፈንገስ መጠን መጨመር የሰውነት መቆጣትን ይቀሰቅሰዋል። ስለዚህ በሰውነት ቅባት መጠን መጨመር እና የፈንገሱ መብዛት በጋራ የሚያመጡት የቆዳ መቆጣት ሌላው መንስኤ ይሆናል ማለት ነው።

ሰንደቅ፡- የፎሮፎር በሽታ በእድሜ እና በጾታ ላይ ያለው ተጋላጭነት ምን ይመስላል?

ዶ/ር ድጋፌ፡- በአብዛኛው ፎሮፎር የሚታይባቸው ሁለት የእድሜ ክልሎች ናቸው። ፎሮፎር በየትኛውም የእድሜ ክልል ላይ የሚታይ አይደለም። እድሜያቸው ከአንድ ዓመት በታች ባሉ ህፃናት እና እድሜያቸው ከ14 ዓመት በላይ በሆኑ ሰዎች ላይ ነው የሚታየው። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ የሰውነት ቆዳ ቅባት መብዛት እነዚህን የእድሜ ክልሎች ተከትሎ የሚመጣ በመሆኑ ነው። በእነዚህ የእድሜ ክልሎች ውስጥ ሰውነት የሚያመነጫቸው አንድሮጂን የተባሉ ሆርሞኖች አሉ። ከ14 ዓመት በኋላ የሚመነጩት የጉርምስና ሆርሞኖች ናቸው ቆዳ ቅባታማ እንዲሆን የሚያደርጉት። ከአንድ ዓመት በታች የእድሜ ክልል ውስጥ ግን ከእናት ወደ ልጅ የሚመጣ ሆርሞን ነው። ስለዚህ የፎሮፎር ችግር እድሜያቸው ከአንድ ዓመት አስከ 14 ዓመት ባሉ ታዳጊዎች ላይ አይታይም።

ሰንደቅ፡- ፎሮፎርን ከሌሎች በሽታዎች ለመለየት ያሉት ምልክቶች ምን ምን አይነት ናቸው?

ዶ/ር ድጋፌ፡- ምልክቶቹ እንደየበሽታው የጉዳት መጠን ይለያያሉ። በጣም ቀላሉ ዳንድሩፍ የሚባለው ከሆነ እንደደረቅ ቆዳ ወይም እንደ ዱቄት ብናኝ ሆኖ የሚከሰት ነው። ይሄ ፎሮፎር በብዛት የሚወጣው ፀጉር ላይ ሲሆን፤ ይፈረፈራል፤ ይቦናል። ከፀጉር ካለፈ ግን አንዳንድ ጊዜ የዓይን ቅንድብ ላይ፣ ሽፋሽፍት ላይ እንዲሁም የጆሮ ፊት ለፊት እና ጀርባ ላይ ሊከሰት ይችላል። በተጨማሪም በአፍንጫ ዳርዳር ላይ የመንጣት ወይም የመላጥ ምልክት ያሳያል። ደረጃው እየጨመረ ሲመጣ ግን ቀለሙ ቢጫ ሆኖ ወደሚጋገር ቅርፊት ይቀየራል። ይሄ ቅርፊት ቅባታማ ነው። በሽታው ከእነዚሁ ደረጃዎች ካለፈ አሊያም የኤች አይ ቪ ኢንፌክሽንን የመሣሰሉ የውስጥ ችግሮች ካሉ በጣም ተሰራጭቶ ሰውነት በአጠቃላይ እየቆሰለ ይሄዳል።

ፎሮፎር እንግዲህ በሁሉም ሰው ላይ አይከሰትም። በአጠቃላይ ስንመለከት ከ15 እስከ 20 በመቶ የሚሆኑ ሰዎች የፎሮፎር ችግር ይኖርባቸዋል። ይሄ የሚሆነው በተፈጥሮ ካለው ተጋላጭነት የተነሳ ነው። ቤተሰቦቻቸው ፎሮፎር ያለባቸው ሰዎች የበለጠ ተጋላጭ ናቸው። ከዚያ ውጪ ግን መታወቅ ያለበት ነገር ፎሮፎር በማበጠሪያ፣ በፎጣ ወይም በፀጉር ማስተካከያዎች እና በሌሎች ንክኪዎች ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍ አይደለም። ሌሎች ፎሮፎር የሚመስሉ በሽታዎች አሉ። ልክ ፎሮፎር መስለው የሚወጡ ፈንገሶች ቆረቆር እና የመሳሰሉት ስላሉ መለየት ያስፈልጋል እንጂ ፎሮፎር አይተላለፍም።

በጾታ ረገድ ስናየው ከሴቶች ይልቅ የበለጠ ተጋላጮቹ ወንዶች ናቸው። ምክንያቱ ደግሞ ለፎሮፎር መንስኤ የሆነው አንድሮጂን ሆርሞን የሚታየው በብዛት በወንዶች ላይ በመሆኑ ነው። ሴቶች ላይ ቢኖርም በወንዶች ላይ ግን ችግሩ ጐልቶ ይታያል። በብዛት ስለቆዳ የሚጨነቁት ሴቶች ስለሆኑ በብዛት የሚታከሙትም ሴቶች ናቸው።

ሰንደቅ፡- ይሄንን የፎሮፎር በሽታ የሚያባብሱት ነገሮችስ ምንድን ናቸው?

ዶ/ር ድጋፌ፡- በሽታውን ይቀሰቅሳሉ ወይም ያባብሳሉ የተባሉ የታወቁ ነገሮች አሉ። አንደኛው ጭንቀት ወይም የአዕምሮ ውጥረት ነው። በጭንቀት ወቅት በተለይ በአዋቂዎች ላይ በሽታው የሚባባስበት ሁኔታ አለ። ሌላው ደግሞ ወቅት ነው። በተለይ በቀዝቃዛ ወቅት ላይ የፎሮፎር በሽታ የመባባስ ባህሪይ አለው። ከዚህ በተጨማሪም የውስጥ ችግሮች ያባብሱታል። ለምሳሌ የኤች አይ ቪ ኢንፌክሽን ካለ ፎሮፎር ይብሳል። ደረጃውም ይጨምራል። አልፎ አልፎ ደግሞ ነርቭ በሚጐዱ በሽታዎች ምክንያት እንዲሁም በተለያዩ መድሐኒቶች ምክንያት ሊባባስ ይችላል።

ሰንደቅ፡- ችግሩ ፎሮፎር መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ የሚሰጡት ህክምናዎች ምን ምን ናቸው?

ዶ/ር ድጋፌ፡- ህክምናው ፎሮፎሩ በተከሰተበት ቦታ ይወሰናል። ችግሩ የተፈጠረው ፀጉር ላይ ሲሆን፤ በአብዛኛው ፀረ-ፈንገስ ሻምፖዎችን እናዛለን። ፎሮፎር በየጊዜው የሚታከም እንጂ በአንድ ጊዜ ህክምና የሚጠፋ ስላልሆነ እነዚህን ሻምፖዎች ለረጅም ጊዜ እንዲጠቀሙ እናደርጋለን። በተጨማሪ ደግሞ የቆዳ መቆጣትን የሚያክሙ የሚቀቡ እና የሚቀመሙ ቅባቶችንም ልናዝ እንችላለን። ፊት ላይ ሲሆን ደግሞ የሚቀቡ ቅባቶች ይታዘዛሉ። በሽፋሽፍት ላይ ሲሆንም የሚታዘዙ የተለዩ ሻምፖዎች አሉ።

በገፅ 16

ሕግ

በኪዳኔ መካሻ (የሕግ ባለሙያ)
Kidane1983@yahoo.com

# ፕሮፌሰር እንድሪያስ ስለጠበቆች

ታዋቂው ምሁር ፕሮፌሰር እንድሪያስ እሸቴ በተለያዩ የውጭ ሀገር ዩኒቨርስቲዎች በማስተማር የተለያዩ የፍልስፍና የጥናት ጽሁፎችን በመፃፍ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህርና የዩኒቨርስቲው የቀድሞ ፕሬዝዳንት ሆነው አገልግለዋል:: በአሁኑ ጊዜም የጠቅላይ ሚኒስትሩ ልዩ አማካሪ ሆነው እያገለገሉ ያሉ ምሁር ናቸው::

እ.ኤ.አ. በ1484 “The Good Lawyer, lawyers Rodes & Lawyers Ethics” በታተመው ቅጽ 3 የፍልስፍና እና የህግ የጥናት መጽሔት ላይ “Does a lawyers Character matter” የሚል ጹሁፋቸውን ከፍል አንድን ወደ አማርኛ መልሼዋለሁ::

- ጠበቆች አንዳንድ ጊዜ ለባህሪያቸው በቀላሉ የማይጨበጥ የሚመስል ምክንያት በማቅረብ ራሳቸውን የማይመኙት ሁኔታ ላይ ያገኙታል:: ሙያዊ ስራቸውን ሲያካሂዱ ከምግባር (ዋለል) አንፃር አጠያያቂ በሆነ መልኩ እንድንሰራ ይጠበቅብናል ይላሉ:: በምሳሌነት ጥፋት መስራቱን እያወቁ ደንበኛቸው እንዳይጋለጥ በንቃት መጠበቅን ይጠቅሳሉ:: ይህንም በማድረጋቸው ከምግባር አንፃር ጠቃሚ ግብን እንደሚያሳኩና ይህን ግብ የሚያሳኩበት ሌላ የተሻለ መንገድ እንደሌለም ያነሳሉ:: ይህ አባባላቸው ግን አመኔታ የሚጣልበት አይመስልም:: ምክንያቱም እንደተነገረን አንዳንድ ጊዜ በዚህ ሙያ ውስጥ ጥሩ ነገር የሚገኘው በመጥፎ ሁኔታ በመስራት ብቻ ነው::

በቅድሚያ ጠበቆች እንዴት መልካም ምግባርን ሊደረድር የሚያቀርብ ሁኔታ ውስጥ እንደሚወድቁ ላሳይ:: በተለይም ጠበቆች እንዲያደርጉ የሚጠየቋቸው የተወሰኑ ነገሮች፣ ለስራ ዝግጁ የሚያደርጋቸው ስልጠና፣ ሙያዊ ስራቸውን የሚመሩበት እሳቤ እና በተወሰኑ የሕግ ስራዎች ውስጥ የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ናቸው ወደዚህ አጠራጣሪ ባህሪ ውስጥ ስበው የሚከቷቸው በመቀጠልም እነኚህን ጠበቆችን ከምግባር አንፃር የሚያስጠረጥራቸውን ግፊቶች ብናውቅም ሙያው ላይ ያለብንን ጭንቀቶች ሙሉ በሙሉ የሚያስወግድ አለመሆናቸውን እጠቁማለሁ:: በመጨረሻም ጠበቆች በአፀያፊ ስራዎች ውስጥ የሚሳተፉበት አሳማኝ ምክንያት አለመኖሩን በቀላሉ የሚያሳዩ ሕጋዊ ሁኔታዎችን አስቀምጣለሁ:: እዚህ ጋር ጠበቆች በሌላ የህዝቡ ህይወት ውስጥ የሚነሱ ነጥቦችንና ምላሻቸው የተለያዩ የባህሪ ልቀቶችን የሚጠይቁ ነገሮች በቀጥታ ይገጥሟቸዋል:: ጠበቆች ከዚህ ማእቀፍ ጋር በተጣጣሙ ፅንሰሃሳቦች የሚመሩ ቢሆን ኖሮ አሁን ስራቸው ላይ እያስተናገዷቸው ያሉ በርካታ አደጋዎችንም ማስወገድ በቻሉ ነበር::

የጠበቆችን ስራ ለመረዳት በሌሎች ሙያዊና ከፍተኛ ኃላፊነትን እንዲሁም በቀጥታ ለግለሰቦች አገልግሎት መስጠትን ባካተቱ ሥራዎች ውስጥ የማይታዩ ጥቂት በግልጽ የሚታዩ የጠበቆችን የሥራ ገፅታዎች ማወቁ ጠቃሚ ነው:: አንደኛው ምክንያት ጠበቆች የሚያገለግሉት አካል ጥቅም ወይም ፍላጎት ሁልጊዜም መልካም አለመሆኑ ነው (እንደሚመስለኝ ይህ ከዴቪድ ሂዩም የፍትህ የተወሰኑ ስራዎች ሁልጊዜም መልካም አይደለችም ከሚለው እሳቤው ጋር የሚያያዝ ነው) ከዚህ አንጻር የጠበቆች ሚና ከመነሻውም አጠራጣሪ ነው:: የህክምና ዶክተሮች ሚና ግን አጠራጣሪ አይባልም:: ምክንያቱም በአጠቃላይ ሀኪሙ ሙያውን ከህክምና ውጭ ላሉ አላማዎች ካላዋለው በስተቀር የሚያስጠብቀው ጥቅም መልካምነቱ የማያጠያይቅ ነው:: ይህ በህክምና ዶክተሮችና በጠበቆች ሚና መሀል ያለው ልዩነት ብዙውን ጊዜ ጠበቆች የሚያስጠብቁት የደንበኛቸውን ሕጋዊ መብቶች እንደሆነ አድርጎ በማስቀመጥ ይደበቃል:: ሆኖም ጠበቆች የሚያስጠብቁት ጥቅም ጭራሹንም ሕጋዊ ላይሆንም ይችላል:: በተጨማሪ ፍትሃዊ ባልሆነ የሕግ ስርዓት አንድ ስሙ ለሕጋዊ መብቶቹ ከሞራል (ምግባር) አንጻር ላይገቡት ይችላሉ:: በትክክለኛው የፍትህ ስርዓትም ውስጥ ቢሆን አንዳንዴ ሕጋዊ መብትን መተግበር ጥፋት ሊሆን ይችላል::

ሌላኛው የጠበቆች ሥራ ከዶክተሮች ሥራ የሚለይበት አይነተኛ ምክንያት ጠበቃው የሚቆምለት የደንበኛው ፍላጎት በሌሎች ፍላጎት ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ የሚያሳርፍ መሆኑ ነው:: ጠበቃው የደንበኛውን ጥቅም በደምብ ማስጠበቅ የሚችለው የሌሎችን ጥቅም በመዝጋት ወይም በማሸነፍ መሆኑ በተደጋጋሚ የሚታይ ነው:: አንድ ዶክተር ግን እየሰራ ያለው የከፋ የህክምና አገልግሎት ኢ ፍትሃዊ ስርጭት ባለበት ማህበረሰብ ውስጥ ወይም እንደ ጦርነት፣ ድርቅ እና የመሬት ርደት ካለ የአስቸኳይ ጊዜ የአደጋ ሁኔታ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር ለታካሚው የሌሎች ህመምተኞችን ሁኔታ ሳያባብስ ሙያዊ አገልግሎቱን መስጠት ይችላል:: በመሆኑም ጠበቆች እንዲያገለግሉት የሚጠየቁት ፍላጎት አይነትና አገልግሎቱን የሚሰጡበት መንገዶች አይነተኛ ባህሪ ስህተት ለመስራት ተጋላጭ አድርገቸዋል::

መደበኛው የሕግ ትምህርትም ጠበቆችን ለሙያው ሞራላዊ አደጋዎች የሚያዘጋጅ አይደለም:: ይዘቱን ትተነው የሕግ ስልጠና ዋነኛው አላማ ተማሪውን ብቁ ተሟጋች እንዲሆን ማስቻል ነው:: የሕግ ትምህርት የሙግትን ክህሎችን አመለካከት ማሳደጉን በሕግ ትምህርቤት የትምህርት ስርዓት የሚሰጡ ብዙዎቹን የትምህርት አይነቶች በመጫን የሚረጋገጥም አይደለም:: ሕጎችን ወይም የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔዎችን መተንተን ሙያዊ የሆነው የሙግትን ጥበብን የማዳበርን አላማ አንቀሳቃሽነቱ በግልጽ የሚታይ አይደለም:: ከምጣኔ ሀብታዊና ከታሪካዊ እይታ አንጻር መዋቅራቸውንና የሕግ ድንጋጌዎን የመነሻ ምክንያት ስንፈትሽ ሕግ በአመዛኙ የሚቆጠረው እንደሌሎቹ የኢኮኖሚያዊ የትምህርት ዘርፎች ነው:: ይሁን እንጂ በዚህ አካዳሚያዊ ገፅታውም ቢሆን የሕግ ትምህርት የተለመዱ የምሁራዊ ጥናት አላማዎችን አያገለግልም:: ተማሪዎችም ሕግን እንደ አካዳሚያዊ የትምህርት መስክ የሚተረጉሙ ስነስርዓቶችን እና ባህሎችን እንዲካኑ አይበረታቱም ወይም አይጠበቅባቸውም:: ከዚህ ጋር በተያያዘ የሕግ መምህራንም ተማሪቻቸውን የወደፊቱ የሕግ መምህር ወይም ምሁር አድርገው አይመለከቷቸውም:: በሕግ ትምህርት ውስጥ የንድፈ ሃሳብም ሆነ የተግባር ስልጠናዎች ዋነኛ አላማም ተማሪውን በአይነቱ ለየት ላለው ለሙግት (ለክርክር) ሚና ማዘጋጀት ነው:: እውቀቱም ጠቀሜታው የተዋጣለት ተሟጋች የሚጠበቅበትን ማሟላት እስከቻለ ድረስ ሲሆን ከሁሉም በላይ ደግሞ ከየትኛውም ተከራካሪ ጎን ቆሞ ጉዳዩን አሳማኝ አድርጎ ለማቅረብ ነው:: ይህ አይነት የትምህርት ብልሀት ማሟላት የማይጠይቀው ነገር ቢኖር ትክክለኛው ነገር ምንድን ነው የሚለውን ለመወሰን የሚያስችል የዳበረ አቅም አልያም ይህንኑ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ዝንባሌን ነው:: እንደተባለውም ይህ የሞራል ውስጣዊ እይታ በብልጠት መንገዱ በመሀል ገብቶ አላማው ለገሀዳዊው ዓለም ፋይዳ ያለውም ሆነ የሌለውም ቢሆን ያን አላማ ለማሳሳት የሚቻለውን አማራጭ ለመጠቀም የመወሰን ወይም የመጠቀምን አቅምን ይገታዋል::

የጠበቆችን ሥራ እና ትምህርት ሞራላዊ ተጠያቂነቱን የሚያባብሰው ስለሚናቸው ያለው ባላንጣዊ ግንዛቤ ነው:: በዚህ ግንዛቤ ውስጥ ጠበቃው የደንበኛውን ጉዳይ በተቻለ መጠን አሳማኝ አድርጎ እንዲያቀርብ ይጠበቅበታል:: ይህ ደግሞ በራሱ የደንበኛውን ፍላጎት ሞራላዊ ፋይዳ ምንም ይሁን ምን ያለ ልዩነት ማስተናገድን ስለሚጠይቅ የጠበቃው ለጉዳዩ ያለው ፍላጎት ለደንበኛው ጉዳይ ባለው ግላዊ አመለካከት የተነሳ እንዳይረግብ ወይም እንዳይቀንስ ያደርገዋል:: ከምንም በላይ ደግሞ ከሌላኛው ወገን በተቃራኒ የሚሟገተው ጠበቃ የደንበኛውን ፍላጎት ከተቃራኒው ተሟጋች እና ከሶስተኛ ወገኖች ፍላጎት እንዲሁም እንደ ፍትህ ካሉ ህዝባዊ እሴቶች እንዲያስቀድምም ይጠየቃል:: የደንበኛውን ፍላጎት ሲያስጠብቅ ሕጋዊ የሆኑ ጥቅሞችንም የመጣስ ኃላፊነትንም እንዲሸከም ሁሉ ይጠየቃል:: በአጭሩ ለአንደኛው ወገን የሚሟገተው ጠበቃ በማህበራዊ ግጭቶች ውስጥ የከፋ ሞራላዊ ሁኔታ ላይ ካለው ወገን ጎን ሊቆም እንደሚችል ሳያሳስበው ለአንዱ መወገን አለበት:: የጠበቃው የተቃራኒን ተሟጋችነት እሳቤ እንግዲህ የሙያዊ ስራውን አሳዛኝ አደጋዎች ወደ ጠበቃው መልካም ሚናነት ያሸጋግረዋል:: በተወሰኑ የህግ ሙያ ስራዎች በተለይም የወንጀል ክስ መከላከል ዙሪያ ያሉት የተከራካሪ ጠበቃውን የሞራል አቋም ፅኑ ፍላጎት የሚያበረታቱ ናቸው:: በጥፋተኝነት በፍ/ቤት መወንጀል በጣም ከባድ ጉዳይ ነው:: መንግስት

የጠበቆችን ስራ ለመረዳት

በሌሎች ሙያዊና ከፍተኛ

ኃላፊነትን እንዲሁም በቀጥታ

ለግለሰቦች አገልግሎት

መስጠትን ባካተቱ ሥራዎች

ውስጥ የማይታዩ ጥቂት

በግልጽ የሚታዩ የጠበቆችን

የሥራ ገፅታዎች ማወቁ

ጠቃሚ ነው

የአንድን ሰው ባህሪ መቆጣጠሩ ማንም ሰው በምክንያታዊነት የሚቀበለው አይደለም:: የፍርድ ቅጣቱ የሚካሄደው ክፍት በሆነ የህዝብ እይታ ፊት ሲሆን በዚያም ሰፊውን ትኩረት የሚስበው ከግለሰባዊው ጸጸት ወይም ቁጭት ይልቅ የግለሰቡ ውድቀት ነው:: በዚህ የተነሳ ከፋ ተፅዕኖው በግለሰቡ ህይወት ሙሉ ማስተጋባቱ አይቀርም:: መንግስት ወክሎ ስልጣኑን በሰጣቸው በግላዊ አመለካከትና ከአድሎአዊነት ጫና ውስጥ የማይወድቁ ተደርጎ በሚገመቱት ፈራጆች ግለሰቡ ጥፋተኛ በመባሉ ነው:: ፍርዱ ትልቅ ግምት የሚኖረው በጎን በኩል ደግሞ ግላዊ ህይወቱ ላይ ትልቅና ሰፊ ውጤት የሚያመጣ ሆኖ እያለ በተሰጣቸው ስልጣን ፍርዱን የሚያሳርፍበት ፍርዳቸው በግለሰቡ ላይ ስለሚያመጣው ጫና ጥቂት ብቻ የሚያወቁ ወይም ብዙም ግድ የሌላቸው ሰዎች ናቸው::

በወንጀል የተፈረደባቸው ጥፋተኞች የሚያጋጥሟቸውን ቅጣት በተመለከተ እራሳቸው ሰልጥነናል ብለው በሚኩራሩት እንኳን ያሉአቸው ተከላካዮች ጥቂት ናቸው:: ወህኒ የገቡ ታራሚዎች ኢሰብአዊና አዋራጅ ለሆኑ አያያዝ፣ የተሻለ አያያዝ አላቸው በሚባሉት ዘንድ እንኳን ሰለባዎች ናቸው:: በአንድ የሆነ ጉዳይ ላይ መንግስት የወሰደው እርምጃ ተገቢ መሆኑን እርግጠኛ ብንሆንም እንኳን በአብዛኛው የማረሚያ ተቋማት የሚካሄደውን አያያዝ ጋር አስተያየትን እንዴት እንደሆነ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው:: የወንጀል ፍርደኛው የውርደት ስሜት የእስሩን ጊዜ ሲያጠናቅቅ የሚቋረጥ መሆኑንም እንዲሁ ማረጋገጥና ማሳየት አንችልም:: ሕጉ የሚያስከፍለውን ዋጋ የከፈሉ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚመርጡትን ስራ በመስራትና በመረጡት መኖሪያ የመኖርን የመሰሉ ነፃነቶቻቸውን መገፈፋቸው ይቀጥላል:: በመሆኑም በወንጀል ፍርድ መቀጣት ጥልቅና ለረጅም ጊዜ የሚዘልቅ ክፉ አሻራን በግለሰቡ ላይ የሚያሳርፍ ነው:: ግለሰቡ ደግሞ ንፁህ በሆነበት ወንጀል ከሆነ የተቀጣው የክፉ አሻራው ስቃይ ግዝፈቱ ከስሌት ሁሉ በላይ መሆኑ እርግጥ ነው:: መንግስት ወንጀልን በመቆጣጠሩ ስራና በተለይም አጥፊዎችን ከሶ ጥፋተኛ በማስባልና ወንጀለኞችን በመቅጣቱ ላይ ሰፊ ስልጣንና ኃይል አለው:: ፖሊስና ሌሎች የመንግስት የምርመራ አካላት ወንጀልን በመመርመርና ምርመራቸውን የሚደግፍ ማስረጃ በማሰባሰብ ትልቅ ስልጣንና ኃይል አላቸው:: አንዴ ግለሰቡ በመንግስት መዳፍ ውስጥ ከገባ መንግስት አንዳቸው ሊያደርገው ያለው ስልጣንና ኃይል ገደብ አልባ ነው:: ይሁን እንጂ አንድ ተራ ዜጋ የፈለገ አቅሙ ቢኖረው ውጤታማ መንግስት በሕግ ሊጠይቅ ከሚችልበት አስገዳጅ ኃይል ጋር ሊመጣጠን ግን አይችልም::

ከዚህ መሰረታዊ ሃሳብ በተቃራኒ ተከራካሪ ጠበቃ እንዴት ምክንያታዊ ይሁንታ እንደሚኖረው መረዳት ይቻላል:: ከወንጀል ፍርድ ጥፋተኝነት አንፃር ሲታይ ጠበቆች ስለደንበኛቸው ፍላጎት ፋይዳ ብዙም መጨነቅ አያስፈልጋቸውም:: ምክንያቱም የወንጀል ተከሳሹን ለመከላከል ጠበቃው የግለሰቡ ዋጋ ያላቸው አላማዎች የሆኑትን ነፃ የመሆንና የጭካኔና የሰብአዊነትን አዋራጅ አያያዝ ለማስወገድ እየሰራ መሆኑን ላይ ሊያርፍ ይችላል:: የሆነ ሰው ተከሳሹ አላማው መቀጣት ነው በሚል ይህን መከራከሪያ ላይቀበል ይችላል:: በተለይም በሀሳባዊያን ማህበራዊ ንድፈ ሃሳቦች ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ወንጀል የፈፀመ ግለሰብ የመቀጣት ፍላጎት አለው ወይም የበለጠ ገፋ ተደርጎ ከታየ ለመፀፀት ወይም ለመታረም የመቀጣት መብት አለው የሚሉ መከራከሪያዎች ያነሳሉ:: እንግዲህ የወንጀል ጥፋተኛው ንፁህ ከሆነ ይህ ተቃውሟቸው እሱን አይመለከትም:: በተጨማሪ ንፁሃን እና አጥፊዎችን ለመለየት የሚያስችል አስተማማኝ የሆነ ዘዴ ባለመኖሩ ጠበቃው የወንጀል ተከሳሾች ጠቃሚና የሚሰመርባቸው እንደ የተለየ ደንበኛ ግን የማይጋራቸው ኢላማዎች ምን መምሰል አለባቸው የሚለውን ለማሳየት የሚሞክር የሆነ መመሪያ ተግባራዊ ሊያደርግ አይችልም:: ይህ ሂደት ደግሞ በተለይ የሚታዩ ላይሆንም ይችላል:: ምክንያቱም የወንጀል ተከሳሾች ብዙውን ጊዜ ንፁሁ እንኳን ሳይቀር አንዳንዴ “ጥፋቱን አመነ” ለመቀጣት ያለውን ፍላጎት ገለፀ የሚያስብል ጭንቀት ውስጥ ይገባሉ:: አጥፊ ተከሳሽ እንኳን ለመፀፀት ያለውን ፍላጎት ቢያሳይና ቃሉን ቢሰጥ ይህ ፍላጎቱ በወንጀል የፍትህ ስርዓቱ በሚደረገው መልኩ መሟላት አለበት የሚያስብልም ግልጽ ያለ ምክንያት የለም:: በየትኛው መልኩ ቢሆን ቅጣቶች በጥፋተኞች ላይ የሚጣሉት ተቀበሉት አልተቀበሉት የሚለው ከግምት ውስጥ ሳይገባ ነው:: ስለዚህ በወንጀል ክስ መከላከል ውስጥ ጠበቃው የተሻለ ዋጋ የሚሰጠው ምክንያታዊ ማረጋገጫ የሚኖረው:: በመሆኑም የወንጀል ተከላካይ ጠበቃ የአንድ ደንበኛው ሞራላዊ ዋጋ ከሚያሳድርበት ጭንቀት በትክክልም ነፃ የመሆን ስሜት የሚሰማው:: (ይቀጥላል)::

# ፎሮፎር...

ነገር ግን ስርጭቱ ሰፊ ከሆነ ፀረ-ፈንገስ የሆኑ የሚዋጡ ክኒኖች ይሰጣሉ።

ሰንደቅ፡- ብዙዎች ፎሮፎርን ለመከላከል በየጊዜው መታጠብን ይመርጣሉ። ይሄ ደግሞ በተዘዋዋሪ የቆዳ ቅባትን በማስወገድ ለድርቀት ይዳርጋልና በምን ያህል ጊዜ ነው መታጠብ ያለብን?

ዶ/ር ድጋፌ፡- አንድ ሰው ፎሮፎር ካለበት የሚመቸውን ሻምፖ መጠቀም ይችላል። ነገር ግን በዚህ ፎሮፎርን ማከም አይቻልም። ሐኪም ቤት እስከሚሄድ ድረስ ግን በሳምንት አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ ብቻ ነው መታጠብ የሚያስፈልገው። ከዚህ በላይ ከሆነ ግን የቆዳ ድርቀትን ያመጣል። የቆዳ ድርቀት ካለ ደግሞ ለኢንፌክሽን እና ቁስለት ያጋልጣል። ሻምፖም ከሌለ በሳሙና ብቻ መታጠብ ያስፈልጋል። ከታጠብን በኋላ ግን ቅባት መጠቀም ያስፈልጋል። በቤት ውስጥ የሚዘጋጁ እንደ አቮካዶ ያሉ ቅባቶች ድርቀትን በጣም ይከላከላሉ። ቅቤም በህክምና የሚከለከል አይደለም። ነገር ግን መቀባት ያለብን ከታጠብን በኋላ ነው። እነዚሁ ታዲያ አጋዥ ህክምና እና ወደ ህክምና እስከምንሄድ ያግዙናል እንጂ ዘላቂ መፍትሔ አይደሉም።

ፎሮፎር እና የቆዳ ድርቀትንም መለየት ተገቢ ነው። ሰዎች ፎሮፎር የቆዳ ድርቀት ይመስላቸዋል። ድርቀት ከሆነ ፀጉር ብቻ ሳይሆን ሌሎችም የሰውነት ክፍሎች የሚደርቁበት ሁኔታ አለ። በተፈጥሮ ደረቅ ቆዳ ያላቸው ሰዎች ፀጉራቸው ብቻ አይደለም የሚደርቀው። የቆዳ ድርቀት ሲኖር መታጠብን በመቀነስ እና ከታጠብን በኋላ ቅባቶችን ማዘውተር ያስፈልጋል።

ሰንደቅ፡- ጨቅላ ህፃናት የችግሩ ተጠቂዎች እንደመሆናቸው ለእነርሱ ምን አይነት ጥንቃቄ መደረግ አለበት?

ዶ/ር ድጋፌ፡- ህፃናት በተወለዱ ሦስት ወይም አራት ወር አካባቢ የፀጉራቸው የፊተኛው አካባቢ ላይ ቢጫ ሆኖ የሚጋገር እድፍ የሚመስል ነገር አለ። ያ ነው ፎሮፎር የሚባለው። ሰዎች ያንን ለማከም በተለያዩ መንገዶች ሙከራ ያደርጋሉ። ይሄ በሽታ ከተወለዱበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት ወይም ዓመት ከስድስት ወር ቆይቶ የሚጠፋበት እድል አለ። ህፃናት ላይ ፎሮፎር ሲከሰት ያለውን ምልክት መለየት ያስፈልጋል። ፎሮፎሩ በህፃናት ፀጉር ላይ እና ፊት ላይ ሊወጣ ይችላል። ፊት ላይ ከሆነ ፊታቸው ይቀላል። ዳይፐር አካባቢ ሲሆን ሊቀላ እና ሊቆስል ይችላል። ፀጉር ላይ ሲሆን ግን ቢጫ ሆኖ የሚጋገር ነገር ይኖራል። እነዚያ ነገሮች ሲኖሩ ሐኪም ማማከር ያስፈልጋል። ለእነዚያ የሚያስፈልጉ ህክምናዎች ይሰጣሉ። በህፃናት ላይ የሚከሰተው ፎሮፎር ብዙም ምልክቶቹ በግልፅ የማይታዩ እና የማያሳክኩ ቢሆኑም ኢንፌክሽን ሊፈጥሩ ይችላሉ።

ሰንደቅ፡- ፎሮፎር ስር እየሰደደ ሲሄድ የሚያስከትላቸው ችግሮች ምንድን ናቸው?

ዶ/ር ድጋፌ፡- ብዙ ችግሮች ይኖራሉ። አንደኛ ፎሮፎር ፀጉር ላይ ሲቆይ የፀጉር መሰባበር እና መሳሳትን ያመጣል። ሁለተኛ ደግሞ የማሳከክ ሁኔታ ካለው ያን ማከክ ተከትሎ የቆዳ መቁሰል ያመጣል። በተጨማሪም እንደ ኤች አይ ቪ ያሉ ኢንፌክሽኖች ካሉ ከባድ የሆነ የቆዳ ችግር የሚያመጣበት አጋጣሚ አለ። ሰውነትን ከፀጉር ጀምሮ ጠቅላላ ሊያቆሳስል ወይም ሊልጥ የሚችልበት ሁኔታ አለ። ይህም ማለት የሰውነታችን 80 በመቶ የሆነው ቆዳ ተላጠ ማለት ነው። ስለዚህ ጉዳቱ እየሰፋ ይመጣል። እነዚህ ሰዎች ፎሮፎርን እንደ ከባድ ነገር ማየት አለባቸው። በሽታው የፀጉር ብቻ ሳይሆን የፊት እና የሌላ ሰውነት ስለሚሆን ቀጣይነት ያለው ክትትል ያስፈልጋል።

ሰንደቅ፡- በሀገራችን ፎሮፎርን እንደ በሽታ ቆጥሮ ወደ ህክምና የመሄድ ልምዱ ምን ይመስላል?

ዶ/ር ድጋፌ፡- ብዙዎች ይመጣሉ። ምናልባት አዲስ አበባ ዋና ከተማ ስለሆነች ይሆናል። ቢሆንም ብዙ ሰዎች ይመጣሉ። ነገር ግን በአብዛኛው የሚመጡት ሴቶች ናቸው። ወንዶች በሽታው ጠንከር ብሎ የመቁሰል ደረጃ ሲደርስ ይመጣሉ። ነገር ግን ያለው የበሽታ ስርጭት እና የሚታከሙት ሰዎች ቁጥር ላይወዳደር ይችላል። የበሽታው ስርጭት ሰፊ ነው፤ የሚመጡት ግን ሴቶች ብቻ ናቸው። በተለይ ህፃናት ላይ የግንዛቤ እጥረት ይመስለኛል ብዙም አይደለም።

# ቂርቆስ ክፍለ ከተማ...

**ይህንን በተመለከተ ተነሺ ነዋሪዎች በተደጋጋሚ ቅሬታ ሲያሰሙ ይሰማል። በዚህ በኩል ችግሮች ያሉ መሆኑን ወይዘሮ ወይንሸት ገልፀውልናል**



የይዞታ ባለቤትነታቸውን በሚገባ ሊያስረዱ የሚችሉ ሰነዶችን ያልያዙ ናቸው። ቀደም ባሉት ጊዜያት ለችግሮቹ መፍትሄ ለመስጠት የተለያዩ የማጣራት ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል።

የመልሶ ማልማት ሥራው ሲከናወን ግን ነዋሪዎችን ከቦታ የማንሳት ብሎም ካሳ የመክፈልና ምትክ ቦታ የመስጠት ሥራ ስለማከናወን ሰነድ አልባ ይዞታዎች የግድ ምላሽ እያገኙ መሄድ አለባቸው። እንደወይዘሮ ወይንሸት ገለፃ ነዋሪዎቹን በማንሳቱ ሂደት በቅድሚያ የማስተናገዱ ሥራ የሚሰራው በይዞታ ባለቤትነት የጠራ መረጃ የያዙ ነዋሪዎችን ነው። ከዚያ በመቀጠልም ያልተጣራ መረጃ ያላቸውን ነዋሪዎች በተመለከተ ግን መረጃቸውን በተለያየ መንገድ ለማጣራት የተቀመጡ አግባቦችን በመጠቀም መፍትሄ እየሰጡ የሚኬድበት አሰራር መኖሩን ኃላፊዋ ገፀውልናል።

መፍትሄ ይሰጣሉ ከተባሉት አሰራሮች መካከል አንደኛው አዲሱ የመሬት ምዝገባ ስርዓት ተግባራዊ እየሆነ በሚሄድበት ወቅት፤ በዚያው መጠን የእያንዳንዱ ይዞታ መረጃ አንድ በአንድ እየተጣራ የሚሄድበት አሰራር የሚኖር መሆኑ ነው። ይህም በሰነድ አልባ ቤቶች ላይ የሚታየውን ችግር በልማቱ ላይ መጓተት እንዳይፈጥር አንዱ አማራጭ መፍትሄ ነው ተብሏል። በዚህ ምላሽ የማያገኝ ከሆነ "ይዞታ" በመባል የሚጠራ አካል መፍትሄ እንዲሰጠው መረጃው የሚላክለት መሆኑን ገልፀውልናል። ጉዳዩ ከዚህ የሚያልፍ ከሆነ ደግሞ ነዋሪዎቹ አስተዳደራዊ መፍትሄ እንዲያገኙ የሚደረግ መሆኑን የገለፁት ኃላፊዋ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ግን ነዋሪዎች ማግኘት የሚገባቸውን ተገቢ ጥቅም አግኝተው እንዲነሱ የሚደረግ መሆኑ ተመልክቷል።

በመልሶ ማልማቱ ሂደት ነዋሪዎች የጋራ መኖሪያ ቤቶችን እንዲያገኙ ከተደረገ በኋላ በሳይቶቹ ላይ አስፈላጊው መሰረተ ልማት ተሟልቶ የማይገኝበት ሁኔታ አለ።

ይህንን በተመለከተ ተነሺ ነዋሪዎች በተደጋጋሚ ቅሬታ ሲያሰሙ ይሰማል። በዚህ በኩል ችግሮች ያሉ መሆኑን ወይዘሮ ወይንሸት ገልፀውልናል። ከችግሮቹ መካከል አንዱ በመሰረተ ልማት ላይ የሚሰሩ የተለያዩ የመንግስት መስሪያቤቶች በቅንጅት አለመስራት መሆኑ የተመለከተ ሲሆን፤ ለችግሩም መፍትሄ ለመስጠት የባለድርሻ አካላት የተለያዩ ውይይቶችን ካደረጉ በኋላ በውስጥ ለውስጥ መንገድና የውሃ መስመር ዝርጋታ ችግሮች የተፈቱ መሆኑን አመልክተዋል። ከመብራት ጋር በተያያዘ ትራንስፎርመሮች ከውጪ የሚመጡ በመሆናቸው፤ ከውጪ ገብተው እስኪተከሉ ድረስ የተወሰነ ጊዜ የሚወስድበት ሁኔታ መኖሩን ወይዘሮ ወይንሸት ገልፀውልናል። ከዚህ ውጪ ግን ነዋሪዎች መልሰው ኑሯቸውን በሚመሰርቱባቸው አካባቢዎች ተገቢው መሰረተ ልማት ሳይሟላላቸው ከአካባቢያቸው እንዳይነሱ አቋም የተያዘ ሲሆን የቂርቆስ ክፍለ ከተማም በዚሁ መልኩ እየሰራ መሆኑን ጨምረው ገልፀውልናል። በዚህም መሰረት በርካታ ነዋሪዎች ኮንደሚኒየም ቢወስዱም መሰረተ ልማቱ እስኪሟላላቸው ድረስ ያልተነሱበት ሁኔታ መኖሩን ወይዘሮ ወይንሸት ጨምረው ገልፀውልናል። ከመልሶ ማልመቱ ጋር በተያያዘ በአንዳንድ ነዋሪዎች ከሚነሱት ቅሬታዎች መካከል አንዱ ለከተማዋ ቅርሶች ተገቢውን ጥበቃ አይደረገም የሚል ነው። ወይዘሮ ወይንሸት በዚህ በኩል ስጋቱ ያላቸው ሰዎች ሊሰጉ የማይገባ መሆኑን ገልፀውልናል። እንደሳቸው ገለፃ በመልሶ ማልማቱ ሂደት ቤቶች ሲነሱ በመጀመሪያ ደረጃ በባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ቅርስ ተብለው የተመዘገቡ ንብረቶች አስቀድመው የሚለዩበት ሁኔታ አለ። ቅርስን በተመለከተም በማስተር ፕላኑ ጥናት የተለዩ ሲሆን ከዚህ ውጪ የሚነሱ ጥያቄዎች ካሉም ቢሯቸው ቆም ብሎ የሚያይበት ሁኔታ ያለ መሆኑንም ገልፀውልናል። በመልሶ ማልማቱ ሂደት የቀበሌና የግል ቤቶች ብቻ ሳይሆኑ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ሳይቀሩ የሚነሱ ሲሆን ለአንዳንድ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከወዲሁ ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ ደብዳቤ የተፃፈላቸው መሆኑን ወይዘሮ ወይንሸት ጨምረው ገልፀውልናል። አንዳንድ መስሪያ ቤቶች ደብዳቤው ከደረሳቸው በኋላ የራሳቸውን አማራጮች እያፈላለጉ መሆኑም ተመልክቷል።

በመልሶ ማልማቱ ሂደት የተነሺዎችን መረጃ መተንተን፣ ህዝብን ማወያየት፣ ተወካይን ማስመረጥ፣ የመግባቢያ ሰነድን ከተሺዎች ጋር የመፈራረም ስራዎች ተካተው የሚሰሩ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ የካሳ ክፍያን መፈፀም፣ የኮንደሚኒየም ቤቶችን ቁልፍ ለተነሺዎች ማስረከብና ምትክ የቀበሌ ቤት የመስጠት ስራም ይከናወናል። ከዚህም በተጨማሪ የመልሶ ማልማቱ ሂደት ለተነሺዎች ምትክ ቦታ ማስረከብን እንደዚሁም ያረጁ ቤቶችን ማፍረስና ማፅዳትን ያካትታል።



## ትዝብትን በጨዋታ

በአሸናፊ ደምሴ ......... demissieashenafi@gmail.com

# የአደባባይ ሰው

ከሰሞኑ በማህበራዊ ድረ-ገፆች "ከሴት ድፍረት" ጋር በተያያዘ የአንድ ዘማሪና ፓስተር ስም ክፉኛ ሲብጠለጠል ተመልክተናል:: እነሆ ዛሬ እኛ በትዝብታችን የነገሩን ጫፍና ጫፍ ይዘን ለመወናጨፍ ወይም እንዲህ ነው እንዲያ ነው ለማለት አይዳዳንም:: ዳሩ ግን የአደባባይ ሰው መሆን ምን ያህል ጥንቃቄ እንደሚሻ እንጨዋወታለን::

አንዳንዴ ሳስበው የአደባባይ ሰው ወይም ዝነኛ መሆን ማለት በብርና በነብር ወጥመድ ውስጥ እንደመታሰር ይመስለኛል:: አንዳንዶችም "የአደባባይ ሰው መሆን ማለት በተራራ አናት ላይ በመስታወት ቤት ውስጥ የመኖር ያህል ነው" ሲሉ አድምጠናል:: ፓውሎ ኩዌልሆ በፃፈው እና ወንድይራድ ገ/አምላክ "እነሆ በረከት" ሲል በተረጎመው መፅሐፍ ውስጥ የሚከተለውን ታሪክ እናገኛለን::

"ባልንጀሮቻችሁን ባያችሁ ቁጥር ራሳችሁን ተመልከቱ" አሉ ጃፓናዊው መምህር ኦካኩራ ካኩሶ ሲያስተምሩ:: አንደኛው ተማሪያቸውም "ግን እንዲያ ማድረጉ ራስ ወዳድነት አይሆንም" ሲል ጥያቄ አቀረበ:: ቀጠለናም "ምክንያቱም ሁልጊዜም የምናተኩረው በራሳችን ላይ ከሆነ ሌሎች ሰዎች የያዟቸውን መልካም እሴቶች ለማስተዋል እድል እናጣለን" አለ:: መምህሩም "አንተ እንዳልከው ሌሎች ሰዎች የያዟቸውን መልካም እሴቶች መመልከት የምንችል ቢሆን እንዴት ደግ ነበር? አሉ::

መምህሩ ቀጠሉና "እውነታው ግን አንተ ካልከው በተቃራኒው ነው:: ሌሎች ሰዎችን ባየን ቁጥር የምንመነጥረው እንከኖቻቸውን ነው:: የሌላኛውን ሰው ክፉ ገፅታ ለማግኘት የቻልነውን ያህል የምንባትለው ከእኛ የባሰ እንዲሆን ስለምንፈልግ ነው:: ስሜታችንን ሲጎዳን ይቅርታ ልናደርግለት የሚከብደንም የራሳችን ጥፋት ይቅር ያስብላል ብለን ስለማናምን ነው:: የምናውቃቸውን ጦረኛ ቃላት እያፈናጠርን እናቆስለዋለን:: ይህን የምናደርገው እውነቱን እያወራን መሆኑን እያወጅን ቢሆንም ቅሉ፤ እውነቱን ከራሳችን ለመደበቅ መጣር ነው የግብራችን ግብ:: ማንም ሰው ምን ያህል ተሰባሪ፣ ምን ያህል ስንጥቅጥቃችን የበዛ፣ ሽንቁራችን የጎደጎደ መሆኑን እንዳያይ ስንል በጣም ጠቃሚ እንደሆንን አድርገን እናስመስላለን:: ለዚያም ነው ወዳጅህን በፈረድህ፣ ሌላኛውን ሰውዬ በባየንክ ቁጥር በትክክል ፍርድ ላይ ያለኸው ራስህ መሆንህም ማወቅ የሚጠቅምህ" አሉት::

ከሁሉም ከሁሉም ግን ዝነኛ ስትሆን፣ ታዋቂ ስትሆን፣ ባለስልጣን፤ መሪ ስትሆን ገጣሚው እንዳለው ዝና ዘነዘናም ጭምር ነውና ጠንቀቅ ማለቱ አይከፋም:: አንዳንዴ ይባስ ብሎ የታዋቂው ሰው ውርደት የእርሱ ብቻ ሳይሆን የቤተሰቡ፣ የአካባቢው፣ የሚመራው ተቋም ወይም የአገሩ መዋረድና መሳት ሁሉ ተደርጎ ይታሰባል:: ያኔ ታዲያ ሁሉም ደብዳቤ ቃላትን ከአፎቱ እየመዠረጠ፤

"ወጣ ወጣና እንደሸምበቆ፣ ተንከባለለ እንደሙቀጫ" ይሉትን ገላጭ አነጋገር መሰካት ይጀምራል:: እኛም እንላለን፤"ከፍ ያለ ማሽላ አንድም ለወፍ፣ አንድም ለወንጭፍ፤ የተጋለጠ ነው" ቂ-ቂ-ቂ! እንዲህ ናትና ንግግር አትሉልኝም::

ከሰሞኑ የፌስ ቡክ ግርግር ሁለት ነገር ታዝበናል:: አንደኛውና ድፋሩ ነገር ሚዛን በሌላው ይህን የድፍረት ዜና ተመስርቶ የተለጠፈ ሀተታ እና ሀተታውን ተከትሎ የሚወረውር "ኮሜንት" የተሰኘ መዓት ድንጋይ "ወይ መሬት ያለ ሰውን" ይሉትን ተረት ያስታውሰኛል:: በነገራችን ላይ ከፀሐፊው አናት የሚወረወሩት ቃላት ወይም "ኮሜንት" የሚሰነዘርበትን ሰው ስነ-ልቦና የመጉዳታቸውን ያህል "የኮሜንት" ሰጪውንም ጭንቅላት በዚያው መጠን የምንለካበት ይመስለኛል:: የአንዳንድ ሰዎች ፍርድ ግርም የሚል ነው::

> አስቂኙ ነገር "የፈሰሰ ውሃ አይታፈስ" የሆነባቸው የፕሬዝዳንቱ ጠባቂዎች እርሳቸውን ማትረፍ ባይችሉ እንኳን በአካባቢው ከነበሩ ፎቶ አንሺዎች እጅ የውርደታቸውን ፎቶ ለማጥፋት ሲሟሟቱ እንደነበር ተሰምቷል። ምን ያደርጋል ታዲያ እድሜ ለቴክኖሎጂ ሙጋቤ ከወደቁበት ከመነሳታቸው በፊት በእኛ ሞባይል ፊት ላይ ምስሉን አግኝተነዋል

ያም ሆኖ "ከፍ ያለ ማሽላ፤ አንድም ለወፍ አንድም ለወንጭፍ" የተጋለጠ ነውና የአስተያየት ኀተራ ሆኖ መጠበቁ ግድ ነው:: ግድ ነው ስል ምን ትዝ አለኝ ግንድ የሚለው ቃል:: ግንድ ትዝ ሲለኝ ደግሞ፤ "የወደቀ ግንድ ምሳር ይበዛበታል" ይሉት አነጋገር ትዝ አለኝ:: እውነት አይደለም ታዲያ?

አንድ ሰው ተዋረደ የሚባለው የሚወርድበት ከፍታ ላይ፣ ስልጣን ላይ፣ ዝና ላይ፣ ሀብትና ሞገስ ላይ ሲገኝ ብቻ ነው:: አንድዬ ብቻ ወርደው ከሚያዋርዱ ክስተቶች ይጠብቀን አቦ:: ወርደው ከሚያዋርዱን ክስተቶች አንዱ ተበድሮ መመለስ አለመቻል ይመስለኛል:: አቤት አበዳሪያችንን ስናይ ድመት እንዳየች አይጥ ስንሯሯጥ ብንታይ፤ እራሱን የቻለ የሙሉ ሰዓት "ሆረር" እና "ኮሜዲ" ፊልም ይወጣዋል::

እዚህች'ጋ ሰሞኑን ከወደቻይና የተሰማች አንዲት ወሬ እንካችሁ:: የቻይናዋ ሁዋን ግዛት ፍርድ ቤት በፍትሃ ብሔር ክርክር ተሸንፈው ቅጣት የተወሰነባቸውን ግለሰቦች አልከፍል ባይነት ታዝቦ- ታዝቦ ሲያበቃ አንድ መላ ዘየደ:: የዘየደው መላ ምን መሰላችሁ? በውስጥ መስመር የቅጣት ብራችሁን ክፈሉ ሲባሉ እምቢ ማለታቸውን ተከትሎ ፎቶአቸውን የከተማዋ ህዝብ አብዝቶ በሚገለገልበት የባቡር ጣቢያ ግድግዳ ላይ መለጠፍ ነው:: ቂ-ቂ-ቂ:: ሰው እኮ የውርደት ፎቶው በአደባባይ ከሚለጠፍ በጫማ ጥፊ ሺህ ጊዜ ቢጠፈጠፍ የሚመርጥ ይመስለኛል::

ይሄኔ የተወሰነባቸውን የቅጣት ገንዘብ በጊዜውና ማንም ሳይሰማ መክፈልን የሸሹ ሁሉ ፎቷቸውን ከአደባባይ ለማስነሳት ሲሉ ተሯሩጠው ለመክፈል ይመጣሉ ብሏል ፍርድ ቤቱ:: ሁኔታውን በሚገባ ለታዘበው "የአህያ ስጋ አልጋ ሲሉት መሬት" እንዲሉ አይነት ይመስላል::

ከሰሞኑም ሌላ ወሬ ከወደዙምባቤ ተሰምቷል:: የ90 ዓመቱ አዛውንት መሪ ሮበርት ሙጋቤ ለህዝባቸው ንግግር ካደረጉበት መድረክ ሲወርዱ መሬት ከዳቸው:: በርግጥ ምናለ መሬት ከሚከዳቸው ስልጣን ቢከዳቸው ብለው ያሟቸው ብዙ ሰዎች አሉ:: አንዳንዶች ግን መሬት ከድቷቸው ይሁን ጠባቂዎቻቸው ረስተዋቸው አይታወቅም እንደፎጣ ተጣጥፈው ታይተዋል:: አስቂኙ ነገር "የፈሰሰ ውሃ አይታፈስ" የሆነባቸው የፕሬዝዳንቱ ጠባቂዎች እርሳቸውን ማትረፍ ባይችሉ እንኳን በአካባቢው ከነበሩ ፎቶ አንሺዎች እጅ የውርደታቸውን ፎቶ ለማጥፋት ሲሟሟቱ እንደነበር ተሰምቷል:: ምን ያደርጋል ታዲያ እድሜ ለቴክኖሎጂ ሙጋቤ ከወደቁበት ከመነሳታቸው በፊት በእኛ ሞባይል ፊት ላይ ምስሉን አግኝተነዋል:: እናላችሁ ጎበዝ የአደባባይ ሰው መሆን ብርም ነብርም አለውና አንድዬ እንደሸምበቆ ተሰቅሎ፣ እንደሙቀጫ ከመውረድ ይጠብቀን:: ያውም እንዲህ ባለውና የማህበራዊ ድረ-ገፆች በተስፋፉበት ጊዜ አያምጣው ማለት ይሻላል::

እናላችሁ ከፍታችንን፣ ዝናችንንና ስልጣናችንን ሁሉ ከምንሰራው ብልግና፣ ከምንሰራው መጥፎ ተግባር፣ ከምናሳየው ክስተት ሁሉ በማን አለብኝነት መታቀብ ባንችል እንኳን፤ በፌስ ቡክ አደባባይ እንዳንጋለጥ ጠንቀቅ ነው:: አሊያ ግን ነገራችን ሁሉ "ወጣ ወጣና እንደሸምበቆ ተንከባለለ እንደሙቀጫ" መሆኑ አይቀሬ ነው:: ለምን ቢሉ "ከፍታህ በጨመረ ቁጥር መውደቂያህ እየራቀህ ነው" እንዳሉ አስተዋዮች:: ቸር እንሰንብት::■

## ኪነጥበብ-ዜና

በአሸናፊ ደምሴ

## የፍቅረኞች ቀን በተለያዩ ዝግጅቶች ይከበራል

**■ በንግስተ ሳባ ሆቴልና በጨጨሆ የባህል ምግብ አዳራሽ ድግስ ተሰናድቷል**



በፍቅር ሙዚቃዎች፣ በኮሜዲያን ጭውውቶች፣ በግጥምና በፍቅር ገጠመኞች የታጀበና በአይነቱ ለየት ያለ ነው የተባለለት የፍቅረኞች ምሽት በንግስተ ሳባ ሆቴል የፊታችን ቅዳሜ የካቲት 7 ቀን 2007 ዓ.ም ከምሽቱ 12 ሰዓት ጀምሮ ይካሄዳል:: በዕለቱ ታዋቂ አርቲስቶች፣ ወጣትና በትዳር የቆዩ ጥንዶች ባለስልጣናትና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ይገኛሉ ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ዝግጅቱን ያሰናዱት አብርሃም ግዛው ኢንተርቴይመንትና ንግስተ ሳባ ሆቴል በጋራ መሆናቸው ታውቋል::

በተያያዘው "ፍቅርን በባህላችን" የተሰኘ መጠሪያ የተሰጠውና ባህላዊ የፍቅር አገላለጽና አልባሳት ይታዩበታል ተብሎ የሚጠበቅ ይህ ፍቅረኞች ቀን ዝግጅት ቅዳሜ ከ8 እስከ 10 ሰዓት በጨጨሆ የባህል ምግብ አዳራሽ ይካሄዳል:: በዝግጅቱ ላይ ለፍቅር ተምሳሌት መሆን የሚችሉ ባለትዳሮች የሚሸለሙ ሲሆን፤ የባህላዊ አልባሳት የሞዴሎች ውድድርም በዕለቱ ይከናወናል::

በተለያዩ ዘርፎች የሽልማት ፕሮግራም የሚጠበቅ ሲሆን፤ ምርጥ የፍቅር ዘፋኝ፣ የፍቅር ፊልም፣ የፍቅር ቴአትር፣ የፍቅር ተዋናይ፣ የፍቅር መጽሔትና የፍቅር ጋዜጠኛ በየዘርፉ ይሸለማሉ ተብሏል:: ዝግጅቱን ለመታደም 60 ብር መግቢያ ሲሆን ለጥንዶች ደግሞ 100 ብቻ ነው:: በልዩ ማዕረግ መታደም ለሚፈልጉም 150 ብር ስለመሆኑ እንዲሁም ዝግጅቱን ፍፁም አስፋ የማስታወቂያና ሚዲያ ኮሚኒኬሽን ከጨጨሆ የባህል ምግብ አዳራሽ ጋር በመሆን እንዳሰናዱት ነግረውናል::

## "ልባም ሴት" ፊልም ተመረቀ




የፍቺ መበራከት የበርካታ ቤተሰቦችን ህይወት ምን ያህል እንደሚያመሳቅል እና የሴትን ልጅ ጥንካሬ የሚተርከው "ልባም ሴት" የተሰኘ የቤተሰብ ድራማ ፊልም ባሳለፍነው ሐሙስ ጥር 28 ቀን 2007 ዓ.ም በሞናርክ ሆቴል በደማቅ ስነስርዓት ተመረቀ:: በመብረቅ ፊልም ፕሮዳክሽን የቀረበው ይህ ፊልም፤ ድርሰትና ዝግጅቱ የሀረገወይን አዱኛ መሆኑም ታውቋል::

"ልባም ሴት" ተሰርቶ ለመጠናቀቅ የ10 ወራትን ጊዜ የወሰደ ሲሆን የ1 ሠዓት ከ30 ደቂቃ ይወስዳል:: በውስጡም ደምስ በየነ፣ ሚኪ ተስፋዬ፣ ኪያ ታደለ፣ ሳሙኤል አዱኛ፣ ፍሬህይወት ከልክለው፣ ህፃን ልዑል አማኑኤልና 25 የሚደርስ አንጋፋና ወጣት ተዋንያን ተውነውበታል::

በዚህ ዓምድ ስር የሚወጡ ጽሁፎች የፀሐፊውን እንጂ የኤዲቶሪያሉን አቋም አያንፀባርቁም

# መድረክ፤ ገዢው ፓርቲ በአባሎቼ ላይ ወከባና እንግልት እያደረሰብኝ ነው አለ

*የአምስተኛው ዙር ሀገር አቀፍ የምርጫ እንቅስቃሴ በተጀመረበት በአሁኑ ወቅት በደቡብ ብ/ብ/ሕ እና በኦሮሚያ ክልሳዊ መንግሥታት የገዥው ፓርቲ ካድሬዎች የመድረክ አባላት፣ ደጋፊዎች ወይም የተቃዋሚ ቤተሰብ አባላት ናችሁ ባሉዋቸው ዜጎች ላይ በመብት ረገጣ፣ በማዋከብና በተለያዩ የማሰቃየት ተግባራት የሚፈጽሙትን በደሎች በማባባስና የመራጮችና ዕጩዎች ምዝገባዎችን የሚያስተጓጉሉ ሕገወጥ ተግባራት በመፈጸም ላይ ይገኛሉ።*

በዚሁም መሠረት፡-

ሀ. በደ/ብ/ብ/ሕ ክልል፡-

1ኛ፡- በቡርጂ ወረዳ በላድሼ ቀበሌ፡- ካድሬዎቹ የመድረክ አባላትና ደጋፊዎች ስለሆናችሁ የእርሻ መሬት አይገባችሁም ካሉዋቸው 10 አርሶ አደሮች ማለትም

1፡- አቶ ማርሳ ካሳ፣ 2፡- አቶ አይላ አዶ፣ 3፡- አቶ አድማሱ ጨቻ 4፡- አቶ ታምሩ ተስፋዬ 5፡- አቶ ሺኮ ጋሞ 6፡- አቶ መርከቤ መጮላ 7፡- አቶ ደጀኔ ዘውዴ 8፡- አቶ ጨብቂ ጠቆ 9፡- አቶ ተክሉ ታደሰ 10፡- አቶ በዙ ዱቤ ላይ የእርሻ መሬታቸውን ከመንጠቃቸውም በላይ በፍትሕ አካል ሳይወሰንባቸው በቀበሌው አመራሮች ብቻ ተወስኖባቸው እያንዳንዳቸው 200 ብር እንዲቀጡ የተደረገ ሲሆን፣ የተነጠቀባቸው የእርሻ መሬታቸውም 1፡- አቶ ዳዊት ጫካ 2፡- አቶ ሶዬ ጩርቂ 3፡- አቶ መኮንን ህርቦ 4፡-አቶ ደሳለኝ ማሬ 5፡- አቶ ቦጋሌ ቦኮ ለተባሉ የኢህአዴግ ካድሬዎች (ለቀበሌው የአመራር አባላት) ተሰጥቷል። ከላይ ከተራ ቁጥር 6 እስከ 10 የተጠቀሱት አርሶ አደሮች ደግሞ ለአራት ዓመታት ከኖሩበት መኖሪያ ቤታቸውም እንዲፈናቀሉ ተደርገዋል። አቶ ዮሴፍ ጣሰው የተባለው አባላችን ደግሞ በተመሳሳይ የእርሻ መሬቱን እንዲለቅና 200 ብር እንዲቀጣ የታዘዘ ሲሆን ትዕዛዙ ሕጋዊ አይደለም በማለቱ በፈጠራ ክስ እየከሰሱት መሆኑም ታውቋል።

2ኛ፡- ከላይ በተጠቀሰው ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት፡- አቶ መርከቤ መጮላ 2፡- አቶ ጨብቂ ጠቆ 3፡- አቶ ታደሰ ጣሶ የተባሉት አርሶ አደሮች በተመሳሳይ የመድረክ አባላትና ደጋፊዎች ናችው በሚል ውንጀላ ለከብቶቻቸው የገንዲ በሽታ መድኃኒት እንዳይሰጣቸው አቶ ሶዬ ጮርቂ የተባለው በቀበሌው የሚገኝ የአራሻ ቀጠና ሹም ከልክሎአቸዋል። በወቅቱም አቶ አብርሃም ሁቃ፣ አቶ አብርሃም አበበ እና አቶ ገብሬ ክንፉ የተባሉ የከብት ሕክምና ባለሙያዎች በሥፍራው እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም አቶ ታደሰ ጣሶ የተባለ አርሶ አደር ከኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ብድር እንዳያገኝ በቀበሌው ሊቀመንበር በአቶ ጂሎ አንዶ ተከልክለዋል።

3ኛ፡- የቀበሌው ነዋሪና ጠንካራ የመድረክ አባል በሆኑት በአቶ ለማ ባሆና ቤተሰባቸው ላይ ደግሞ የሚከተሉት በደሎች በቀበሌው ካድሬዎች አማካይነት ተፈጽሞባቸዋል።

አባታችው የተቃዋሚ ፓርቲ አባል ስለሆነ በሚል ሰበብ ሕፃናት ልጆቻቸው ክትባት እንዳያገኙ መሰረት በለጠ በሚባሉ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ተከልክለዋል።

በቀበሌው ውስጥ ሰፊ ያልታረሰ መሬት እያለ የተወሰነ የእርሻ መሬታቸውን ለትምህርት ቤት ሥራ እንፈልጋለን ብለው ከወሰዱባቸው በኋላ የተቀረውንም ሰብል እያለበት ለቆ እንዲወጣ ከማዘዛቸውም በላይ ለቤት መሥሪያ ያዘጋጁትን ፍልጥ ለሊት አቃጥለውባቸዋል።

ለወራጅና ለቋሚ የተዘጋጁ እንጨቶችንም አቶ አለሙ አዲሱ የተባለ የቀበሌው ታጣቂ የወሰደባቸው ሲሆን የቀበሌው አመራሮች የአቶ ለማን አቤቱታ አንቀበልም ብለው ግለሰቡ ወሰዶ እንዲያስቀር አድርገዋል።

በሌላ ሰው ቤት አስቀምጠው የነበሩትን 18 ኩንታል በቆሎም አቶ ሉጬ ጠቃሎ የተባለ አንድ የቀበሌው ነዋሪ በመኪና አስጭኖ ሲወስድባቸው ለቀበሌው አመራሮች አመልክተው ከተቃዋሚ አባል ጋር ድርድር የለንም በምል ሰሚ አጥተው ከመቅረታቸውም በላይ በተቃዋሚነታቸው ምክንያት ብቻ ማሕበራዊ እቀባ በቀበሌው በሚገኙ አራት ቀጠና ካድሬዎች ማለትም በአቶ ሪራ ዱኮ፣ በአቶ ጌታሁን ገሌ፣ በአቶ አዲሱ አይላ፣ በአቶ ጨሞ ጣቆ፣ በአቶ ካሳዬ ኩኤ፣ በአቶ ማርቆስ ማሌ፣ በአቶ ሉጬ አጋ፣በአቶ ሉጬ ዳይጎና በአቶ ጦንኤ ዳርጬ አማካይነት ተጥሎባቸው ከማሕበረሰቡ እንዲገለሉ ተወስኖባቸዋል።

*የመራጮች ምዝገባን በሚመለከትም በኦሮሚያ ክልል በበደሌ፣ በጀልዱና በወለጋቄለም በማሎግ ምርጫ ክልሎች ኮታችንን ስለጨረስን በማለት በርካታ የምርጫ ክልሉ መራጮች ሳይመዘገቡ እንዲመለሱ በማድረግ የሕዝቡን የመምረጥ መብት ሲያፍኑ ቆይተዋል።*

4ኛ፡- <u>በወላይታ ዞን</u> <u>በዳሞት ፉላሳ ወረዳ</u> ለ2007 ሀገር አቀፍ ምርጫ ዳሞት ጋሌ ቀጥር 2 የመድረክ የክልል ምክር ቤት ዕጩ ተወዳዳሪ ሆነው የተመዘገቡት የአቶ ዘለቀ ላጽሶ ከተወዳዳሪነት እንዲወጡ የተደረገባቸውን ግፊት ባለመቀበላቸው በግል ያለሙትን ደን በመጨፍጨፍና በማስፈራራት ተጽዕኖ እያደረጉባቸው ይገኛሉ። ከዚህም ሌላ በዚሁ የምርጫ ክልል ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የመድረክ ዕጩ ተወዳዳሪ የሆኑት አቶ ተፈሪ ሊሬ በኢህአዴግ በኩል ተወዳዳሪያቸው በሆኑት በአቶ ታደሰ መርድ ወንድም በአቶ ታከለ መርድ አማካይነት ከምርጫ ውድድሩ እራሳቸውን እንዲያገሉ፣ ከላገለሉ ግን ከሚሠሩበት የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ሥራቸው እንደሚባረሩ የማስፈራሪያ ዛቻ እንደደረሳቸው ለማወቅ ተችሏል።

ለ. በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት

1ኛ፡- በምዕራብ ወለጋ ዞን በሚገኙ የምርጫ ክልሎች እጩዎችን ለማስመዝገብ ከአዲስ አበባ የተንቀሳቀሰው ቡድን አባላት የሆኑትን 1- አቶ ሙላቱ ገመቹ የኦፌኮ ም/ሊቀመንበር፣ 2- ዶ/ር በላይነሽ ይሳሐቅ የኦፌኮ የሥራአስፈጻሚ ኮሚቴ አባል እና 3- አቶ እንዳለ ከበደ የምዕራብ ወለጋ ኦፌኮ የአካባቢ ኮሚቴ ሰብሳቢን ጥር 12 ቀን 2007 ዓ.ም ከደምቢዶሎ ወደ ግምቢ ሲንቀሳቀሱ አይራ ከተማ እንደደረሱ መሽቶባቸው መሠረት በሚባል ሆቴል ገብተው አልጋ ከያዙ በኋላ ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት ላይ በሆቴሉ ባለቤት ከአካባቢው ደህንነትና አስተዳደር ባለሥልጣናት በቴሌፎን እነዚህ ሰዎች ወንጀለኞች ስለሆኑ መኝታም ሆነ ምግብ እንዳይሰጣቸው የሚል ትዕዛዝ ስለደረሰን ልናሳድራችሁ አንችልምና ከሆቴሉ ለቃችሁ ውጡ፣ የከፈላችሁትን ገንዘብም ተቀበሉ፣ ተብለው ከሆቴሉ እንዲወጡ ተደርገው በመኪና ውስጥ ለማደር ተገደዋል። በነጋታው ሁኔታውን ለአይራ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት አስመዝግበው ወደ ዓለም ተፈሪ ከተማ ላሎና ዩብዶ ምርጫ ክልል ጽ/ቤቶች ዕጩዎችን አስመዝግበው ወደ ጉሊሶ ከተማ ደርሰው አረጋ ሽፈራው ሆቴል አልጋ ይዘው ሳለ ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት ላይ በርካታ የታጠቁ የፖሊስ አባላት ለፍተሻ ስለምንፈልጋችሁ መኝታ ቤታችሁን ክፈቱ በማለት ከፍተኛ ውዝግብ ከፈጠሩባቸው በኃላ ስለመሸ አሁን ልንከፍትላችሁ አንችልም፣ ስለዚህ ነገ ሲነጋ መጥታችሁ ሊትፈትሹን ትችላላችሁ፣ ካልሆነ ግን ሰብራችሁ መግባት ትችላላችሁ የሚል መልስ ሲሰጣቸው ከብዙ ውዝግብ በኋላ ትተው መሄዳቸው ታውቋል።

2ኛ፡- በኢሉባቦር ዞን በገቺ ቦረቻና በበደሌ ምርጫ ክልሎች እንዲሁም በወለጋ ዞን በሆሮ ጉዱሩ ጅማገነት ምርጫ ክልል የመድረክ ዕጩዎችን ላለመመዝገብ ቢሮ ዘግቶ በመውጣትና የትምህርት ማስረጃ ካላመጣችሁ በማለት ሲያጉላሉ ቆይተዋል። በምዕራብ ሸዋ ዞን በጀልዱ ምርጫ ክልል ደግሞ ከነጭራሹም የመድረክ ዕጩዎችን አንመዘግብም በማለት ሲያጉላሉ ቆይተዋል።

3ኛ፡- የመራጮች ምዝገባን በሚመለከትም በኦሮሚያ ክልል በበደሌ፣ በጀልዱና በወለጋቄለም በማሎግ ምርጫ ክልሎች ኮታችንን ስለጨረስን በማለት በርካታ የምርጫ ክልሉ መራጮች ሳይመዘገቡ እንዲመለሱ በማድረግ የሕዝቡን የመምረጥ መብት ሲያፍኑ ቆይተዋል።

4ኛ፡- በቡሌ ሆራ ወረዳ ምርጫ ክልል በመልካ ሶዳ ቀበሌ ቁጥር 1 ምርጫ ጣቢያ ደግሞ 57 ነዋሪዎች የተቃዋሚ ደጋፊ ስለሆናችሁ አንመዘግባችሁም ተብለው ስለተከለከሉ ሕገመንግሥታዊ መብታቸውን ለማስከበር ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት አቤቱታቸውን በማቅረብ ላይ ይገኛሉ።

በአሁኑ ወቅት ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አይነት በርካታ በደሎች በመድረክ አባላት ላይ በተለያዩ አከባቢዎች እየደረሱ ቢሆንም የመድረክ አባላት ሰላማዊ ትግላቸውን በቆራጥነት በመቀጠል የተጋረጡባቸውን መሰናክሎች በመቋቋም ዕጩዎችን በብዛት በማስመዝገብ ላይ ይገኛሉ።■

በዚህ ዓምድ ስር የሚወጡ ጽሁፎች የፀሐፊውን እንጂ የኤዲቶሪያሉን አቋም አያንፀባርቁም

# ታሪክ ሠሪ ታሪክ አሻጋሪ ሲያገኝ

በዳንኤል ክብረት
(www.danielkibret.com)

አበው ሲመርቁ "ወይ መልካም ልጅ፣ ወይ መልካም ደቀ መዝሙር ይስጥህ" ይላሉ:: የሚረከብህ ማለታቸው ነው:: ብዙ ታሪክ ሠሪዎች ታሪካቸውን የሚያስተላልፍላቸው አጥተው ሳናውቃቸው ቀርተናል:: ዛሬ ታሪካቸውን ከፍ አድርገን የምንናገርላቸው ታላላቆቻችን ታሪካቸውን የሚጽፍ፣ የሚጠብቅና ለትውልድ የሚያስተላልፍ ያገኙትን ነው:: ስማቸውን ሰምተን ታሪካቸው ያጣን፣ ሥራቸው ደርሶን ታሪካቸው የጠፋብን አያሌ ጀግኖች አሉን:: አንዳንድ አባቶች እንዲያውም ሰው ሲያጡ ታሪካቸውንና ቅርሳቸውን ለወንዞችና ለተራሮች በአደራነት ሰጥተው ነበር:: ይሄው በየዘመኑ እየተቆፈረ የሚወጣው ቅርስ መሬት አደራ የተቀበለችውን እያስረከበች ነው::


በዘመናዊ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ጎልተው ከሚጠቀሱት ታላላቅ ሰዎች መካከል ሊቀ ሊቃውንት መሐሪ ትርፌ አንዱ ናቸው:: የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ትርጓሜ (1948)፣ የሐዋርያት ሥራ ትርጓሜ፣ የሰባቱ መልእክታትን ትርጓሜ፣ የዮሐንስ ራእይን ትርጓሜ (1951) ያገኘነው በእርሳቸው ድካም ነው:: ከዚህም በተጨማሪ 'ርትዕት ፍኖት ዘባስልዮስ በባሕረ ጣና' (1948)፣ 'መጽሐፈ በቁዔት ዘጾም ወዘበዓል' (1946)፣ ቃለ ምዕዳን (1948)፣ መዝገበ ሃይማኖት (1950) ይህንንም መጻሕፍቱ በመጀመሪያ ገጻቸው 'ከሊቀ ሊቃውንት መሐሪ ትርፌ' በማለት ያስታውሱናል:: በዚያ ዘመን ጵጵስና ከሊቅነት በኋላ የሚመጣ መዓርግ ነበርና ቅዱስ ሲኖዶስ እኒህን ታላቅ ሊቅ ብጹዕ አቡነ ጴጥሮስ 'የጎንደርና የበጌምድር ጳጳስ' ብሎ በሐምሌ 12 ቀን 1952 ዓም ሾማቸው::

ብጹዕ አቡነ ጴጥሮስ ባገለገሉባቸው ቦታዎች በሦስት ነገሮች ይታወቃሉ:: የመጀመሪያው ሁለገቡ ሊቅነታቸው ነው:: የሀገር ቤቱን ትምህርት አንድ ሳያስቀሩ የተማሩ ናቸው:: በተለይም ደግሞ በሐዲስ ኪዳን ትምህርታቸው የሚጠቀሱ ሊቅ ናቸው:: ከሀገር ቤቱ ትምህርት ባሻገርም ወደ ግብጽ ተሻግረው ለሦስት ዓመታት ያህል ተምረው ተመልሰዋል:: የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት አንድን አባት 'ሊቅ' የምትለው በሦስት ነገሮች ነው:: በኦርቶዶክሳዊ ሕይወቱ፣ በኦርቶዶክሳዊ ትምህርቱ እና በኦርቶዶክሳዊ ድርሰቱ:: በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይህን ከሚያሟሉት መካከል አንዱ ናቸው - አቡነ ጴጥሮስ (1901- 1961 ዓም)::

አቡነ ጴጥሮስ የሚታወሱበት ሁለተኛው ነገር ያለማቋረጥ ዞረው በማስተማራቸው ነው:: የጎንደር ከተማ ለእርሳቸው የሥራ ማዕከል እንጂ የመቀመጫ ከተማ አልነበረም:: እንዲህ እንዳሁኑ መኪና ባልነበረበት ጊዜ እስከ ሱዳን ድንበር ድረስ በእግርና በበቅሎ ዞረው አጥቢያዎችን ጎብኝተዋል፣ አስተምረዋል፣ ችግሮችን በቅርበት ፈትተዋል፣ አጥምቀዋል፣ አብያተ ክርስቲያናትንም ተክለዋል:: በዚህ አገልግሎታቸው የተነሣም እጅግ አስቸጋሪ በሚባሉ ቦታዎች የሚኖሩ ምእመናን ሳይቀር ያስታውሷቸዋል::

በጎንደር ስለ አቡነ ጴጥሮስ ሐዋርያዊነት የሚነገር አንድ ትርክት አለ:: ብጹዕ አባታችን ያለ ዕረፍት ከጋራ ጋራ፣ ከቆላ ቆላ ሲዘዋወሩ የተመለከቱ አንድ አባት "አባታችን ምነው ጥቂት ቢቀመጡ" አሏቸው:: አቡነ ጴጥሮስም 'አይ አባታችን ሂዱ እንጂ መች ተቀመጡ ተባልን" ብለው መለሱላቸው ይባላል::

የአቡነ ጴጥሮስ ሦስተኛው መታወሻቸው ለገዳማዊ ሕይወት የነበራቸው ፍቅር ነው:: በተለይም ዐቢይ ጾምንና ጾመ ማርያምን ከከተማ ወጥተው በታላላቅ ገዳማት ማሳለፍ ይወዱ ነበር:: በመጨረሻው ሕይወታቸውም ዕለተ ዕረፍታቸውን የተረዱት ለዐቢይ ጾም ሱባዔ በማኅበረ ሥላሴ ገዳም በነበሩበት ጊዜ ነበር:: እዚያ በሱባዔ ላይ እንዳሉ ዕረፍታቸው መድረሱን ዐወቁ:: ወደ ጎንደር ተመልሰውም ሥራቸውን መልክ መልክ ማስያዝ ጀመሩ:: በተለይም በየሀገሩ ሲዘዋወሩ ያሰባሰቧቸው ታሪካዊ ቅርሶች ለትውልድ ይተላለፉ ዘንድ ሁነኛ ሰው እንደሚያስፈልጋቸው ዐወቁ::



*አባ ሙሉ ዐቅማቸው እየደከመ፣ እድሜያቸው እየጨመረ ሄዷል። ሁለት ጊዜ በአገልግሎት ላይ ወድቀው ዛሬ በክራንች ነው የሚጓዙት። የዛሬ 23 ዓመት በጎንደር ሳገኛቸው የነበራቸው የሃይማኖት ጽናትና ለሥራ ያላቸው ፍቅር ግን መቼም የሚሞት አይመስልም።*

አባ ሙሉ ሽታነህ በአቡነ ጴጥሮስ ዓይን የገቡት ያኔ ነበር:: አባ ሙሉ አቡነ ቀሲሳቸው ናቸው:: ዲቁናና ቅስና የሰጧቸው አቡነ ሚካኤል ሲሆኑ ቅኔና ቅዳሴን በሚገባ የተማሩ ሊቅ መነኮስ ናቸው:: ደርቡሽ ያጠፋውን ኳንትቻ አርባዕቱ እንስሳ እንደገና ነፍስ የዘሩበት፣ አለፋ ወረዳ ያለቺውን ቼባ ማርያም እንደገና የገነቡ፣ በጉሙዝ አካባቢ ሐዋርያዊ ተልዕኳቸውን የፈጸሙ፣ የአንጋራ መድኃኔዓለምን ገዳም የእህል ችግር ለመፍታት በሬ በታንኳ ጭነው በመውሰድ ተአምር የሠሩ፣ የአቡን ቤት ገብርኤልን ባለ ታላቅ ሕንጻ አድርገው ካህናቱን ከልመና ያወጡ፣ የአባ ዝንግሪትን ድልድይ አስገንብተው ሕዝብን ያገናኙ፣ ከወጣት ጋር ወጣት፣ ከዐዋቂ ጋር ዐዋቂ ሆነው ለስብከተ ወንጌል የሚጣደፉ የጎንደር ፈርጥ ናቸው::

ይህንን የገመገሙት፣ በመንፈሰ ትንቢትም የተመለከቱት አቡነ ጴጥሮስ ታሪካዊ ቅርሶቻቸውን በአደራ ለአባ ሙሉ አስረከቧቸው:: ይህንን አደራ አባ ሙሉ ለሃምሳ ዓመታት ጠብቀዋል:: መሣሪያ ይዘው በኃይል ሲያስፈራሯቸው፣ ገንዘብ ይዘው በወርቅ ሲደልሏቸው፣ ሥልጣንን ተጠቅመው አውጣ አግባ ሲሏቸው፣ ተንኮል ተጠቅመው ለስርቆት ሲያሸምቁባቸው፤ እርሳቸው ግን ጸሎት ከጥበብ ተጠቅመው ከግማሽ ምእት በላይ ጠብቀዋል:: ወርቅን በምናኔ ድል አድርገዋል:: ቅርሶቹን አልባሌ አስመስለው በማስቀመጥ ሌቦችን አታለዋቸዋል:: ቤታቸው የገባ ሰው እንኳን ቡትቶ የተከማቸ እንጂ ቅርስ የተቀመጠ መሆኑን አያውቅም ነበር:: እርሳቸውም ሌላ ቦታ እንዳስቀመጡት ነበር የሚያወሩት:: በሥልጣንና በኃይል የሚመጣባቸውንም በሱባዔ ያሳልፉታል::

አባ ሙሉ ዐቅማቸው እየደከመ፣ እድሜያቸው እየጨመረ ሄዷል:: ሁለት ጊዜ በአገልግሎት ላይ ወድቀው ዛሬ በክራንች ነው የሚጓዙት:: የዛሬ 23 ዓመት በጎንደር ሳገኛቸው የነበራቸው የሃይማኖት ጽናትና ለሥራ ያላቸው ፍቅር ግን መቼም የሚሞት አይመስልም:: ሰንበት ትምህርት ቤቶችን መርዳት፣ ወጣቶችን ማበረታታት፣ ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጉ ግንባታዎችን በታማኝነትና በጥራት መሥራት፣ ገዳማትና ችግረኞች እንዲረዱ ማድረግ፣ የተጣሉትን ማስታረቅ፣ ዛሬም አልጋ ላይ ሆነው እንደገና ሊሠሩት የሚመኙት አገልግሎታቸው ነው:: ሎሬት ጸጋየ ገብረ መድኅን በቴዎድሮስ ስንብት ላይ እንደገለጸው 'ከሠሩት ነገር ይልቅ ያልሠሩት ይቆጫቸዋል"::

አሥራ አንድ ሊቃነ ጳጳሳት በጎንደር ተፈራርቀዋል:: አባ ሙሉ ግን ሳይቀየሩ ሁሉንም አገልግለዋል:: የሁሉን ታሪክ ለግማሽ ምእተ ዓመት ሰብስበዋል:: ወደ ፈጣሪያቸው ከመሄዳቸው በፊት ግን እነዚያን በተጋድሎ ያቆዩዋቸውን የወርቅ፣ የብርና የነሐስ ንዋያተ ቅድሳት፣ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ቅርሶች ለትውልድ ማስረከብ ፈለጉ:: የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ኤልሳዕም ሐሳባቸውን ተቀብለው ለቅርሶቹ ማስቀመጫ ሙዝየም እንዲሠራ አደረጉ:: ሙዝየሙም ጥቅምት 26 ቀን 2003 ዓም አስመረቁ:: አባ ሙሉም ለሃምሳ ዓመታት የጠበቋቸውን ቅርሶችም ሕዝብና መንግሥት ባለበት፣ ቤተ ክህነትና ምእመናን በተገኙበት በይፋ ለትውልድ አስረከቡ::

ታሪክ ሠሪ እንዲህ ያለ ታማኝ ታሪክ አሻጋሪ ሲያገኝ ምንኛ ዕድለኛ ያደርገዋል:: አባ ሙሉን ያብዛልን::■

በዚህ ዓምድ ስር የሚወጡ ጽሁፎች የፀሐፊውን እንጂ የኤዲቶሪያሉን አቋም አያንፀባርቁም

# የምርጫ አፈፃፀም ዋና ዋና ድንጋጌዎች

**አቶ አስመላሽ ወ/ስላሴ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሕግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ናቸው። ከምርጫ ሕጎች ጋር በተያያዘ በአንድ ወቅት ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው በሚል እንደሚከተለው ቀንጭበን አቅርበነዋል።**

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

በኢፌዴሪ ሕገመንግስትና በተሻሻለው የምርጫ ሕግ ውስጥ ተደንግገው ከሚገኙ ዴሞክራሲያዊ መብቶች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ። የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በማንኛውም ሁኔታ ልዩነት ሳይደረግባቸው በቀጥታ እና ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ስልጣናቸውን በተግባር ላይ ማዋል እንደሚችሉና ማንኛውም ዜጋ በቀጥታና በነፃነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካኝነት በሕዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ እና በማንኛውም የመንግስት ደረጃ በየጊዜው በሚካሄድ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ እንደዚሁም የመደራጀት፣ ሀሳብን በነፃ የመግለጽ፣ የአቤቱታ የማቅረብና ፍትሕ የማግኘት መብት አለው።

## የምርጫ መርሆዎች

የኢትዮጵያ የምርጫ ስርዓት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሚወዳደሩ ዕጩዎች መካከል አብላጫ ድምጽ ያገኘ ዕጩ አሸናፊ የሚሆንበት ስርዓት ነው። ምርጫ ሁሉ አቀፍ፣ ቀጥተኛ፣ በምስጢር ድምጽ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነፃነት የሚገልጽበት እና ያለምንም ልዩነት በእኩል ሕዝባዊ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት፣ እያንዳንዱ መራጭ የሚሰጠው ድምጽ እኩል እንደሆነ እና ማንኛውም መብቱ በሕግ ያልተገደበ ኢትዮጵያዊ ለመምረጥም እንደማይገደድ የሚሉት በሕግ ማዕቀፎቻችን ከተደነገጉ የምርጫ መርሆዎች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው።

በመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲ ስርዓት የሚመረጥ መንግስት ሕጋዊነት የሚመሰረተውም በሚከተሉት መርሆዎች ላይ ነው። ማለትም መራጮች በምርጫ ዘመቻው አማካኝነት ስለ ፓርቲዎች ፖሊሲ እና ስለዕጩዎች ባህሪ የተሟላ መረጃ ሲሰጣቸውና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ሲያደርጉ እና መራጮች ያለማንም ጣልቃ ገብነት፣ ያለፍርሃት፣ ያለ ተጽዕኖ፣ ያለጫና ወይም ከጉቦ ነፃ በሆነ መልኩ በነፃነት ድምጽ መስጠት ሲችሉ ነው። የምርጫ አስፈፃሚዎችም ለሕገመንግስት ታማኝ፣ ከፖለቲካ ድርጅት ወገንተኝነት የፀዱ፣ እንደሁኔታው የሙያ ብቃት ያላቸውና በመልካም ስነምግባራቸው የሚታወቁ መሆንም አለባቸው።

## የመራጮች አመዘጋገብ ስርዓት

የመራጮች ምዝገባ የዴሞክራሲያዊ የምርጫ ሂደት አንዱ አካል በመሆኑ በጥንቃቄ መከናወን ይገባዋል። ምክንያቱም የምዝገባ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ዜጎች ብቻ መመዝገባቸውን እና መምረጣቸውን ማረጋገጥ ያስችላል። ምን ያክል ሰው እንደሚመርጥ በማወቅ ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ ይረዳል። አንድ መራጭ ወይም ዕጩ በአንድ ምርጫ ጣቢያ ወይም ክልል ከአንድ ጊዜ በላይ መመዝገብ እንደዚሁም ከአንድ ምርጫ ጣቢያ ወይም ክልል ውጭ መመዝገብ እንደማይችልና በመራጭነት መመዝገብ የሚችለው በግንባር በመቅረብ ብቻ መሆኑ ዜጎች ያለ አድልዎ እና ያለ እንግልት ተመዝግበው ተወካዮቻቸውን በመምረጥ በመንግስት ስልጣን እንዲሳተፉ ማድረግ ተገቢ መሆኑን በመገንዘብ ግልጽ መስፈርትና አሰራር በተሻሻለው የምርጫ ሕግና በቦርዱ መመሪያ ቁጥር 2/2001 ዓ.ም በመዘርጋት በሀገራችን እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል።

## መስፈርቶች

በተሻሻለው የምርጫ ሕግ መሰረት በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያበቁ መመዘኛዎች የሚከተሉት ናቸው። ማለትም በምዝገባው ዕለት ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ እና በዕጩነት ሊቀርብበት በፈለገበት የምርጫ ክልል ቢያንስ 6 ወር የኖረ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በመራጭነት ሊመዘገብ ይችላል። እድሜው 18 ስለመሆኑ ጥርጣሬ ሲኖር በቤተሰቡ፤ እነሱ ከሌሉ ደግሞ የሰውየውን እድሜ በሚያውቅ ሌላ ሰው ምስክርነት ምዝገባ ሊካሄድ ይችላል። ይሁን እንጂ በአዕምሮ ሕመም ምክንያት የመወሰን አቅም የሌለው መሆኑ የሚታወቅ፤ በፍርድ የተወሰነበትን የእስራት ቅጣት በመፈፀም ላይ ያለ ወይም የመምረጥ መብቱ በሕግ የተገደበበት ሰው በመራጭነት ሊመዘገብ አይችልም።

## የምዝገባ ጊዜ

ማንኛውም የመራጮች ምዝገባ የሚካሄደው በምርጫ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ቅዳሜና እሁድን እንደዚሁም የበዓላት ቀናትን ጨምሮ በመንግስት የሥራ ሰዓት ይሆናል። ቦርዱም ምዝገባ ከሚጀምርበት ዕለት ከአስራ አምስት ቀን በፊት ጀምሮ በተከታታይ የምዝገባ ቀናትን ህዝቡ እንዲያውቅ ማድረግ ይጠበቅበታል። በወጣው መደበኛ የምዝገባ ጊዜ ውስጥ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሳይመዘገቡ የቀሩ ወይም በመራጭነት መመዝገብ መብቱ ላይ ተቃውሞ ቀርቦበት በፍርድ ቤት ውሣኔ እንዲመዘገብ የተወሰነለት ሰው ቦርዱ በሚያወጣው ልዩ የምዝገባ ጊዜ በመራጭነት ሊመዘገብ ይችላል። የምርጫ ጣቢያዎችም እነዚህን መራጮች በልዩ የምዝገባው ጊዜ ውስጥ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ቦታ መመዝገብ አለባቸው።

## የምዝገባ ቦታ

የመራጮች ምዝገባ መካሄድ ያለበት በተቋቋሙ የምርጫ ጣቢያዎች ብቻ ይሆናል። ከዚህ ውጭ ቤት ለቤትም ሆነ በሌላ ቦታ እየተንቀሳቀሱ መመዝገብ አይፈቀድም። ይሁን እንጂ በተፈቀዱ ተንቀሳቃሽ የምርጫ ጣቢያዎች እየተዘዋወሩ መመዝገብ ይቻላል። ማንኛውም የምዝገባ ቦታ ምቹ አማካይና በግልፅ ሊለዩ የሚችሉ መሆን አለባቸው በወቅቱም ለህዝብ ይፋ ሊደረጉ ይገባል። በአንድ ቦታ መኖር ያለበት አንድ የምርጫ ጣቢያ ብቻ ነው። ይህም ጣቢያ ማስተናገድ ያለበት የመራጮች ብዛት ከአንድ ሺህ መብለጥ የለበትም። በጣቢያው የሚኖረው መራጭ ከተጠቀሰው ቁጥር የሚበልጥ መሆኑ ከተገመተ የምርጫ ጣቢያው በሁለት ተከፍሎ ምዝገባው መካሄድ ይኖርበታል። እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ጉዳይ መኖሪያ ቤቶች፣ ወታደራዊ ካምፖች፣ ሆስፒታሎች፣ የእምነት ቦታዎች (መስጊዶችና ቤተክርስቲያኖች)፣ የፖሊስ ጣቢያዎችና የፖለቲካም ሆኑ የሃይማኖት ድርጅቶች ህንፃዎች የመራጮች ምዝገባ ቦታ ሆነው ማገልገል እንደማይችሉ ነው።

## በምዝገባ ቦታ መገኘት ያለባቸው ሰዎች

የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ የተወዳዳሪ ፓርቲዎች ወይም የግል ዕጩ ተቀማጭ ወኪሎች እና የህዝብ ታዛቢዎች በምዝገባ ቦታ መገኘት ይጠበቅባቸዋል። እነዚህ ሰዎች እንዲገኙ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ከመራጮች ምዝገባ ዕለት ከአስር ቀናት በፊት በጽሑፍ ሊያሳውቃቸው ይገባል። ይሁን እንጂ እንዲገኝ የተነገረው ሰው ባለመገኘቱ ምክንያት የመራጮች ምዝገባ ሂደት አይቋረጥም።

## ለምዝገባ ስለሚደረግ ቅድመ ቁሳቁስ

የምርጫ ጣቢያዎች ለመራጮች ምዝገባ በሚያመች መልኩ በምርጫ አስፈፃሚዎች ሊዘጋጁ ይገባል። መግቢያና መውጫው የተለያየ የመመዝገቢያ ቤት፣ ድንኳን ወይም ዳስ ማዘጋጀት እና የህዝብ ታዛቢዎችም ሆኑ የዕጩ ወኪሎች ተመዝጋቢዎች ወደ ምዝገባ ቦታ ሲገቡና ከዚያ ሲወጡ በግልጽ ለመታዘብ እንዲችሉ አቀማመጣቸው ፊት ለፊት መሆን አለበት። ለመራጮች ምዝገባ የሚያገለግሉ መዝገባች፣ የመራጮች መታወቂያ ካርዶች እና ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶች ሠነዶች በወቅቱና በበቂ መጠን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ስለሆነም የምዝገባ ቁሳቁሶች ከዕጩዎች ምዝገባ እለት ከ8 ቀን በፊት ምርጫ ጣቢያ ማድረስ፣ በሕጋዊ የመረካከቢያ ቅፅ መረከብ ምቹ ቦታ በማዘጋጀት በጥንቃቄ ማስቀመጥና ተገቢውን ጥበቃ ማድረግ ያስፈልጋል።

ሌላው ጉዳይ ምዝገባ ከመካሄዱ በፊት በቅድሚያ ሁለት የመራጮች መዝገብ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። በአንደኛው መዝገብ ሽፋንም ላይ መዝገብ ቁጥር አንድ፤ በሌላኛው ደግሞ መዝገብ ቁጥር ሁለት ተብሎ ይፃፋል። በሁለቱም መዝገብ ሽፋንም ላይ የክልሉ የዞኑ፣ የምርጫ ክልሉ እና ጣቢያው እንደዚሁም የወረዳውና የቀበሌው መጠሪያዎች እና አመተምህረት ይመዘገባል።

በውስጥ ገጾቻቸው ላይ ደግሞ ተከታታይ የገጽ ቁጥሮች በጥንቃቄ መሙላት ይገባል። መራጩ ሕዝብ የመራጮች ምዝገባ የሚካሄድበትን ጊዜና ቦታ ከምዝገባው ቀን ቀደም ብሎ እንዲያውቅ ማድረግ ማስታወቂያዎችንና ፖስተሮችን ግልጽ በሆኑ ቦታዎች ላይ መለጠፍ እንደዚሁም መዝጋቢዎችን በጥንቃቄ መመልመልና ስለመራጮች ምዝገባ አፈፃፀም ማሰልጠን ይገባል።

## የአመዘጋገብ ሂደት

የመዝገብ ሹሙ መመዘኛውን የሚያሟላ ሰው በግንባር ቀርቦ ማስረጃውን ሲያሳይ መመዝገብ ይጠበቅበታል። ለምዝገባ የቀረበ ሰው እንደ አመጣጡ ተራውን ጠብቆ ከመዝገብ ሹሞቹ አንደኛው ፊት መቅረብና መዝጋቢዎች የሚጠይቁትን የማንነት ጥያቄ በትክክል መመለስ አለበት። መዝጋቢውም የሚመዘግበውን መረጃ ድምፁን ከፍ አድርጎ በመናገር መሙላት አለበት። ተመዝጋቢውም በመራጮች መዝገቡ ላይ በስሙ ትይዩ ፊርማውን እንዲያስቀምጥ ይደረጋል፤ የመራጮች ካርድም ይሰጠዋል፤ የድምፅ መስጫውን ቦታ፣ ቀንና ሰዓት እንደዚሁም ምን አይነት ሠነዶችን ይዞ መምጣት እንደሚገባው እና ስንት ዕጩ ተወዳዳሪ መምረጥ እንደሚችሉ ለተመዝጋቢው ማሳወቅ ያስፈልጋል። ለምዝገባ የሚቀርቡ መራጮች በሁለቱም መዝገቦች ላይ ተመጣጥነው እንዲመዘገቡ ማድረግ ይገባል። እድሜያቸው የገፋና አካል ጉዳተኞች ተራ ሳይጠብቁ ለምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በማሳወቅ ቅድሚያ ተሰጥተቸው መመዝገብ አለባቸው። ዓይነ ስውራን እና አቅም የሚያንሳቸው ሰዎች በአካል ተገኝተው በሚመረጡት ሰው በመረዳት መመዝገብ የሚችሉ ሲሆን፤ ረዳቶቻቸውም ኢትዮጵያዊ የሆነ፣ እድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነው እና ዕጩ ወይም የዕጩ ተወካይ ያልሆነ ሰው መሆን ይኖርበታል።

## ለምዝገባ የሚቀርቡ የማንነት ማስረጃዎች

አንድ ዜጋ የነዋሪነት፣ የሰራተኛነት ወይም የተማሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት በማቅረብ በመራጭነት መመዝገብ ይችላል። እነዚህ ማስረጃዎች በሌሉበት ወቅት አንደ መንጃ ፈቃድ፣ የመኖሪያ የምስክር ወረቀት ወይም ከውትድርና የተገለለበት ሠነድ ወይም የስደተኞች ካርድ የሥራ ፈቃድ ወይም የጡረታ አበል መታወቂያ በመሳሰሉት የመለያ ማስረጃዎች መመዝገብ ይቻላል። የቀረበው መታወቂያ ወይም ፓስርርት ጊዜ ያለፈበት ቢሆንም ለመመዝገብ ያገለግላል። እነዚህ ማስረጃዎች በማይኖሩበት ወቅትም መዝጋቢዎች መራጩን ለይተው የሚያውቁ ከሆነ ወይም የህዝብ ታዛቢዎች በሚሰጡት ምስክርነት ምዝገባ ሊከናወን ይችላል። በዚህ ወቅት የሚያዘው የምስክርነት ቃል ጉባኤ የህዝብ ታዛቢዎች እና የምርጫ አስፈፃሚዎች ፊርማ ተረጋግጦ ሊቀመጥ ይገባል።

## ስለመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ

የምዝገባ መታወቂያ ካርድ የሚሰጠው በሕግ መሠረት ለተመዘገበ ሰው ነው፤ በድምጽ መስጫው ዕለትም ካርዱን ይዞ ወደ ምርጫ ጣቢያ መምጣት አለበት። ካርዱ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት መራጭ ከድምጽ መስጫው ዕለት በፊት ባሉት የሥራ ጊዜያት ወይም በድምፅ መስጫው ዕለት ለምርጫ ጣቢያው ሊያመለክት ይችላል። ጥያቄውም ከታመነበትም ጉዳዩን በቃለ ጉባዔ በመያዝ በምትኩ ሌላ ካርድ ሊሰጠው ወይም ድምጽ ሊሰጥ እንደሚችል ሊታወቅ ይገባል።

## የመራጮችን መዝገብ ስለመዝጋት

የመራጮች ምዝገባ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ በየዕለቱ የመጨረሻው ተመዝጋቢ ቁጥር በተዘጋጀው ቅጽ መዝገቡን መዝጋት ያስፈልጋል። መሙላትና በቀፁም ላይ መዝጋቢዎች እና የህዝብ ታዛቢዎች ሊፈራረሙበት ይገባል።

መደበኛው የምዝገባ ጊዜ ሲጠናቀቅም ምዝገባ መቆም አለበት። በመቀጠልም በየመዝገቦቹ ውስጥ በመጨረሻ ተራ ቁጥር ከተመዘገበው ስም ቀጥሎ ያሉትን መስመሮች በዚግዛግ መስመር መዝጋትና የተመዘገቡ መራጮች ማጠቃለያ ድምርን ማስፈር እንደዚሁም በእያንዳንዱ መዝገብ ላይ የተመዘገበውን ጠቅላላ መራጭ በጾታ መለየትና በሚዘጋጀው የመተማመኛ ሠነድ ላይ ማስፈር ያስፈልጋል። የተዘጋጀው መዝገብና የሚያዘው ቃለጉባኤም በምርጫ አስፈፃሚዎችና በህዝብ ታዛቢዎች መፈረም አለበት። በተዘጋው መዝገብም ላይ ምዝገባ አይካሄድም፤ ምንም አይነት ነገር አይፃፍም።

## መዝገቦችን ለህዝብ ይፋ ስለማድረግ

የመራጮች ምዝገባ እንደተጠናቀቀ የመራጮች መዝገብ በምርጫ ጣቢያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ቅዳሜና እሁድን እንደዚሁም የበዓላት ቀናትን ጨምሮ ለተከታታይ 5 ቀናት በመንግስት የሥራ ሰዓታት ይፋ ወጥቶ ህዝብ በግልጽ እንዲያየው መደረግ አለበት። ህዝቡ በግልጽ እንዲያይ የሚያደርጉትም መዝገቡን በኃላፊነት የተረከቡት የመዝገብ ሹሞች ናቸው።

ማንኛውም የማንነት ማስረጃውን የያዘ ሰው የሚፈልገውን መረጃ ለማየት ሲጠይቅ የመዝገብ ሹሙ የተጠየቀውን መረጃ ከዕጩዎች መዝገብ ላይ ማሳየት አለበት። ጥያቄ አቅራቢውም መዝገቡን በእጁ

*መንካት ወይም መዝገቡ ላይ መፃፍ ወይም ምልክት ማድረግ አይችልም። የመራጮች መዝገብ ህዝብ በግልጽ እንዲያየው ሲደረግ የምርጫ ጣቢያው የህዝብ ታዛቢዎች፣ የፓርቲዎች ወይም የግል ዕጩ ወኪሎች እና የምርጫ አስፈፃሚዎች እንዲገኙ ማድረግ ያስፈልጋል።*

*የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ግልጽ የሚሆንባቸው ቀናት ሲጠናቀቅም፣ መዝገቡ ለ5 ተከታታይ ቀናት ህዝቡ እንዲያየው ስለመደረጉ፣ ህዝቡ መዝገቡን ሲመለከት የጠየቀውን መረጃ ይዘት እና መረጃውን ስለማግኘቱ እና አለማግኘቱ እንደዚሁም ለአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበ አቤቱታ ካለ እና ስለተሰጠው መልስ በአጭሩ መዝገቡ ለሕዝብ ግልፅ በሆነባቸው ቀናት የተገኙና ያልተገኙ አካላትን የሚመለከቱ መረጃዎችን የያዘ መተማመኛ ይዘጋጃል። የህዝብ ታዛቢዎች እና የምርጫ አስፈፃሚዎች ከተፈራረሙበት በኋላ በሰነድነት ይያዛል።*

**ከመዝገብ ስለመሰረዝ**

*ማንኛውንም ተቃውሞ የቀረበበት ሰው በአዕምሮ ህመም ምክንያት ለመወሰን ብቃት የሌለው ወይም በማጭበርበር የተመዘገበ ወይም ተፈርዶበት በማረሚያ ቤት የታሰረ ሆኖ ከተገኘ ከመዝገብ ይሰረዛል። ለመሰረዙ የቀረበበትን ማስረጃን በመጥቀስ ቃለጉባዔ መያዝ እና ቃለጉባኤው ላይ የምርጫ አስፈፃሚዎች እና የህዝብ ታዛቢዎች እንዲፈራረሙበት ማድረግ ያስፈልጋል። አንድን ሰው ከመራጮች መዝገብ ላይ መሠረዝ የሚቻለው እስከ ድምጽ መስጫው እለት ድረስ መሆኑ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል።*

**የተከለከሉ ተግባራት**

*መመዘኛዎን የማያሟላ ነገር ግን በመራጭነት ተመዝግቦ የተገኘ ሰው፣ ወይም አለማሟላቱን እያወቀ መዝግቦ የተገኘ ወይም ለምዝገባ ከተወሰነው ቀንና ሰዓት ውጭ ምዝገባ ከናወነ የመዝገብ ሹም እንደዚሁም ከአንድ ጊዜ ቦታ በላይ ወይም ተመዝግቦ የተገኘ እና የምዝገባ መታወቂያ ካርድ ይዞ የተገኘ ሰው፣ ለመመዝገብ ሲል የሀሰት መግለጫ ወይም ማስረጃ የሰጠ ወይም ያቀረበ፣ መራጮች እንዳይመዘገቡ ያስፈራራ ወይም የሁለት መረጃ ወይም ማስረጃ የሰጠ፣ የመመዝገብ ወይም አቤቱታ የማቅረብ መብትን የከለከለ ወይም የገደበ ወይም ያወከ፣ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድን የለወጠ፣ የሰረዘ፣ የደለዘ ወይም በሕጋዊ መንገድ የተመዘገበን መራጭ የሰረዘ ወይም የደለዘ እና በምርጫ ጣቢያው ኃላፊው ከተመደቡ መዝጋቢዎች ውጪ የመራጮች ምዝገባ ያከናወነ ሰው በሕግ ተጠያቂ ይሆናል። በየደረጃው ያሉ የምርጫ አስፈፃሚ የመራቾች ምዝገባ እንቅስቃሴን አስምልክቶ ለበላይ የምርጫ አስፈፃሚ አካላት ሪፖርት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።*

**የዕጩዎች አመዘጋገብ ስርዓት**

*ግልፅና ከመሰናክል የፀዳ የዕጩዎች ምዝገባ ዕጩዎች መብታቸውን ያለ አድልዎ በእኩልነት በመጠቀም ጠንካራ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ አማራጭ ሃሳቦችን ለህዝብ እንዲያቀርብና የዴሞክራሲ ባህልን እንዲያገለብቱ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ እንዲካሄድ ይረዳል። ለዚህም ነው በሀገራችን የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎች ማለትም የተሻሻለውን የምርጫ ህግና የቦርዱ መመሪያ ቁጥር 1/2001 ተዘጋጅተው በስራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።*

**መስፈርቶች**

*በተሻሻለው የምርጫ ሕግ መሰረት የሚወዳደርበትን ብሔራዊ ክልል / የአካባቢውን/የሥራ ቋንቋ የሚያውቅ፣ በምዝገባ ዕለት እድሜው 21 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነው፣ በሕግ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብቱ ያልተገደበ እና ቦርዱ የሚያወጣውን የምርጫ ስነምግባር ደንብን ተቀብሎ ለመፈረም ፈቃደኛ የሆነ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በዕጩነት ሊቀርብ ይችላል።*

*ከምርጫው ዕለት አስቀድሞ በምርጫ ክልሉ ውስጥ በመደበኛነት ለሁለት ዓመት የኖረ ወይም የትውልድ ቦታው በዕጩነት ሊቀርብበት በፈለገበት የምርጫ ክልል ውስጥ ከሆነ ወይም ከተማው ወይም ወረዳው ከአንድ በላይ የምርጫ ክልሎች የሚያቅፍ ከሆነ፣ በከተማው ወይም በወረዳው ውስጥ ለሁለት ዓመት በመደበኛነት የሰራ ከሆነም በዚያው ከተማ ወይም ወረዳ በፈለገው የምርጫ ክልል ዕጩ ሆኖ መቅረብ ይችላል። ይሁን እንጂ ይህ መመዘኛ በስራ ወይም በትምህርት ምክንያት ከምርጫ ክልል ውጭ የነበረን ሰው ወይም ከዚህ በፊት በምርጫ ክልሉ ተመርጦ በመስራት ላይ ያለን ሰው አይመለከትም። በግሉ ዕጩ ሆኖ ለመቅረብ የሚፈልግ ሰው ደግሞ የመምረጥ መብታቸወ በሕግ ካልተከለከሉ የምርጫ ክልሉ ነዋሪዎች ውስጥ ከአንድ ሺ የማያንስ ድጋፍ ፊርማ ማቅረብ ይጠበቅበታል። ይሁን እንጂ ለወረዳ ወይም ለከተማ አስተዳደር ወይም ለቀበሌ ም/ቤት ምርጫ በግል የሚቀርብ ዕጩ የሚያሰባስበው የድጋፍ ፊርማ ብዛት እንደቅደም ተከተላቸው ከ200፣ ከ200 ወይም ከ50 የሚያስ መሆን አለበት።*

**የድጋፍ ፊርማ መስጠት ስለሚችል ሰው፣**

*ኢትዮጵያዊ ዜጋ፣ በምርጫ ክልል ቢያንስ ለስድስት ወራት በነዋሪነት የቆየ፣ እድሜው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነው፣ የመምረጥ መብቱ በህግ ያልተከለከለ፣ የአእምሮ በሽተኛ ያልሆነ ፣ እና የእስራት ቅጣት በመፈፀም ላይ የሚገኝ የህግ እስረኛ ያልሆነ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሆነ ሰው ነው ለግል ዕጩ ተወዳዳሪ የድጋፍ ፊርማ መስጠት የሚችለው። አንድ ሰው ለውድድር ከቀረቡት መቀመጫዎች በላይ ለሆኑ ዕጩዎች የድጋፍ ፊርማ መስጠት አይችልም። የግል ዕጩውም ያሰባሰበው የድጋፍ ፊርማ ትክክለኛነት በአሰባሰበበት የቀበሌ አስተዳደር በኩል አድርጎ ለሚወዳደርበት ለምርጫ ክልሉ ማቅረብ ይኖርበታል።*

**ስለዕጩ አቀራረብ እና አመዘጋገብ፣**

*መመዘኛዎችን የሚያሟላ ማንኛውም በግሉ በዕጩ ተወዳዳሪነት ሊቀርብ ይችላል። ይሁን እንጂ አንድ ፓርቲ ዕጩ ማቅረብ የሚችለው በቦርዱ በሕግ የተመዘገበ ከሆነ ነው። እያንዳንዱ ድርጅት ፓርቲውን ወክለው የሚወዳደሩ ዕጩዎችን ዝርዝር በሚወዳደሩበት የምክር ቤት ምርጫ በመለየት በጊዜ ሰሌዳው መሰረት ለቦርዱ ወይም ለምርጫ ክልል ጽህፈት ቤት ማሳወቅ አለበት። የዕጩዎችን ዝርዝር የሚያሳውቀው የፓርቲው የበላይ አመራር ወይም በዞኑ ወይም በወረዳው የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር ሲሆን በፊርማው እና በድርጅቱ ማህተም የተረጋገጠ ሊሆን ይገባል። የፓርቲው ዕጩ በፓርቲው መወከሉን እና በዕጩነት ለመቅረብ ማስማማቱን የሚገልፅ ማስረጃም ተያይዞ መቅረብ አለበት።*

*በዕጩነት መመዝገብ የሚቻለው በግንባር በመቅረብ ነው። ይሁን እንጂ በፓርቲ የቀረበ ዕጩ በግንባር ቀርቦ መመዝገብ ካልቻለ ዕጩውን ያቀረበው ፓርቲ ወይም ወኪሉ በሚቀርበው የማንነት ማስረጃ ዕጩው ሊመዘገብ ይችላል፡፤*

*አንድ ሰው ዕጩ ሆኖ መቅረብ የሚችለው በአንድ የምርጫ ክልል ብቻ ነው። ከአንድ በላይ በሆኑ የምርጫ ክልሎች በዕጩነት ተመዝግቦ የተገኘ ሰው ከሁለቱም የምርጫ ክልሎች ከውድድሩ ይሰረዛል። ከአንድ የምርጫ ክልል በላይ በዕጩነት መመዝገቡ ከምርጫው ውጤት በኋላ የታወቀ በምርጫ ያሸነፈ ዕጩ ውጤቱ ተሰርዞ ድጋሚ ምርጫ ይካሄዳል።*

**ዕጩ ስለመለወጥና ስለመተካት፣**

*ፓርቲ ያቀረበውን ዕጩ መለወጥ ወይም መተካት ይችላል። ዕጩው በራሱ ፈቃድ የለቀቀበት ፓርቲ የዕጩ ምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ እስከሚያልቅ ድረስ በሌላ ዕጩ ሊተካ ይችላል። ዕጩው እራሱን ያገለለው በዕጩ ምዝገባ የጊዜ ሰሌዳው የመጨረሻ ቀን ከሆነ ፓርቲው ዕጩው ራሱን ካገለለበት ቀን ጀምሮ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ሌላ ዕጩ ሊያቀርብ ይችላል።*

*ዕጩ የሞተበት ፓርቲ የዕጩ ምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ሌላ ዕጩ ሊተካም ይችላል። የዕጩ ምዝገባ ጊዜ ካለፈ በኋላ ዕጩው የሞተበት የፖለቲካ ድርጅት ከድምፅ መስጫው ዕለት ከ15 ቀን በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ሌላ ዕጩ ሊተካ ይገባል። ይህንን ካላደረገ ምርጫው ባሉት ዕጩዎች መካከል በተያዘለት ጊዜ ውስጥ ይከናወናል። አንድ የፓርቲ ዕጩ የምርጫው ቀን ከመድረሱ አስራ አምስት ቀናት ባነሰ ጊዜ ውስጥ የሞተ እንደሆነ በምርጫ ክልሉ የሚካሄደው ምርጫ ቆሞ ዕጩ የሞተበት ድርጅት ዕጩ እንዲተካ ተደርጎ ሌላ ምርጫ ይካሄዳል። ይሁን እንጂ ፓርቲው ተተኪ ዕጩ ማቅረብ እንደማይችል በፅሁፍ ከገለፀ ምርጫው በቀሩት ዕጩዎች መካከል በተያዘለት ጊዜ ይካሄዳል። እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ጉዳይ የምርጫ ጊዜ የተለወጠ እንደሆነ በምርጫ ክልሉ ተመዝግበው የነበሩ መራጮች ሌላ ምዝገባ ሳይካሄድ፣ የሞተው ዕጩ በቻ ተተክቶ ምርጫው የሚካሄድ መሆኑን ነው። የድምፅ መስጫው ቀን ሁለት ቀን እስኪቀረው ድረስ እራሱን ለማስተዋወቅ ቅስቀሳ ማድረግ የሚችለውም የተተካው ግለሰብ ብቻ ነው።*

**በተሻሻለው የምርጫ ሕግ መሰረት የሚወዳደርበትን ብሔራዊ ክልል /የአካባቢውን/ የሥራ ቋንቋ የሚያውቅ፣ በምዝገባ ዕለት እድሜው 21 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነው፣ በሕግ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብቱ ያልተገደበ እና ቦርዱ የሚያወጣውን የምርጫ ስነምግባር ደንብን ተቀብሎ ለመፈረም ፈቃደኛ የሆነ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በዕጩነት ሊቀርብ ይችላል**

**ወደሌላ ምርጫ ክልል ተዛውሮ ስለሚወዳደርበት ሁኔታ፣**

*አንድ ዕጩ በዕጩ ምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ከአንድ የምርጫ ክልል ወደ ሌላ የምርጫ ክልል ተዛውሮ መወዳደር ይችላል። የዝውውሩ ጥያቄም በፓርቲው ማህተምና አመራር ፊርማ ወይም በግል ዕጩው ፊርማ በተረጋገጠ ደብዳቤ የሚዘዋወርበትን የምርጫ ክልል በመግለፅ ዕጩው ተመዝግቦበት ለነበረው የምርጫ ክልል መቅረብ ይኖርበታል። ዕጩውም ተሰጥቶት የነበረውን የዕጩነት መታወቂያ ተመዝግቦበት ለነበረው የምርጫ ክልል ይመልሳል፣ ከመዝገብም ላይ ይሰረዛል። ይህንኑ የሚያረጋግጥ የጽሁፍ ማስረጃም ይሰጠዋል። ይህንንም በማሳየት የዝውውር ጥያቄ ባቀረበበት ቦታ በዕጩነት ሊመዘገብ ይችላል።*

**ስለ ዕጩዎች መታወቂያ ካርድ**

*መመዘኛውን የሚያሟሉ ዕጩዎች በዕጩ መመዝገቢያ ቅጽ ላይ ስማቸው እንዲሰፍር ከተደረገና ያቀረበው ጉርድ ፎቶ በካርዱ ላይ ከተለጠፈ በኋላ የዕጩነት መታወቂያ ካርድ እንደሁኔታው በምርጫ ክልሉ ጽ/ቤት ማህተምና ኃላፊ ፊርማ ወይም በቀበሌው ምርጫ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ፊርማ ብቻ ተረጋግጦ ይሰጣቸዋል። ለቀበሌ ምክር ቤት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ይህ ካርድ ላይሰጥ ይችላል። የፓርቲ ዕጩዎች የዕጩነት መታወቂያ ካርድ ለዕጩዎቹ ወይም ለፓርቲው ተወካዮች መረከባቸውን እንዲያረጋግጡ በማድግ ሊሰጥ ይችላል። የፈረሙበት መተማመኛም በማስረጃነት እንዲቀመጥ ማድረግ ያስፈልጋል። የሚሰጠው ካርድ የሚያገለግለው የምርጫ ውጤት በቦርዱ ይፋ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ ብቻ ሲሆን፣ ጊዜው እንዳለቀም ዕጩዎች ወዲያውኑ ለምርጫ ክልሉ ወይም ለቦርዱ ዋና ጽህፈት ቤት ማስረከብ አለባቸው።*

**ዕጩዎችን ለሕዝብ ስለማሳወቅ፣**

*የምርጫ ክልሉ በጊዜ ሰሌዳው መሠረት የዕጩዎቹን ስም ዝርዝር በቀረቡበት የምርጫ አይነት በመለየት ለምርጫ ክልሉ ሕዝብ ይፋ ማድረግ ይጠበቅበታል። አስፈላጊ መረጃዎችን በተዘጋጀው የማሳወቂያ ቅጽ ላይ በመሙላት ሕዝቡ በሚበዛበት እና በሚዘዋወርበት እንደዚሁም በምርጫ ክልሉ ጽህፈትቤት ቅጥር ግቢ እና በየምርጫ ጣቢያዎች በፊርማና በማህተም በማረጋገጥ መለጠፍ ያስፈልጋል። ለወረዳ፣ ለከተማ፣ ለክፍለ ከተማና ለቀበሌ ምክር ቤቶች ምርጫ የዕጩ ማስታወቂያ ፖስተር በምርጫ ጽህፈት ቤት ኃላፊው ፊርማ ብቻ ተረጋግጦ ሊለጠፍ እንደሚችል ግንዛቤ ሊያዝ ይችላል።*

*ከቀረበው ጽሁፍ መረዳት የሚቻለው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የመምረጥና የመመረጥ መብቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ግልጽ፣ ዝርዝርና በአለማቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው መስፈርቶችና አሰራሮች መደንገጋቸውን እና መብቶቹን በሰራ ላይ ለማዋል በሚደረገው እንቅስቃሴ ምንም አይነት ተፅዕኖ ወይም እንቅፋት ሊደረጉበት እንደማይገባ ነው። የምርጫ እቅስቃሴዎችን ለመምራት የወጡት አለም አቀፍ የምርጫ መርሆዎችን አካተው የያዙት እነዚህ የሕግ ማእቀፎች የተለያየ አመላከት ያላቸው ፓርቲዎች ያለ አድልዎና ያለመሰናክል ተመዝግበው ህግና ስርዓትን አክብረው በምርጫፉ እንዲሳተፉ፣ አላማቸውን በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ ለመራጩ ሕዝብ እንዲገልፁ፣ መራጩ ሕዝብም ያለ ውጣውረድና መሰናክል በመራጭት በመመዝገብና በመረጃ ላይ በመመስረት ፈቃዱን በነፃነት በመግለፅ ወኪሎቹን እንዲመርጥ የሚያስችሉ ናቸው።*

**የዕጩዎች የመመዝገቢያ ቦታ እና ጊዜ፣**

*ለህዝብ ተወካዮች፣ ለክልል እና ለዞን ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ምዝገባ የሚካሄደው በምርጫ ክልል ነው። ለወረዳ፣ ለከተማ እና ለክፍለ ከተማ ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ የዕጩዎች ምዝገባ የሚካሄደው በቀበሌ ውስጥ ከሚገኙት የምርጫ ጣቢያዎች መካከል ቀደም ሲል የቀበሌ የምርጫ ጽህፈት ቤት ሆኖ እንዲያገለግል በተመደበው የምርጫ ጣቢያ ይሆናል። የዕጩዎች ምዝገባ የሚካሄደው በወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም የበዓላትን ቀናትን ጨምሮ ዘወትር በመንግስት የሥራ ሰዓት ይሆናል። ይሁን እንጂ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ቦርዱ ተጨማሪ ወይም ልዩ የዕጩዎች የመመዝገቢያ ጊዜ ሊያመቻች ይችላል።*



# የአይቮሪኮስት የአፍሪካ ዋንጫ ቁልፍ ሰው አሰልጣኝ ኸርቨ ሬናርድ

■ *ከቁሻሻ ጠራጊነት ወደ ዋንጫ ሰብሳቢነት*

በቆንጂት ተሾመ

አይቮሪኮስት ከ23 አመት በኋላ የአፍሪካ ዋንጫን በማንሳት የድል ታሪኳን አድሳለች። ለዚህ አዲስ የድል ምዕራፍ መገለጥ ደግሞ ቁልፍ ሚና ከተጫወቱት መካከል የቡድኑ አሰልጣኝ ኸርቨ ሬናርድ ዋነኛው ናቸው። ከዛምቢያ ብሔራዊ ቡድን ጋር እ.ኤ.አ. የ2012 የአፍሪካ ዋንጫን ያነሱት አሰልጣኙ አሁን ደግሞ የ2015 የአፍሪካ ዋንጫን ከኮትዲቯር ጋር ደግመው ወስደዋል። በዚህም ከሁለት የተለያዩ የአፍሪካ ብሔራዊ ቡድኖች ጋር የአፍሪካ ዋንጫን በሶስት አመት ውስጥ ያነሱ የመጀመሪያው አሰልጣኝ አድርጓቸዋል። ከዝሆኖቹ የድል ታሪክ ጋር ተያይዞም ስማቸው በስፋት የሚነሳ ሆኗል።

በዲድየር ድሮግባ የሚመራው ወርቃማ ትውልድ ማሳካት የተሳነውን የአፍሪካ ዋንጫ አሸናፊነትን በእሳቸው የአሰልጣኝነት ዘመን ተሳክቶለታል። ቡድኑ በአፍሪካ ዋንጫው የመጀመሪያ የምድብ ማጣሪያ ጨዋታ ያሳየው አቋም ለዋንጫ እንዲታጭ አላደረገውም ነበር። በውድድሩ ከፍተኛ የአሸናፊነት ግምት የተሰጠውን የአልጄሪያ ቡድንን 3ለ1 ካሸነፈ በኋላ ግን የብዙዎችን እምነት አግኝቷል። በፍጻሜ ጨዋታውም ከጋና ጋር በመደበኛና ጭማሪ ሰአት ያለግብ ተለያይቶ ወደ መለያ ምት ሲያመራም በቀደመው ታሪኩ ምክንያት እድለኛ እንደማይሆን ተገምቶ ነበር። በተለይም ሁለት መለያ ምቶችን መሳቱን ተከትሎ ዋንጫውን ጋና እንደምትወስደው ነበር የታሰበው። ከዚህ በፊት የአይቮሪኮስት ብሔራዊ ቡድን በ2012 የአፍሪካ ዋንጫ ፍጻሜ በመለያ ምት በዛምቢያ ተሸንፈው ዋንጫ ማጣታቸው የሚታወስ ነው።

አሁን ግን የዝሆኖቹ ቡድን በመለያ ምት የመሸነፍ ታሪኩን አልደገመም። ቡድናቸው በመለያ ምት 2 ለ 0 እየተመራ እንኳን እንደሚያሸንፍ እምነት እንደነበራቸው አሰልጣኙ ኸርቨ ሬናርድ ተናግረዋል።

የቡድናቸውን የሜዳ እንቅስቃሴ ቆመው በመከታተል







የሚታወቁት ፈረንሳዊው አሰልጣኝ ከአሁኑ የኮትዲቯር ቡድን ጋር ዋንጫ የማንሳታቸው ዋነኛ ሚስጥር በቡድኑ ላይ ለውጥ ማድረጋቸው ነበር። ይህ ለውጥ ስመጥር ተጫዋቾችን ከአዳዲሶቹ ጋር በማዋሀድ የተጀመረ እንደሆነም ተናግረዋል። እንደ ዊልፍሬድ ቦኒና ግራድል ያሉ ተጫዋቾች እምቅ አቅማቸውን እንዲያወጡ ሰፊ እድል ተሰጥቷቸዋል። በቡድኑ ውስጥ የቆዩ እንደ ያያ ቱሬና ጀርቪንሆ ያሉ ተጫዋቾችም ራሳቸውን ትልቅ ግምት ሰጥተው እንዳይጫወቱ አድርገዋል።

"የአሁኑ የአይቮሪኮስት ቡድን የተለየ የሚያደርገው በጣም የሚያዳምጥ መሆኑ ነው" የሚሉት አሰልጣኙ "በዱባይ በነበረን የዝግጅት ቆይታ ቡድኑን ለማዋሀድና የአንድነት ስሜት ለመፍጠር የቻልንበት ጊዜ በጣም ጠቅሞናል" ብለዋል።

የ46 አመቱ ፈረንሳዊ አሰልጣኝ በአሁኑ የኮትዲቯር ቡድን ውስጥ የፈጠሩት ሌላው አዲስ ነገር ሁሉም የቡድኑ ተጫዋች እኩል ሚና እንዳለው እንዲያስብ ማድረጋቸው ነው። በዚህም ቡድኑ ለዋንጫ እንደበቃ የቡድኑ አባላት ተናግረዋል። የቡድኑ አምበል ያያ ቱሬ ምስክርነቱን ሲሰጥ፤ "ያለ አሰልጣኛችን ሬናርድ ምንም ነገር አናሸንፍም ነበር። የእሱ መኖር ሁላችንም እኩል አስተዋጽኦ እንድናበረክት አድርጓል። እኔም ብሆን ጥሩ ካልተንቀሳቀስኩ ከቡድኑ እንደሚቀንሰኝ ነግሮኝ ነበር። እሱ በጣም ምርጥ ሰው ነው"

የእድል ገዴ ነው የሚሉትን ከበረዶም በላይ የነጣ ሸሚዝ በመልበስ የሚታወቁት አሰልጣኝ ኸርቨ ሬናርድ ዛሬ በአፍሪካ ምድር ስኬታማ ይሁኑ እንጂ በልጅነታቸው ዝቅተኛ በተባለው ቁሻሻ ጠራጊነት ስራ በመስራት ያሳለፉ ናቸው። በታዳጊነት ዘመናቸው ኑሯቸውን ለመደጎም ሲሉ በጽዳት ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው የተለያዩ የህንጻ ክፍሎችን ቆሻሻ በመሰብሰብ ሰርተዋል። በዚህ ስራም ለስምንት አመታት ሲያሳልፉ ህይወት በጣም ፈታኝ እንደነበረች ያስታውሳሉ። ከስራቸው ባሻገርም እግር ኳስን በመጫወት አሳልፈዋል።

ኸርቨ ሬናርድ የእግር ኳስ ህይወታቸውን በተከላካይ መስመር በመጫወት ነው የጀመሩት። ኤ ኤስ ለተባለው የፈረንሳይ ክለብ በመሰለፍ የፕሮፌሽናል ተጫዋችነት ህይወትን የጀመሩ ሲሆን፣ ለ ስታድ ደ ቫለሩስና ድራጉግናን ለተባሉ የሀገሪቱ ክለቦችም ተጫውተዋል። በ1983 እስከ 1998 ድረስ በተጫዋችነት ቆይተዋል። ይሁንና ጥሩ እግር ኳስ ተጫዋች መሆን እንደማይችሉ ሲረዱ ወደ አሰልጣኝነት ማምራትን መርጠዋል።

በፈረንሳይ አማተር ክለቦችን በማሰልጠን የአሰልጣኝነት ሙያን የጀመሩት ኸርቨ ሬናርድ የመጀመሪያ ቅጥራቸው እ.ኤ.አ. በ2001 ለድራጉግናን ክለብ ነበር። በ2004 የእንግሊዙን ካምብሪጅን ያሰለጠኑ ሲሆን ከ2005 እስከ2007 ደግሞ ኤ ኤስ ቼርን በዋና አሰልጣኝነት አገልግለዋል።

የሬናርድ ዝና የጎላው በ2008 የዛምቢያ ብሔራዊ ቡድንን በዋና አሰልጣኝነት በያዙ ወቅት ነበር። ቀድሞ በጋና ብሔራዊ ቡድን ውስጥ ምክትል አሰልጣኝነት አብረው በሰሩት ሌላው ፈረንሳዊ አሰልጣኝ ክላው ለ ሮይ ጥቆማ ነበር የዛምቢያ ቡድንን የተረከቡት። አንጎላ ባስተናገደችው በ2010 የአፍሪካ ዋንጫም የዛምቢያ ቡድንን ለሩብ ፍጻሜ አድርሰዋል። ወዲያውም የአንጎላ ቡድንን ለአንድ አመት ለማሰልጠን ተስማሙ። ከአንጎላ ጋር ያልተሳካ አመት ካሳለፉ በኋላ ወደ ፈረንሳይ አቅንተው በሊግ ዋን (Lige 1) የሚጫወተው ሶቻክስ ክለብን ለሁለት አመት አሰልጥነዋል።

በፈረንሳዩ ክለብ ጥሩ የሚባል ጊዜን ባለማሳለፋቸው ዳግም ብሔራዊ ቡድን ማሰልጠን ይሻላል በማለት የክለቦችን ጥሪ አልሰማም አሉ። በድጋሚም ዛምቢያ ያቀረበችላቸውን ጥያቄ ተቀብለው ወደ አፍሪካ መጡ። ኢኳቶሪያል ጊኒና ጋቦን በጥምረት ባዘጋጁት የ2012 የአፍሪካ ዋንጫ ላይም ለአሸናፊነት ያልተጠበቀውን የዛምቢያን ቡድን ይዘው ተገኙ። ለፍጻሜም ደርሰው ኮትዲቯርን በመለያ ምት አሸንፈው የአፍሪካ ዋንጫን አነሱ።

ከዛምቢያ ጋር ዋንጫ ካነሱ ከሶስት አመት በኋላ በኢኳቶሪያል ጊኒ ኮትዲቯርን ይዘው ሻምፒዮን የሆኑበትን ሚስጥር ሲጠየቁ "ምናልባት እዚህ (ኢኳቶሪያል ጊኒ) አንዳች ነገር ይኖር ይሆናል" በማለት ከሳቅ ጋር ምላሻቸውን ሰጥተዋል። "ከሁሉም በላይ ግን የብሔራዊ ቡድኑ የአንድነት መንፈስ ዋጋ ሊሰጠው ይገባል" ሲሉም የአሸናፊነታቸውን ምክንያት ተናግረዋል።

በልጅነታቸው ቁሻሻ በመሰብሰብ ኑሯቸውን ይደጉሙ የነበሩት ሬናርድ አሁን ግን ዋንጫ በመሰብሰብ ሀብትና ዝናን አካብተዋል። ከኮትዲቯር ጋር ዋንጫ ካነሱ በኋላም ተፈላጊነታቸው ጨምሯል። በከፍተኛ ገንዘብ ሊቀጥሯቸው ከሚፈልጉ ብሔራዊ ቡድኖች ግብጽ ቀዳሚዋ መሆኗ ተሰምቷል። እሳቸው ግን "አሁን ከኮትዲቯር ጋር ደስታዬን የማጣጥምበት ጊዜ ላይ ነኝ። ሌላ ቡድን ለማሰልጠን አልተነጋገርኩም" ሲሉ ምላሻቸውን ሰጥተዋል።■

## በካፍ የክለቦች ሻምፒዮና

# ቅዱስ ጊዮርጊስ በባህር ዳር ስታዲየም ይጫወታል

የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን የክለቦች ሻምፒዮናና የኮንፌዴሬሽን ዋንጫ የማጣሪያ ጨዋታዎች በሳምንቱ መጨረሻ በተለያዩ የአፍሪካ ከተሞች ይካሄዳሉ። በካፍ ሻምፒዮና የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ሻምፒዮኑ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ በኮንፌዴሬሽን ዋንጫ ደግሞ ደደቢት ኢትዮጵያን ወክለው ይወዳደራሉ።

በክለቦች ሻምፒዮና ቅዱስ ጊዮርጊስ ከአልጄሪያው ኤል ኢውማ ጋር በቅድመ ማጣሪያ ውድድር የተመደበ ሲሆን፣ የመጀመሪያ ጨዋታውን ከሜዳው ውጪ ያደርጋል። ከሁለት ሳምንት በኋላ የመልስ ጨዋታውን ደግሞ በባህር ዳር ስታዲየም እንደሚያደርግ ታውቋል።

ቅዱስ ጊዮርጊስ የባህር ዳር ስታዲየምን ለመጠቀም የፈለገው ስታዲየሙ አለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀና ኢንተርናሽናል ጨዋታዎችን ለማስተናገድ የሚችል በመሆኑ ነው። የአዲስ አበባ ስታዲየም በአሁኑ ወቅት የአፍሪካ የወጣቶች አትሌቲክ ሻምፒዮናን ለማስተናገድ እድሳት ላይ ይገኛል። ሜዳው የሚያስተናግዳቸው ጨዋታዎች ሁሉ ወደ አበበ ቢቂላ ስታዲየም መዞራቸው ይታወቃል። ጊዮርጊስ በካፍ ሻምፒዮና ከአልጄሪያው ክለብ ጋር የሚኖረውን የመልስ ጨዋታ በአበበ ቢቂላ ስታዲየም የባህር ዳር ስታዲየምን ነው የመረጠው።

የባህር ዳር ስታዲየም ካለፈው አመት ጀምሮ አገልግሎት መስጠት የጀመረ ሲሆን አለምአቀፍ ጨዋታዎችን ለማስተናገድ የሚችል መሆኑ ተነግሯል። ስታዲየሙ በካፍ ሰዎች የተጎበኘ ሲሆን ኢንተርናሽናል ጨዋታዎችን ለማስተናገድ እውቅናም ሳያገኝ አይቀርም ተብሏል።

በተያያዘ ዜና በካፍ ኮንፌዴሬሽን ዋንጫ ከሲሺየልሱ ክለብ ኮት ደ ኦር ጋር የተመደበው ደደቢት የመጀመሪያ የቅድመ ማጣሪያ ጨዋታውን ከሜዳው ውጪ ያደርጋል። አሰልጣኝ ንጉሴ ደስታን አሰናብቶ ዮሀንስ ሳህሌን የቀጠረው ደደቢት በኮንፌዴሬሽን ዋንጫ ሲሳተፍ ዘንድሮ ለሶስተኛ ጊዜ ነው።■

## ኢሳ ሀያቱ

# በአውሮፓ ሚዲያዎችን ዘገባ ተበሳጭተዋል



የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) ፕሬዝዳንት ካሜሮናዊው ኢሳ ሀያቱ የአውሮፓ ሚዲያዎች ዘገባ ተበሳጭተዋል። የምዕራባውያኑ ሚዲያዎች የአፍሪካ ዋንጫ ችግሮችን በጣም አጋነው በመዘገብ ከእነሱ ማነሳችንን ሊነግሩን ይፈልጋሉ ሲሉም ወቀሳቸውን አሰምተዋል።

በኢኳቶሪያል ጊኒ አስተናጋጅነት በተካሄደው የ2015 የአፍሪካ ዋንጫ እሁድ እለት በኮትዲቯር አሸናፊነት ተጠናቋል። ከፍጻሜው ጨዋታ በፊት በግማሽ ፍጻሜ ጨዋታ ኢኳቶሪያል ጊኒ ከጋና ሲጫወቱ ሜዳ ውስጥ የተፈጠረው ክስተት ግን የውድድሩን ገጽታ ያበላሸ ነበር። የአስተናጋጇ ሀገር ደጋፊዎች በዳኛ ውሳኔ ተበሳጭተው የጋና ቡድን ደጋፊዎች ላይ ጥቃት አድርሰዋል። ሜዳ ውስጥ በመግባትም ጨዋታው እንዲረበሽ አድርገዋል። የስታዲየሙን ንብረቶችም አውድመዋል። ካፍም ኢኳቶሪያል ጊኒ የ100ሺ ዶላር እንድትቀጣና ተጎጂዎችንም እንድታሳክም ውሳኔ አስተላልፏል።

በኢኳቶሪያል ጊኒና ጋና ጨዋታ ላይ የተፈጠረው ያልተገባ ጥፋት ክስተት እውነት ቢሆንም ኢሳ ሀያቱ ግን የምዕራባውያኑ ሚዲያዎች ግን አጋነው ዘግበውታል ብለዋል። "አሁንም አፍሪካን ቅኝ ለመግዛት የሚቋምጡ ናቸው" ሲሉም ተችተዋል።

"አውሮፓ ውስጥ አንዳች መጥፎ ነገር ሲፈጠር ስህተት ነው ይላሉ፣ አፍሪካ ውስጥ ሲሆን ግን ከሙስና ጋር አያይዘው ያወሩታል" ያሉት ፕሬዝዳንቱ፣ በ2012 የአውሮፓ ዋንጫ ማጣሪያ በሰርቢያና ጣሊያን ጨዋታ የተፈጠረውን ከፍተኛ ጸብና ውድመት ሚዲያዎች የዘገቡበትን መንገድ ለአብነት አስታውሰዋል።

"በሰርቢያና ጣሊያን ጨዋታ ምን ነበር የተፈጸመው? እዚህ የተፈጠረውም ተመሳሳይ ነገር ነው። ነገር ግን አፍሪካ ውስጥ ሲሆን እንደልዩ ነገር ታይቶ ይዘገባል። ይህ ተገቢ አይደለም። ክስተቱ እግር ኳስ ጨዋታ ላይ የተፈጠረ ነገር ነው። የምዕራባውያን ሚዲያዎች ግን ከሌላ ነገር ጋር በማያያዝ ይዘግቡታል። ይህ ቅኝ የመግዛት ስሜታቸውን የሚያጋልጥ ነው" ብለዋል።■

# ቅዱስ ጊዮርጊስ ኡጋንዳዊ አጥቂ አስፈርሟል



ቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ክለብ ቡድኑን ለማጠናከር የፊት መስመር ተጫዋች አስፈርሟል። ብራን ኦምኒ የተባለው ተጫዋች ከታንዛኒያው ኬኤፍ ኤፍ ክለብ በመልቀቅ ለጊዮርጊስ ለሁለት አመት ለመጫወት መስማማቱ ታውቋል።

የ26 አመቱ ኦምኒ የኡጋንዳ ብሔራዊ ቡድን አጥቂ በመሆን የሚጫወት ሲሆን፣ በክለቡ ኬኤፍ ኤፍ ውስጥም ግቦችን በማስቆጠር ይታወቃል። በቅዱስ ጊዮርጊስ ክለብ ውስጥም ግቦችን በማስቆጠር ቡድኑን ውጤታማ እንደሚያደርግ ታምኖበታል። ተጫዋቹ በኢትዮጵያ ለመስራት የሚያስችለውን ህጋዊ የስራ ፈቃዱን እንዳገኘ ለአዲሱ ክለቡ መሰለፍ የሚጀምር ይሆናል።

በካፍ የክለቦች ሻምፒዮና የአልጄሪያውን ክለብ ከሜዳው ውጪ የሚገጥመው ቅዱስ ጊዮርጊስ በፊት መስመር ቦታ ያለበትን ክፍተት እንደሚሸፍንም ይጠበቃል። ብራን ኦምኒ በቅዱስ ጊዮርጊስ የሀገሩ ልጆች ግብ ጠባቂው ሮበርት ኦዱንካራ እና አይዛክ ኢሴንዴ ጋር በመጫወት የሚጠቀስ ሶስተኛው ኡጋንዳዊ ይሆናል።■

ዳሸን ባንክ ግሎባል ፋይናንሻል ማርኬት ሪቪው ከተሰኘ አለም አቀፍ ተቋም እ.ኤ.አ. የ2014 በኢትዮጲያ እጅግ በጣም በዕድገት ግስጋሴ ላይ ያለ ባንክ ተብሎ ሽልማትና ዕውቅና ተቀዳጀ




በዚህ አጋጣሚ ባንካችን ለዚህ ክብር የበቃው በእናንተ ውድ ደንበኞቻችን ነውና እናመሰግናለን!!

ዳሸን ባንክ
Dashen Bank

2014 Most Progressive Bank Ethiopia
Global Financial Market Review

ስልክ (+251) 011 466 1380 ፋክስ (+251) 011 465 3037
dashen.bank@ethionet.et www.dashenbanksc.com

ለእድገት ትክክለኛ ምርጫ !